# ጅማ ዩኒቨርሲቲ


## የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል


## የድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

# አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ ሚና (በቢፍቱ ሚሊኒየም 2ኛ ደረጃ ትምህርት-ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


በ

ብዙዓለም ሙሴ ዉቤ



ጅማ ኢትዮጲያ

ሰኔ 2015 ዓ.ም

# አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ ሚና (በቢፍቱ ሚሊኒየም 2ኛ ደረጃ ትምህርት- ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጹሑፍ(አማርኛ) ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር


በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ በከፊል ሟሟያነት
የቀረበ ጥናት

በ


ብዙዓለም ሙሴ ዉቤ

ዋና አማካሪ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)
ረዳት አማካሪ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)



ሰኔ 2015 ዓ/ም
ጅማ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲሰ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጹሑፍ (አማርኛ) ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር፣የተማሪዎች፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ ሚና በሚል ርዕስ በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር (TeAm) ለሁለተኛ ድግሪ በከፊል ሚሟያነት የቀረበዉ ጥናት በዉስጥ እና በዉጭ ፈታኞች ተገምግሞ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| 1. የዋና አማካሪ ስም | ፊርማ | ቀን |
|---|---|---|
| ________________ | ________________ | ________________ |
| 2. የረዳት አማካሪ ስም | | |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| 3. የዉጭ ፈታኝ ስም | | |
| ________________ | ________________ | ________________ |
| 4. የዉስጥ ፈታኝ ስም | | |
| ________________ | ________________ | ________________ |

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ የሰዉን ስራ፣ መረጃና ሃሳብ ተገቢ የሆነ ምንጭ በመጥቀስ እንዲሁም የተጠቀምኩባቸዉን ተዛማጅ ጹሁፎች በሙሉ ምንጫቸዉን በትክክል በመጥቀስ በዋቢነት አቅርቢያለሁ፡፡ምክንያቱም የሰዉን ስራ፣መረጃ እና ሃሳብ ተገቢዉን ምንጭ ሳይጠቅሱ የራስ አስመስሎ ማቅረብ ሙያዊ ታማኝነትን የሚያሳጣ ከመሆኑም በላይ በዩንቨርሲቲዉ ህግ እና ደንብ መሰረት በዲስፕሊን የሚያስጠይቅ መሆኑን በሚገባ አዉቃለሁ፡፡ስለሆነም ይህ ጥናታዊ ጹሑፍ የራሴ ስራ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ________________________

ፊርማ ________________________

ቀን ________________________

# ምስጋና

ይህ ጥናት ከጅማሬዉ እሰከ ፍጻሜዉ እንዲከናወን የረዳኝ ፈጣሪ ከእናቱ ከድንግል ማሪያም ጋር ምስጋና ይግባዉ፡፡በመቀጠል ከትልመ ጥናት ንድፍ ጀምሮ ረቂቁን በማረም፣ በማስተካከል ጥናቱ ፈር እንዲይዝ ቅንነት በተሞላዉ ገንቢ አስተያየታቸዉን በመስጠት ለረዱኝ አማካሪዬ ለዶ/ር ምህረት ሳዳሞ ልባዊ ምሰጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም በማነኛዉም ሰዓት እርዳታቸዉ ባስፈለገኝ ጊዜ ሁሉ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጥናቱ ተጀምሮ እሰኪጠናቀቅ ላገዙኝ ለዶ/ር ለማ ንጋቱ ላቅ ያለ ምሰጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመቀጠል ጥናቱ ሙከራዊ በመሆኑ ከተተኳሪዎች ጋር ብዙ መቆየት ይጠይቅ ነበር፡፡ ስለሆነም ዉድ ጊዜያቸዉን ሰዉተዉ ልዩ እገዛ በማድረግ የተባበሩኝ ጓድኞቼ መምህርት ይርጋለም መኮንን እና መምህር ሞገስ ተመስገን የቢፈቱ ሚሊንየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር ዩሐንስ ገረመዉ ልበዊ ምሰጋናዬን አቀርባለሁ፡፡እያይዠም በሃሳብ፣ በገንዘብ ከጎኔ ለነበራችሁ የማከብራችሁ የምወዳችሁ ለዉድ ቤተሰቦቼ ልባዊ ምሰጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ፈተናዎችን በማረም፣አስተያየቶችን በመስጠት ሙያዊ እገዛቸዉ ላልተለየኝ የቢፈቱ ሚሊንየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህረት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ የቢፍቱ ሚሊንየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ልባዊ ምሰጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ሚና በሙከራዊ ጥናት ማረጋገጥ ነበር፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት በጉራፈርዳ ወረዳ ከሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የቢፍቱ ሚሊኒየም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በትምህርት ቤቱ ካሉት በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ዉስጥ 128 የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ይገኛሉ. ከነዚህም መካከል 64 ተማሪዎችን በቀላል እጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል።ከሙከራና ከቁጥጥር ቡድኑ በአንብቦ መረዳት ፈተና በቅድመ- ትምህርት እና በድህረ -ትምህርት ፈተና መረጃዎች ተሰብስበዋል። በፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች በአይነታቸው ከተደራጁ በኋላ መጠናዊ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት (Independent Samples t-test) ተሰልተው በገላጭና ድምዳሚያዊ ስታትስቲክስ ተተንትነዋል በቅድመ-ልምምድ ፈተና በመጀመሪያ ደረጃ ተጠኚ ተማሪዎችን በቡድን ደረጃ ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያላቸዉን ተማሪዎች የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል አስችሏል፡፡በዚህ መሰረት በቅደመ-ትምህርት የሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት(17.41) ሲሆን የቁጥጥር ቡድኑ በቅደመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (17.38) ሆልኗል፡፡ የጉልህነት ደረጃዉም( $p>0.05$) ነዉ። ስለሆነም በቅድመ-ልምምድ ፈተና በቁጥጥር ና በሙከራ ቡድኑ መካከል በአንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ከአማካይ ያለዉ ልዩነት (0.31) በመሆኑ የጎላ ልዩነት አይታይም፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ሁለቱም ቡድኖች ምንም አይነት የልምምድ ልዩነት ሳይኖራቸዉ በመደበኛዉ የማስተማሪያ ዘዴ ተምረዉ ያሳዩት ዉጤት ነዉ፡፡ ነገርግን ሁለቱም ቡድኖች ማለትም የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛዉ የማስተማሪያ ዘዴ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ በማስተማር ዘዴ ከተማሩ በኋላ ያመጡት ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት አማካይ ዉጤት 17.3 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ዉጤት 24.94 ሆኖዋል፡፡ ይህ በመሆኑም በድህረ-ልምምድ ፈተና የሙከራ ቡድኑ ከፍተኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በ(7.64) በልጦ ይታያል፡፡በቁጥጥር ቡድኑ እና በሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ ፈተና አማካይ ዉጤት መካከል ጉልህ ልዩነት ($p<0.05$) ታይቷል፡፡ከዚህም በመነሳት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የበለጠ አስተዋጽኦ አለው ከሚል መደምደሚያ ላይ ተደርሷል። ይህን መደምደሚያ መሰረት በማድረግ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴን ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና ቢሰጥ አጫጭር ልቦለድ በበቂ ሁኔታ በመማሪያ መጻፍ ዉስጥ ቢካተት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ አተገባበር በስፊትና በአግባቡ መተግበር አስላጊ እንደሆነ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ የወደፊት የጥናት ጥቆማዎችም ቀርበዋል፡፡

# የይዘት ማውጫ

ምስጋና ..... i
አጠቃሎ ..... ii
የይዘት ማውጫ..... iii
የሠንጠረዥ ማውጫ ..... vi
ምዕራፍ አንድ፣መግቢያ ..... 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር ..... 5
1.3 የጥናቱ መላምት ..... 8
1.4 የጥናቱ ዓላማ ..... 8
1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ..... 8
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 8
1.6 የጥናቱ ወሰን ..... 9
1.7 የጥናቱ አደረጃጀት ..... 9
ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት ..... 10
2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት ..... 10
2.1.1 የአጭር ልቦለድ ምንነት ..... 10
2.1.2 አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ያለው ሚና ..... 10
2.1.2.1 አጭር ልቦለድ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ መሆኑ፣ ..... 12
2.1.2.2 አጭር ልቦለድ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳድግ መሆኑ፣ ..... 14
2.1.3 አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ያለዉ ሚና፣ ..... 14
2.1.4 የአንብቦ መረዳት ምንነት ..... 18
2.2. ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ..... 21
ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ ..... 25

3.1 የጥናቱ ንድፍ ........................................................................................................ 26
3.2 የናሙና አመራረጥ ስልት ........................................................................................ 26
3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ................................................................................ 26
3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ .................................................................................... 27
3.2..3 የተማሪዎች አመራረጥ ...................................................................................... 27
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ...................................................................................... 28
3.3.1 ቅድመ- ልምምድና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎች ........................................................... 29
3.3.1.1 ቅድመ-ልምምድ ፈተና .................................................................................... 29
3.3.1.1 ድህረ-ልምምድ ፈተና ..................................................................................... 31
3.4 የምንባቦች አመራረጥ እና የትምህርት አቀራረብ ............................................................ 32
3.4.1 የምንባቦች አመራረጥ .................................................................................... 34
3.4.2 የመልመጃዎች አዘገጃጀት ................................................................................ 35
3.4.3 ቅድመ-ንባብ ተግባራት .................................................................................... 36
3.4.4 የንባብ ጊዜ ተግባራት ..................................................................................... 36
3.4.5 የድህረ-ንባብ ተግባራት .................................................................................... 37
3.5 የአጠናን ሒደት ....................................................................................................... 37
3.6 የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ስልት ................................................................................ 39
ምዕራፍ አራት: - የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ .................................................. 39
4.1 የመረጃ ትንተና ....................................................................................................... 40
4.1.1.ከፈተናዎች የተገኘ የጥናቱ መረጃ ትንተና ............................................................... 40
4.1.1.4 የሙከራ ቡድኑ የቅደመ-ትምህረትና የድህረ-ትምህርት .............................................. 44
4.2 የውጤት ማብራሪያ .................................................................................................. 45
ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች ............................................ 47
5.2 መደምደሚያ ........................................................................................................... 50
5.3 የመፍትሔ ሃሳቦች ................................................................................................... 51

ዋቢ .......... 52
አባሪ .......... 55
አባሪ “ሀ “ .......... 55
የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና .......... 55
አባሪ “ለ” .......... 60
የድህረትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና .......... 60
አባሪ “ሐ” .......... 68
አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ለማስተማር የቀረቡ ቴክስቶች .......... 68
አባሪ “መ” .......... 100
የቅድመ ፈተና የፓይለት ዉጤት .......... 100
አባሪ “ሰ” .......... 102
የሙከራ ና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት .......... 102
አባሪ “ረ” .......... 103
የድህረ ፈተና የፓይለት ውጤት .......... 103
አባሪ “ሸ “ .......... 104
የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ድህረ ፈተና ዉጤት .......... 104
አባሪ “ቀ” .......... 105
የተሰላ የSPSS ውጤት .......... 105

# የሠንጠረዥ ማውጫ

4.1.1.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ- ትምህርት ፈተና....................................... 40
ሠንጠረዥ፡-4.1.1.2 የድህረ -ትምህረት አንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤት የሙከራና
የቁጥጥር ቡድኑ ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት............................................................... 42
ሠንጠረዥ 4.1.1 .3፡- የቅደመ-ትምህረትና የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት የቁጥጥር
ቡድኑ ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት............................................................... 43
ሠንጠረዥ4.1.1 4፡-የሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትእና የድህረ-ትምህርት የአንብቦ
መረዳት ፈተና ዉጤት ንጽጽር በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት................................................ 44

# ምዕራፍ አንድ፤መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስነጽሑፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት የመጠቀም ጽንሰ ሀሳብ እየታወቀ የመጣው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡ ከዚያ በፊት የነበረው የቋንቋ ትምህርት አሰጣጥ ስዋሰዋዊ የአቀራረብ ዘዴን የተከተለ ነበር፡፡ ነገር ግን የቋንቋ ትምህርቱ ወደ ተግባቦታዊ አቀራረብ በማዘንበሉ የተነሳ፣መዋቅራዊ አቀራረብና ቀጥተኛ እዝን አፋዊ /audio lingual method/ ዘዴዎች እየታወቁ መጡ ታዲያ በዚህ ወቅት ለስነጽሑፍ ትኩረት ማጣት ዋነኛ ምክንያት የነበረዉ ስነጹሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያነት መጠቀምያለውን ፋይዳ ሙሁራን በጥናታቸዉ አጉልተው አለማሳየታቸው እንደሆነ ያስረዳሉ (Khatib and Rahimi 2012)፡፡

በኋላ ግን በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር የሚለው ፍላጎትና ተነሳሽነት እንደገና ከ1980ዎቹ ጀምሮ ተሻሽሎ እንደቀጠለ ያስረዳሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ስነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ሚና የሚያሳዩ በርካታ መጽሐፍት መታተማቸውን ተከትሎ እንደሆነ Duff maley et al (2005) ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ (Khatib and Nasrollahi 2012) ፡፡ ስነጽሐፍን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም የሚለው ጽንስ ሀሳብ መነሻው የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ለንግግር ቋንቋ ማለትም፣ ተግባቦታዊ የቋንቋ አጠቃቀም ከፍተኛ ትኩረት እያገኘ በመምጣቱ እንደሆነ ከቀረቡት መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚያበረክተውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አስመልክቶ በርካታ ምሁራን አስተያየቶችን ቢሰነዝሩም አሁን ባለው የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስነጽሁፍ ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ የሚችል ድርሻ የለውም፡፡ ከ1966 ዓ/ም በኋላ ሀገሪቱ የተከተለችው ፍልስፍና ነጸብራቅ የነበረው ስርዓተ ትምህርት የቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍት ከየትምህርት አይነቱ የተውጣጡ ደረቅ እውነታዎችን የያዙ ምንባቦች የታጨቁባቸው መድብሎች አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ለቋንቋ ትምህርት እውነተኛ አውድ ከማሳጣቱም በላይ በእጅጉ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ፍላጎት አጥቅቶታል (በድሉ 1996)፡፡አጫጭር ልቦለዶችን ለማስተማሪያ መሳሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን ችሎታ ለማሳደግ በጣም ውጤታማ ነው ይህም የሆነበት ምክንያት ሳቢና ማራኪና አስደሳች በመሆኑ ተማሪዎች ለማንበብ ሂደቱን

ለመቀላቀል ጉጉት እና ፍላጎት እዲያድርባቸዉ የማድረግ ባህሪ ስላለዉ ነዉ፡፡ አጫጭር ልቦለዶችን መጠቀም በመማር ማስተማሩ ሂደት ውስጥ መሻሻል እንዳለ አመልክቷል (Jeni 2020) ፡፡

አጫጭር ልቦለዶችን እንደ ማስተማሪያ መሳሪያ መጠቀም በተለይ የማንበብ ግንዛቤን ለማሳደግ በጣም ጥሩ መንገድ እንደሆነ ይገልጻሉ።

ምክንያቱም አጫጭር ልቦለዶች ተማሪዎች በቀረበው ጽሑፍ ዙሪያ ክርክሮች እንዲያደርጉ፣ እንዲጽፉና እንዲነጋገሩ፣ የተለያዩ ፍቺዎች እንዲያመነጩ በማስቻል፣ የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ በማበልጸግ በታሪኩ የሚተላለፉትን ሃሳቦችን በጥልቀት እንዲገነዘቡ ያደርጋቸዋል ምክንያቱም አጫጭር ልቦለዶች በፈጠራ ስራ የታጨቁ በመሆናቸዉ የተማሪዎችን ስነልቦና መግዛት የሚችሉ ናቸዉ።

ይሁን እንጂ መምህራን አጭር ልቦለድና ሌሎች ስነጽሑፍን በቋንቋ መማር ማስተማሩ ሂደት እንደ ክፍተት መሙያ አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በማያያዝ አጫጭር ልቦዶች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሚያዳብር፣ እንደሚያሰፋ፣ በትርጉም ወይም በፍቺ የበለጸገ መሆኑን አስረድተዋል (Ghasemi 2011):: በዚህም መሰረት አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ሚና አጉልተው የሚያሳዩ ማብራሪያዎችን ስንመለከት፣ አጭር ልቦለድ የሰው ልጅ ወግና ልማድ፣ባህል፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች የሚገልጹበት መሆኑ፣ሳቢ ማራኪ የንግግር ቋንቋ የሚቀርብበት፣ ሳቢነት ያለውና በባህል የበለጸገ መሆኑ፣ተማሪዎችን ከማህበረሰቡ ጋር የበለጠ የሚያቀራርብና የሚያስተዋውቅ በመሆኑ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር አንዱ ፈጣን የላቀ ድርሻ አለው በማለት ይገልጻሉ (Jeni 2020)::አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያዳብራል፣ይህም የሚሆነው ተማሪዎች በአጭር ልቦለድ ሥራ የቀረበላቸውን መነሻ ሀሳብ ወይም መልዕክት መሠረት በማድረግ እዲወያዩ፣እዲከራከሩ የተለያዩ ቃለ-ምልልሶችን እያደረጉ እንዲማሩ፣ ያስችላቸዋል ይህን በተመለከተ Ghasemi (2011) ያስቀመጡትን ስንገነዘብ፣ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር፣ ተማሪዎች በቀረበው ጽሑፍ ዙሪያ ክርክሮች እንዲያደርጉ፣ እንዲጽፉና እንዲነጋገሩ፣ የተለያዩ ፍቺዎች እንዲያመነጩ በማስቻል፣የእርስ በእርስ መስተጋብራቸው የበለጠ ዳብሮ እንዲታይ ያደርጋል፣ በማለት ያብራራሉ፡፡

የአጫጭር ልቦለድ ይዘቶች የተማሪዎችን ምናባዊነት ያጎለብታሉ፣ያነሳሳለ፣እውነተኛውን ቋንቋ እንዲጠቀሙ፣የቡድን ውይይቶች ላይ እንዱሳተፈ፣ ቃለ-ምልልሶችን እንዲያደርጉ

እና የግል ስሜታቸውን እንዲገልጹ ያስችለዋቸዋል በማለት ገልጸዋል፡፡ ከገለፃዎቹ የምንረዳው የአጭር ልቦለድ ይዘቶችን ተጠቅመን ስናስተምር የተማሪዎች ተሳትፍ የዳበረ ይሆናል ሀሳባቸዉን የመግለጽ ነፃነት ይኖራቸዋል፡፡ተማሪዎች የነቃ ተሳትፍ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል፣ሀሳባቸውን እንዱገልጹ ሰፊ ዕድል ይፈጥርላቸዋል ይህም ተነሳሽነታቸውን የበለጠ እንደሚያሳድግ አበራረተዋል፡፡

Carter et al (1986) አጫጭር የልቦለድ ታሪኮች ተማሪዎችን ማነቃቃትና ፣ማነሳሳት በተመለከተ፣ ተማሪዎች የማንበብ ልምድ ሲኖራቸዉ የቀረበን ጽሑፍን በማወደደርና በማመሳሰል ሁኔታ በተነሳሽነት ያነቡታል፡፡ የትምህርቱ አቀራረብም ተማሪዎች አስቀድሞ በራሳቸው የተለያዩ ቃላዊ ትረካዎችን እንዲናገሩ በማድረግ የተሰጣቸዉን ጽሑፍ ወይም አጫጭር ታሪክ በትምህርቱ ይዘት ውስጥ የሚያሰርጻቸውን ስሜቶች በተመለከተ Khatib and Nasrollahi (2012) በትምህርት ውስጥ ክሂሎችን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ አጫጭር የልቦለድ ሥራዎችን በተነሳሽነት ተማሪዎች ያነባሉ፣ሲነበብላቸውም በጥልቀት ያዳምጣሉ፣በአነበቡትና ባዳመጡት ነገር ላይ ተመስርተው ሀሳባቸውን ያንፀባርቃሉ፡፡ የተለያዩ የህይወት ገጽታዎች ግንዛቤ ያገኛሉ፡፡ በዚህም በአስተሳሰባቸዉ ጥልቅ አሳቢ ይሆናሉ፡፡ አጫጭር ልበወለዶች በዚህ ሂደት ተማሪዎች የባህሪ ለውጥን እንዲያመጡ የላቀ ድርሻ አላቸዉ፡፡

በሌላ በኩል አጫጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የመገመትና ትርጓሜ የመስጠት ችሎታን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ምክንያቱም የአጭር ልቦለድ ይዘቶች የተለያዩ ደረጃዎች ባሏቸው ትርጉሞች የበለፀጉ በመሆናቸው ተማሪው በንቃት በመሳተፍ ፊት ለፊት ያልተገለጹ ነገሮችንም አውጥተው ማየት እንዱችሉ ያስችላቸዋል በማለት ያብራራሉ (Carter et al 1986)፡፡ ከገለጻዎቹ የምንረዳው አጫጭር ልቦለዶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም፣ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፍ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎቹ የመመራመርና አእምሮን የማሰራት ሁኔታን ስለሚፈጥርላቸው በቋንቋ ትምህርት የበለጠ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዲያገኙ የሚያስችል አቀራረብ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

አጫጭር ልቦለዶች የአንብቦ መረዳት ችሎታን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ለማዳበር ስላላቸው ሚና ከተለያዩ አስረጅዎች አንፃር ባጭሩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ በመቀጠልም ይህ ጥናት ትኩረት በአደረገበት አጫጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ

ማስተማር ከተማሪዎች አንብቦ መረዳት ጋር ያለውን ቅንጂት፣የተለያዩ ሙሁራን ወይም አጥኝዎች ያዩበትን መንገድ እንመለከታለን፡፡

እንደሚታወቀው አንብቦ መረዳት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰፊ ድርሻ አለው፡፡ አንብቦ መረዳት ሲባል፣ቋንቋን በአእምሮ መረዳት ብቻ ሳይሆን ምንባቡ ወይም ጹሑፉ የሚያስተላልፈውን መልዕክት ፣መገንዘብ፣መረዳት ነው በማለት ይገልጻሉ (Ghasemi 2011)፡፡ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የአንብቦ መረዳት ብቃት ለማዳበርና ለማሳደግ የተለያዩ ምንባቦች ሊቀርብላቸው ይችላል፡፡

ይህንን የአንብቦ መረዳት ብቃት ለማምጣት ደግሞ አጫጭር ልቦዶች የመጀመሪዉን ቦታ እንደሚይዙ እና ለዚህም ዋናው ተጠቃሽ ምክንያት የሚሆነው አጫጭር ልቦለዶችን ተማሪዎች በሚያነቡበት ወቅት በሳቢነታቸው ስለሚማረኩ ነው፡፡ በምንባቡ ውስጥ ባለው ሀሳብ የመስማማት፣ የመከራከር፣ የመረዳዳት፣የመነሳሳት ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፤ ተማሪዎች በላዕላይ ከተላለፈ መልዕክት ይልቅ በሚስጢር ያለዉን ሀሳብ ለመረዳት ትልቅ ፍላጎት ያድርባቸዋል በዚህም እርካታን ያገኛሉ፡፡ ሌሎች ስነ-ጽሁፍ ያልሆኑ ጽሁፍችን ሲያነቡ ግን የሚረዱት ቀጥታ ጽሁፉ ላይ ያለውን ሀሳብ ብቻ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Ghasemi (2011) ከዚህ በመነሳት አጫጭር ልቦለዶች፣ በባህሪያቸው ዘመናዊነት ያላቸው በመሆኑ እንዱሁም በዓይነት የተለያዩ መሆናቸው ለቋንቋ ተማሪዎች ሳቢ እንዱሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ለዚህም ደረጃቸውን የጠበቁ ሥራዎች፣ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን ሁኔታ መመረጥ እንዳለባቸው ያስገነዝባሉ፡፡

Ghasemi ( 2011) ከዚህ ጋር በተመሳሳይ መልኩ ተማሪዎች አጫጭር ልቦለዶችን በሚያነቡበት ጊዜ ያልደረሱበትን ታሪክ ለማወቅ ሲለ በከፍተኛ ተነሳሽነት ያነባሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ትረካውን በተመስጦ እንደያነቡ ያስችላቸዋል ባነበቡት ነገር ላይም ምላሽ ይስጣሉ፡፡ እነዚህን መሰል ተግባራት ስንመለከት አጭር ልቦለድ ክፍል ውስጥ ያለውን የመማር ማስተማር ሁኔታ ከተማሪዎች ህይወት ጋር ስለሚያስተሳስር፣ ተማሪዎች በንቁ መንፈስ እንዲከታተሉት ያደርጋል በማለት ያአስረዳሉ፡፡

Lazar (1993)ተማሪዎች የአጫጭር ልቦለድ ምንባቦች ሲያነቡ፣ራሳቸውን በታሪኩ ውስጥ እንዳለ በመቁጠር፣ እንዲተነብዩ ፣ከታሪኩ ጋር እንዲያዋህዱና ያላቸውን አስተውሎት ከታሪኩ አንፃር እንዲያዩ በማድረግ፣ግላዊ ተሳትፍአቸው እንዲጎለበቱ ያስችላቸዋል በማለት Slater (1987)ን ዋቢ በማድረግ ያብራራል (Lazar 1993) ፡፡

Lazar (1993) በተከታታይ ከሰጡት ማብራሪያ መገንዘብ እንደሚቻለው አጫጭር ልቦለዶች የአንባቢን ስሜት የሚገዙ መሆናቸው፣ተማሪዎች ቀጣዩ ምን ይሆን በማለት በጉጉት ያነቧቸዋል፡፡ ሌላው በህሪያቸው ዘመናዊነትና የተለያዩ ዓይነት መሆናቸው ሳቢነታቸውን ያጎለዋል፡፡ ተማሪዎች አስደናቂና ዘመናዊ ትረካዎችን ማንበብ እንዲችሉ ሰፊ አማራጮችን ይፈጥርላቸዋል፡፡ በአነበቡት ነገር ላይ ተመስርተውም ከነባራዊው ዓለም ጋር በማስተሳሰር ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩና ስሜታቸውን እንዲገልጹ ያስችላቸዋል፡፡ ሰለሆነም አጫጭር ልቦለዶች ለክፍል ደረጃው በሚመጥን መልኩ እየተመረጡ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ቢካተቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳትና የማመዛዘን ችሎታ እንደሚያሻሽል መረዳት ይቻላል፡፡በመሆኑም አጥኚዋ አጫጭር ልቦለድችን ተጠቅሞ በማስተማር በቢፍቱ ሚሊኒየም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ ሚና ለመፈተሽ ተነሳስታለች፡፡

## 1.2 የጥናቱ መነሻ ችግር

የዚህ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ አጭር ልቦለዶን ተጠቅሞ ማስተማር፣ የተማሪዎችን፣ ፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ሚና የሚል ነው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ከመነሻዉ በተጠቀሰው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ለማጥናት ምክንያት የሆናት ፣ ባስተማረችበት ትምህረት ቤት ችግሩን በስፋት ያስተዋለች በመሆኑእና በተለያዩ ይንቨርሲቲዎች ላይ የተሰሩ ጥናቶችን በመዳሰስ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ክፍተቶች መኖራቸዉ ነዉ፡፡ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማና ብቁ እንዲሆኑ ከሚያስፈልጓቸው ክሂሎች አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ ስለሆነም ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል (Hyland 1990) ፡፡ ለተማሪዎች ለክፍል ደረጃዉ የሚዘጋጁት ምንባቦች የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያለምንም ችግር ሐሳቡን መረዳት፣ መተርጎምና ማብራራት መቻልን አጠቃሎ የያዘ ችሎታ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠዉ ያስፈልጋል (በድሉ 1996)፡፡

በተጨማሪ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ሊሆን የቻለበት ምክንያት በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ማሻሻልን ማዕከል ያደረገ የትምህርት ዕጦት መኖር ነው ሲሉ ያስረዳሉ (Madarega et al 2010) ፡፡

እንዲሁም Lumquinga (2012) ሲያሰረዱ በትምህርት ቤት ውስጥ የማንበብ ዋናው ጠቀሜታ ተማሪዎቹ ቃላትን ማንበብ እንዲማሩ እንጂ የቃላቱን ትርጓሜ እንዲረዱ

አይደለም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ቃላትን ብቻ እንዲናገሩ የሚደረጉ ከሆነ የተናገሯቸዉን ቃላት ፍቺ ሲጠየቁ መመለስ አይችሉም፡፡ ይህ ደግሞ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከእለት ወደእለት እንዳይሻሻል ያደርገዋል፡፡ስለዚህ ተማሪዎች ከማንበብ ጋር ሳይተዋወቁ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ሳይኖራቸው የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቃሉ፡፡ ስለሆነም የአብዛኞቹ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ነው፡፡ ጥሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ስለሌላቸው የሚያነቡትን ምንባብ በሰፊው እንዳይረዱት አድርጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም በትምህርት ውጤታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል (Conely 1992)፡፡

በተጨማሪ Atkins et al (1996) በርካታ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የዳበረ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ስለሌላቸው የሚያነቡትን ጹሑፍ በሰፊው እንዳይመለከቱና በትምህርት ውጤታቸው ላይም አሉታዊ ተጽእኖ እንዳሳደረ ያስረዳሉ፡፡

Bintiz (1997) በአንብቦ መረዳት ዙሪያ ከ100 በላይ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት ምህረት ቤት የሚያስተምሩ መምህራንን ጠይቀው በሰበሰቡት መረጃ መሰረትም ሁሉም መምህራን የተማሪዎቻቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያልዳበረ መሆኑን በጥናታቸው አመላክተዋል፡፡

በርካታ የሀገር ውስጥ ምርምሮች የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያልዳበረ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ ለአብነት ተሾመ (1997) በከንባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አመላክተዋል፡፡ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ የመሆን ምክንያትም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አሰጣጥ ችግር መሆኑን ከጥናቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም መሰረት (2007) በአንካሻ ወረዳ በሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሒል ትምህርት አቀራረብ ቅኝት በሚለው ጥናታቸው የደረሱበት ድምዳሜ መምህራን ለማንበብ ክሂል የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ እንደሆነ፤ የማንበብ ክሂልን በመተግበር ሂደት ተጽእኖ የሚያደርጉ ጉዳዮች እንዳሉ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ታፈረ ( 2000) በዳንግላ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ዳራና አንብቦ የመረዳት ችሎታ በሚለው ጥናታቸው የተማሪዎች የማንበብ ክሒል በዝቅተኛ ደረጃ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

እነዚህ ጥናቶች ችግሩ መኖሩን አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም መፍትሄ ለመፈለግ ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ጥናቱ ተከናውኗል በተጨማሪም አጥኚዋ በምታስተምርበት ወቅት ያስተዋለችዉ ችግር ተማሪዎች ምንባብ በሚያነቡበት ጊዜ

ቃላትን በተቆራረጠ ድምጽ ፣አዝጋሚ በሆነ ፍጥነት በመታገል የሚያነቡ መሆናቸው ፣ አንዳንዴም ድምጽ በማሰማት እንዲያነቡ ሲጠየቁ ፍቃደኛ አለመሆናቸውን ተገንዝባለች፡፡ በዚሁ ልክ የአንብቦ መረዳት ጥያቂዎችን የመመለስ አቅማቸው ያነሰ ነው፡፡ አብዛኛዎቹ የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በመጸሐፉ ለቀረቡት የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች የመተንበይና አጠቃላይ ሀሳብ የመስጠት አቅማቸው ዝቅተኛ በመሆኑ፣ከምንባቡ የወጡ የ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› ጥያቄዎችን በምክንያት አስደግፌው እንዲመልሱ ሲታዘዙ የተብራራ መልስ ለመስጠት ሲቸገሩ ይስተዋላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ጥልቅ ግንዛቤ የሚጠይቁ በአመስጥሮ በምርመር ሊገኙ የሚችሉ ሃሳቦችን የመገንዘብ አቅማቸው ያነሰ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ችግር እንዴት ሊፈታ ወይም ሊቃለል ይችላል? የሚለውን አጥኚዋን ሲያሳስባት የነበረ ጥያቄ በመሆኑ፣ለጥናቱ መነሻ ምክንያት ሆኗታል፡፡ ከችግሩ አሳሳቢነት በመነሳት የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችግር ለማቃለል የቋንቋ ትምህርቱ በአጭር ልቦለድ መሳሪያነት ቢሰጥ ችግሩን ሊቃልል ይችላል የሚል መላምት አጥኚዋ ነድፋለች፡፡

በመቀጠልም አጥኚዋ ይዛ ከተነሳችዉ የጥናት መላምት ጋር የሚቀራረቡ ጥናቶችን ለመነሻነት ተመልክታለች፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ፣በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ ጥናት አቅራቢ በተጨባጭ ከመነሸው ለመጠቆም እንደሞከረችዉ በመማር ማስተማር ሂደት ያስተዋለችው የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችግር መኖር፣ ጥናት ለማካሄድ ዋነኛ አነሳሽ ምክንያት ሆኗታል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የዚህ ጥናት አቅራቢ ባደረገችው ፍተሻ መሰረት፣ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር ለማቃለል የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም፣ማስተማሪያ ሞዴልን መሰረት ያደረጉ፣የስነ-ጽሑፍ ዘሮች ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡበት መንገድ የተመለከቱ እንዲሁም ችግሩ መኖሩን የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ከዚህ አንጻር የአንብቦ መረዳትን ችግር ለማቃለል ሌላ መንገድ ሊኖር ይችላል በሚል አነሳሽ ምክንያት፣ አጭር ልቦለዶን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችግር ሊያቃልል ይችል ይሆን? የሚል መላምት በመንደፍ ይህን ጥናት ተካሂዷል፡፡

ይህን መነሻ ሀሳብ መሰረት በማድረግ አጥኚዋ አጭር ልቦለዶን ተጠቅሞ ማስተማር፣ የተማሪዎች፣ አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን ሚና ማረጋገጥ በጉራፈርዳ ወረዳ በቢፍቱ ሚሊኒየም ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአስረኛ ክፍል ተተኳሪነት ላይ ጥናቷን አካሂዳለች

## 1.3 የጥናቱ መላምት

የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉ አስተዋጾ አዎንታዊ ይሆን ወይስ አሉታዊ የሚል አማራጭ መላምት በመጠቀም አማርኛ ቋንቋ ለሚማሩ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን ለማሻሻል ያለዉን ጠቀሜታ በከፊል ሙከራዊ ጥናት ለማረጋገጥ መሞከር ነዉ፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ዉጤታማነቱን ፈትሾ ለመረዳት ጥናቱ የሚከተሉትን መላምት ይዞ ተነስቷል፡፡

1. ከሙከራ ጥናቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑም ሆነ በቁጥጥር ቡድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ ይኖራል (H1=አማራጭ መላምት)
2. ከሙከራ ጥናቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑም ሆነ በቁጥጥሩ ቡደድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም (H0=አልቦ መላምት)

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር፣ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለው ሚና መመርመር ነው፡፡

### 1.4.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ በማስተማር፣ የምንባቡን ገጻዊ ወይንም ቀጥተኛ መልክትን መረዳት ላይ ያለዉን ሚና መመርመር፡፡
- አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋ በማስተማር በምንባቡ የተገለጸዉን በመመርኮዝ በመተንበይ ፣በመገመት ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት ያለዉን ፋይዳ መመርመር፡፡

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት አጭር ልቦለደ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ሚና ለመፈተሸ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ በመሆኑ የሚከተለትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚዳብርበት ሁኔታ ምላሽ የሚስገኙ መረጃዎችን ለማስገኘት ይረዳል፡፡
2. አጭር ልቦለድ ለአንብቦ መረዳት ማስተማሪያነት ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ሚና በመረዳት መምህራን የማስተማር ስልታቸዉን እዲቀይሱ ያደርጋል፡፡

3. ትምህርት ቤቱ ከጥናቱ የሚገኘዉን ዉጤት ተንተርሰዉ ለተማሪዎች የሚመጥኑ አጫጭር ልቦለድ መጻሐፎቶች በቤተ መጻሐፍት እዲገኙ እዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡

4. የቋንቋ ስራዓተ ትምህርት እና የማስተማሪያ መጽሐፍት አዘጋጆች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚስችሉ አጫጭር ልቦለዶችን እንዲያካትቱ አስተዋጾ ያደርጋል፡፡

5. አጫጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ ማስተማር በተመለከተ ለሚነሱ ጥናቶች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት አጭር ልቦለዶን ተጠቅሞ ማስተማር፣የተማሪዎችን፣የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር ላይ ያለውን ሚና መፈተሸ በሚል ርዕስ የተጠና ነዉ፡፡ጥናቱ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጲያ ቤንች ሸኮ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ በቢፍቱ ሚሊኒየም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 2015 ዓ.ም የአስራኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት ያደረገ ነዉ፡፡ አጥኚዋ የቁጥጥር ቡድኑን በተለመደዉ መንገድ እንዲማሩ ያደረገች ሲሆን የሙከራ ቡድኑን ደግሞ አማርኛ ቋንቋ ለማስተማር የተጠቀመችዉ አጫጭር ልቦለዶችን ነዉ እንጂ ሌሎች የስነጹሑፍ ዘሮችን አልተጠቀመችም በመሆኑም አጭር ልቦለድ በአማረኛ ቋንቋ ትምህርት ዉስጥ አንብቦ መረዳት ላይ ያለዉን ሚና መርምራለች፡፡ጥናቱ ሌሎች ክሂሎችንና ሁለቱን እወቀቶች ላይ ሊደርስ የሚችለዉን ተጽኖ ትኩረት አላደረገም፤፡ ስለሆነም የጥናቱ ዋና ትኩረት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር ላይ ያለዉን ሚና ማረጋገጥ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

## 1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ጥናቱ በአምስት ምዕራፎች የተደራጀ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ምዕራፍ የመግቢያ ክፍሉ የሚዳስሰው የጥናቱ ዳራ ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ መላምት ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ ጠቀሜታ እና የጥናቱ ወሰን ያካተተ ነዉ፡፡ ሁለተኛው ምዕራፍ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የተለያዩ ዝርዝር መረጃዎችን የያዘ እና የቀረበዉን መረጃን የሚመለከቱ ተዛማጅ ጽሑፎችን ክለሳ ድርሳን ይዞል ። ሦስተኛው ምዕራፍ የምርምሩ ዘዴ፣ የንሞና አወሳሰድ፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ እና የመረጃ ትንተና ዘዴን ያጠቃለለ ነዉ። ምዕራፍ አራት ስለ መረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ ይገኝበታል።በመጨረሻም፣ ምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ፣ መደምደሚያ እና አስተያየት አጥቃሎ ይዟል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት አጭር ልቦለዶን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር ያለዉን ሚና መፈተሽ ነዉ፡፡ ይህ መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳብ ለማብራራት በትኩረት ነጥቡ ዙሪያ ያሉ ተዛማጅ ጹሑፎችን ለመዳሰስና ትንተና ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡.

## 2.1 ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የአጭር ልቦለድ ምንነት

አጭር ልቦለድ ፈጣን አተራረክ እና ድርጊት የሚታይበት፣ገጠመኞችን የያዘ አንጊና ወደ አንድ አርኪ መቋጫ የሚደርስ እንደሆነ ዘሪሁን (2007) ቼኾቨንን በመጥቀስ ያብራራል፡፡ ከዚህ በማስከተል ዘሪሁን (2007) አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ-ጽሐፍ ዘሮች ተለይተው የሚታወቁበትን ባህሪያት ሲገልጹ አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ጥብቅ ትስስር ያለው፣ እንዲሁም ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው መሆኑን አብራርተዋል ከዚህ በተጨማሪ አጭር ልቦለድ አካባቢንና ማህበረሰብን ለመረዳት ያስችላል በማለት ይገልጻል፡፡ትረካዎች ከመጠን አንጻር እስከ አምስትመቶ ቃላት የያዙ ትረካዎች ናቸው፡፡አጫጭር ትረካዎች እስከ አስራ አምስት ሺህ ቃላት የሚደርስ የሚይዙ ከሆነ አጭር ልቦለድ ይባላሉ፡፡አጫጭር ትረካዎች እንደ ቀልድ ቀላል የሆኑ ወይም ውስብስብነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡በእየለት ውሎዎቻችን የምናደርጋቸው ቃለምልልሶች፣ ውይይቶች በአጫጭር ትረካዎች የተሞሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ አጫጭር ትረካዎች የተለያዩ ልምዶችን፣ ጽንስ ሀሳቦችን ለመናገር ያስችላሉ፡፡ ምናልባትም አጫጭር ትሪካዎች ስንሰማቸው፣ ስናነባቸው ሊያስደንቁን ይችላሉ:: በተለያየ ቦታና ጊዜ ስላሉ ሰዎች እንድናውቅ ያደርጋሉ፡፡እንዲሁም የራሳችንን ህይውት ከሌላው ጋር በማወዳደር ስለህይወት የተለያዩ ፈርጆች ግንዛቤ ማስገኘት የሚያስችሉ ናቸው በማለት ስለ አጫጭር ትረካዎች ምንነት አብራርተዋል (Bachman 1999)፡፡

### 2.1.2 አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ያለው ሚና

አጭር ልቦለድ ቋንቋን ለማስተማር በስርዓተ-ትምህርት ውስጥ ሊካተት የቻለበትን ሁኔታ አጀማመሩን ለመቃኘት ተሞክሯዋል፡፡ አያይዘንም አጭር ልቦለድ ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና በዝርዝር እንመከታለን፡፡

አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር ያለውን ሚና በተመለከተ እንደገለጹት አጭር ልቦለድ የቋንቋን ትምህርቱን የበለጠ ለመገንዘብ የሚረዳ፣ ስነ-ልሳናዊ ትምህርት ግባትን በመፍጠር ሰፊንባብ ለማድረግ ያስችላል (Ghasemi 2011)፡፡ተማሪዎች አውድን በመፍጠር አንብቦ የመረዳት አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ በአጭር ልቦለድ ውስጥ የተለያዩ ቅርጾች በማስገኘት ተማሪዎች ለንባብ እንዲነሳሱ እድል ይፈጥርላቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ከገለጻው መረዳት እንሚቻለው የአጭር ልቦለድ ስራ በእውነተኛው አውድ ማቅረብ ስለሚችል የተለያዩ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችና የቋንቋ ቅርጾችን የማሳየት አቅም አለው ተማሪዎችም በቀረበው አውድ መሠረት የተለያዩ ተግባራትን መስራት መቻላቸው የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን የማዳበር እድላቸዉን ያሰፋዋል፡፡

አጫጭር ልቦለድ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ እውነተኛ አውድን መፈጠር በመቻል ከፍተኛ ድርሻ አለዉ ይህን አስመልክቶ Khatib and Nasrollahi (2012) Murdoch (2002)ን በመጥቀስ ሲያስረዱ 'ተማሪዎች ቃላትን ዕለት ከዕለት ማህበራዊ ግንኙነት ትርጉማቸውን ይረዳሉ፡፡ እንግዳ የሆኑ ቃላት በሚገጥማቸው ጊዜ ከቋንቋ ስነ-ልሳናዊ አገባብ ዙሪያ ትርጉሙን ለመረዳት ይጥራሉ እንጂ መዝገበ ቃላት ፍለጋ ላይሄድ ይችላሉ በማለት ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ከሚቀርብላቸው አውድ የስዋሰውን እና የቃላት ትርጉምን ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡ እውነተኛና ተማሪዎች ሊገነዘቡት የሚችሉት የትምህርት መሳሪያ፣ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እንዲሰሩ ያበረታታቸዋል፡፡ ተማሪዎች ከሚቀርብላቸው የተለያዩ አውዶች የቋንቋ መዋቅርን፣ የቃላት አውዳዊ ፍችን፣ በተለያዩ ሀረጋትና ዓርፍተ ነገሮች ያሉ ገለጻዎችን ና ጽንስ ሀሳቦችን በነቃ መንፈስ ይከታተላሉ፡፣ ሰፊ የንባብ አጋጣሚም ይፈጥረላቸዋል፣ በመናገር፣ በክርክር፣ ለቃላት ትርጓሜ በመስጠት ሲሳተፉ ከታሪኩ ጋር የመዋሃድ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርላቸዉ Bachman (1999) Krashen (1982)ን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡

ከ Lazar (1993) ገለፃ መረዳት እንደሚቻለዉ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ አውዳዊ አቀራረብ መኖር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማዳበር እንደሚቻል ነው፡፡ ምክንያቱም አጭር ልቦለድ የጋሀዱ አለም እውነታ የሚንጸባረቅበት በመሆኑ ተማሪዎች በጽሁፍ ይዘቶች ሲማሩ የአርፍተ ነገር አወቃቀር፣ የቃላት አጠቃቀምን ያገኛሉ፡፡

ለረዥ ክፍለ ዘመናተ የተፃፉት ልቦለዶች ዛሬም ስለሰው ልጅ መሰረታዊ ባህሪያት የሚሰጡት መረጃ ከፍተኛ ነው፡፡ ዘመንና ባህል አያግዳቸውም ከተፃፈበት ባህልና ዘመን

አድማስ ባሻገር ቅናትን ፣ ፍቅርን ፣ ጀግንነትን ፣ ስስትን ወዘተ. የመሳሰለ የሠዎችን መሰረታዊ ባህሪያት በህይወት ውስጥ የሚያስከትለትን ጥሩና መጥፎ ለውጦችን ያሳያሉ (በድሉ 1996)፡፡ በአንጻሩ ሆን ተብሎ ለማስተማሪያ የሚዘጋጁ ምንባቦች ትኩረት የሚያደርጉት ለቃላት መረጣና ለአረፍተ ነገር ግንባታ ስለሆነ ምንባቦቹ ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር አይነተኛ ምክንያት ናቸዉ፡፡

የአጭር ልቦለድ ስራዎች ግን የሚያንጸባርቁት ህይወትን በቋንቋ በመግለጽ መሆኑ ሆን ተብሎና ለማስተማሪያነት ከተዘጋጁ ምንባቦች ይለያል በማለት ያስረዳሉ (Khatib and Nasrollahi 2012) ፡፡ ከተሰጠው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለዉ አጭር ልቦለዶ የሚያነሳው የሰውን ጉዳይ ነው፡፡ ሰዋዊ በመሆኑም በየትም ዘመንና ቦታ የተገለጸና የተወሳ ጉዳይ ከዛሬው ዘመን ጋር የሚያስተሳስረው ባህሪ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ባህሪም አጭር ልቦለድ እውነተኛ አውድን መሠረት ያደረገ በመሆኑ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ምቹ መደላድልን ይፈጥራል ፡፡ ከዚህ በመነሳት አጭር ልቦለድ ለማስተማሪያነት ሲውል ከቦታና ከዘመን አንጻር የቃላት አጠቃቀምን ከተጨባጩ አውድ ጋር በማዛመድ ማቅረብ እንደሚያስችል እንገነዘባለን፡፡

### 2.1.2.1 አጭር ልቦለድ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ መሆኑ፣

አጭር ልቦለድ የተለያዩ ነገሮችን ጠቋሚና አስተላላፊ መሳሪያ ነው፡፡ ይህውም የሰዎችን ልማድ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ይተላለፌበታል፡፡ እነዚህ ደግሞ የባህል መገለጫዎች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ በልቦለድ አማካኝነት በእውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ባህሉን ወግን፣ልማድን፣የአኗኗር ዘይቤዉን ይገልጻል፡፡ ከቀረበው ገለጻ መረዳት የሚቻለው የህዝቦች ባህል በአጭር ልቦለድ ይገለጣል፣ የተለያዬ ባህልን ለመግለጥ ሰዎች አጫጭር ታሪኮችን፤ ልቦለዶችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ የህዝቦች ባህል የተንጸባረቀባቸው አጫጭር የልቦለድ ስራዎች ለማስተማሪያነት በሚቀርቡበት ጊዜ ተማሪዎች ባህልን፣ወግን፣ልማድን እዲያዉቁ ያደርጋቸዋል፤ ግንዛቢያቸው ይሰፋል፡፡ በዚህ ሂደት የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችና የሀሳብ አገላለጾችን፣ ትርጓሜ አሰጣጥን እንዲረዱ ሰፊ መሰረትና አውድን እንደሚፈጥርላቸዉ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ሌላዉ ባህል በህዝቦች መካካል እውቂያን ማሳደጊያና የሰውን ስሜት የሚገዛና አነሳሽነው፡፡ ባህል ለቋንቋ ትምህርት ሲቀርብ ተማሪዎች የሚያዳብሩት ክሂልን ፣ መተርጎም ተዛምድዋቸውንና ግንኙነታቸውን በመመርመር ለመገንዘብ ያስችላቸዋል:: አንዱ ከሌላው ጋር መስተጋብር እንዲፈጠርም ያደርጋል በማለት Hernandez (2011) Turker et al (1991)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ እንዲተገበር ባህል ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል በማለት አስረድተዋል፡፡
ከማብራሪያው መረዳት የሚቻለው ባህላዊ ገጽታን የሚያንጸባርቁ የስነ-ጽሁፍ ስራዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ተማሪዎች ባህልን ከሚማሩት ትምህርት ጋር እያገናዘቡ ተዛምድኣቸውን የመመርመር የሚተላለፈውን መዕልክትም የመረዳት አቅማቸውም እየበረታ ይሄዳል፡፡ ሌላው አጭር ልቦለድን ለቋንቋ ማስተማሪያነት የመጠቀማችን ምክንያት የስነ-ጽሁፍ ዘር የሆነዉ አጭር ልቦለድ የባህል መገለጫ መሆኑ ነው፡፡ አጭር ልቦለድ የአንድ ማህበረሰብ ማህበራዊ፤ ፖለቲካዊ እና ታርካዊ ሁነቶች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይንጸባረቁበታል፡፡ልቦለዶች፣ አጫጭር ታሪኮች፣ የህብረተሰብን ባህል፣ወግ፣ልማድ፣የአኗኗር ዘይቤ በተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ፡፡ ተማሪዎች አጫጭር የልቦለድ ሥራዎችን በሚያነቡበት ጊዜ አውዳዊ እውቂያን ይፈጥርላቸዋል፤ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችንም ያስታውሳሉ በማለት ያስገነዝበናል (Lazar 1993) ፡፡
በተመሳሳይ መልክ ዘሪሁን ( 2007) አጭር ልቦለድ ከህብረተሰቡ ባህል ጋር ያለውን ትስስር ሲገልጽ፤ የህብረተሰብ ባህላዊ እሴት ምንነቱን ይገልጽበታል፡፡ የተናጋሪው አስተሳሰብ አለባበስና አመጋገብ፤ ጀግንነትና ድፍረት፤ ደስታና ሀዘን ምኞት ፍላጎቱን ያሳያል በማለት ያስረዱናል ፡፡ በተጨማሪም አጭር ልቦለድ በአንድ ዘመን ይኖሩ የነበሩ ሰዎች እንዴት ይኖሩ እንደነበረ፣ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስል እንደነበር ያሳያል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከ ዘሪሁን (2007) ገለጻ መገንዘብ እንደሚቻለዉ፣ ባህል በቋንቋ ሲገለጥ አንባቢ ከዘመኑ እና ከእሱ አድማስ ውጪ የነበሩና ሊኖሩ የሚችሉ ሁነቶችን በቋንቋ አማካኝነት ይረዳሉ ፡፡ ባህልን ለማወቅና ለመረዳት በሚያደርገው ንባብ የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቅሞችን፣ ገለጻዎችን፣ ይገነዘባሉ፡፡ የንባብ ክሂልንም ያዳብራሉ፡፡

በዚህ ንዑስ-ርዕስ አጭር ልቦለድ በባህልና በቋንቋ አጠቃቀም የበለፀገ ስለመሆኑ፣ ከዚህ ገጽታው በመነሳት ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ፋይዳ በተመለከተ የተሰጡ ማብራሪያዎችን በአጭሩ ተመልክተናል፡፡ በመቀጠል አጭር ልቦለድ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሊፈጥር የሚችለውን፣ የተነሳሽነትና የአሳታፊነት ሚና ተብራርቷል፡፡

## 2.1.2.2 አጭር ልቦለድ መነሳሳትንና ተሳትፎን የሚያሳደግ መሆኑ፣

በቋንቋ ትምህርት ክፍል ጊዜ ውስጥ አጫጭር ልቦለዶችን ከምንጠቀምባቸው ምክንያቶች ሳቢነቱ፣ ማራኪነቱ፣ አነሳሽነቱ ነዉ፡፡ ተማሪዎች ለአጫጭር ታረኮች እዉቀት ቅርብ ሲሆኑ ትምህርቱ በጽሁፍ ይዘቶች አማካይነት ሲቀርብ ከራሳቸው ህይወትና ልምድ ጋር በማመዛዘን የበለጠ ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎች ልቦለድን ሲያነቡ ከአዳዲስ ጭብጦችና አገላለጾች ጋር እዲተዋወቁ እዲላመዱ ያደርጋቸዋል ፡፡ በታሪኩም በመመስጥ በተነሳሽነት ስሜት እንዲያነቡ ያስችላቸዋል በለማት ያስረዳሉ (Lazar 1993)፡፡

እዚህ ላይ ለመግጽ የተፈለገው ጉዳይ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር በተማሪዎች ላይ እንዴት መነሳሳትን ሊፈጥር ይችላል የሚለው ነው፡፡ በአጫጭር ልቦለድ ስራዎች እውነተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ስለሚንፀባረቅባቸው ተማሪዎች ከህይወት ገጠመኞቻቸው ጋር በማስተሳሰር ማብራሪያ ይሰጣሉ፣ ማለትም ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች አጫጭር ልቦለድችን፣ ትረካዎችን ሲያነቡ ከአዳዲስ ጭብጦችና አገላለጾችን ሊያገኙ ስለሚችሉ፣ በተነሳሽነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልምዳቸዉ ይዳብራል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 2.1.3 አጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ያለዉ ሚና፣

አጭር ልቦለድ እንደሌሎች የስነ-ጽሁፍ አሃዶች ባህላዊ እዉቀትን ፣ተነሳሽነትንና የቋንቋ እውቀት በማስገኘት የቋንቋ ትምህርቱን የበለጠ ያሳድጋል በለማት Khatib and Nasrollahi (2012) Murdoch (2002)ን መሠረት በማድረግ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Krashen (1982) በሆንግ ኮንግ ባደረጉት የዳሰሳ ጥናት መሠረት የስነ-ጽሁፍ አሃዶቹን ያነበቡ ተማሪዎች ቃላትን የማንበብ ችሎታቸው እንደሚዳብር ይገልጻሉ፡፡ እንዱሁም Erkaya (2005)ን ዋቢ በማድረግ ተማሪዎች የስነ-ጽሁፍ ጽሁፎችን (ቴክስቶችን) ሲያነቡ የሚያገኙትን ጠቀሜታ ሲያብራሩ፣ ተማሪዎች የስነ-ጽሁፍ ጹሁፎችን (ቴክስቶችን) ሲያነቡ ጥልቅ አሳቢ ፣ ተንታኝ ፣ ተመራማሪ፣

ፈጠሪና አመዛዛኝ፣አገናዛቢ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ማለትም አጭር ልቦለድ አንባቢዎች ጥልቅ አሳቢነትን፣ተመራማሪነትን ያሰርጻሉ፤ይህ ሁኔታም ለአእምሮአቸው ደስታን ስለሚፈጥርላቸው፣ በንባባቸው እንዲቀጥሉበት ፣እዲገፉበት መንገድ ይከፍትላቸዋል፡፡

Krashen (1982) ዳሰሳ ጥናት የምንረዳዉ ነገር አጭር ልቦለድ በቋንቋ ትምህርት ከአንብቦ መረዳት ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳላቸዉ መረዳት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ባነበቡት ነገር ላይ ተንተርሰው ከቃላት ዕውቀትና ባህላዊ ተረካው በመነሳት መልዕክትን አንጥሮ የመለየት የመጠየቅና የመመርመር ተግባርን ሲሰሩ፣ነገሮችን ከቀድሞ እውቀታቸው ጋር ሲያመዛዝኑና ሲያገናዝቡ በታሪኩ በመሳብ ቀጣዩን ለማወቅ ወደፊት በመጓዝ ሲያነቡ፣ የአንብቦ መረዳት አቅማቸው በዚያው ልክ እንደሚድያግ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ላይ አንብቦ መረዳት ከላዕላይ መልዕክት እስከ ውስጣዊ ጥልቅ ምርምር ድረስ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ከችግሩ መነሻ ላይ እንደተጠቆመው የዚህ ጥናት አቅራቢ ትኩረት ያደረገችበት አከባቢ ባለዉ ትምህርት-ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ዋነኛ ችግራቸው አንብቦ መረዳት ነዉ ፡፡ የአንብቦ መረዳት ችግር ካለ ደግሞ ሌሎች ክሂሎችን ለመገንዘብ ወይም ለማዳበር የበለጠ ተጽኖ ይፈጥራል፡፡በዚህ ስራ ላይ Khatib and Nasrollahi (2012) Arigol (2001) የጠቀሰውን Hismanoglu (2005) መሠረት በማድረግ አጭር ልቦለድ ለተማሪዎች የሚሰጠውን ጠቀሜታ ጠቅለል አድርገው አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም አጭር ልቦለድ የተማሪዎችን የንባብ ተግባር ያዳበራል፡፡ ተማሪዎች፣ በጣም ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ፣ እንዲወያዩ ያደርጋል፡፡

ውይይት ሲያደርጉም በጽሁፍ ያገኙትን መልዕክት ከራሳቸው ዳራ ጋር በማገናዘብ ለመረዳት ይጥራሉ፤ በማስከተልም ሀሳቡን ከውጭው ዓለም ወይም ሁኔታ ጋር በማስተሳሰር ግንዛቤያቸውን እንዲያሰፉ መሰረት ይሆናል በማለት ያስገነዝባሉ፡፡

ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለው አጭር ልቦለድ ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘሮች የሚለይባቸው ባህሪያት ተደናቂነት የዘመኑ ሁኔታ መግለጽ መቻልና የተለያዩ አይነት አማራጮች ያለው መሆኑ፣ ተገልጿል፡፡ ተማሪዎች በንቁ መንፈስ እንዲያነቡ ያስችላል፡፡ እንዲሁም ከራሳቸው የህይወት ዳራና አጠቃላይ ስለ ህይወት የሚሰጡትን መልዕክት በማስተሳሰር ትርጉም ለመስጠት ጥረት ያደርጋል፡፡ በማስከተልም ሰፉ ውይይት ለማደረግ እንደሚያስችል እንገነዘባለን፡፡

ለዉጤታማ አንብቦ መረዳት ችሎታ ዳራዊ እውቀት መኖር ማለትም የይዘት እውቀት ከፍተኛ ድርሻ እንዳለው ያስረዳል Ghasemi (2011) ስለሆነም በንባብ ጊዜ ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን መሰረት አድርገው ለአነበቡት ነገር ትርጓሜ በመስጠት መረዳት ያስችልቸዋል፡፡ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማጎልበት አጫጭር ልቦለዶች የተለያየ ሚና እንዳላቸው አስቀድሞ ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡ በተጨማሪ መግለጽ የሚቻለዉ አጫጭር ልቦለዶች በአንብቦ መረዳት ተጽኖ ፈጣሪ አሃዶች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ተማሪዎች አጫጭር ልቦለዶችን እያነበቡ በቀጥታ ባላዕላይ ፍቺ የተላለፈውን መልዕክት ይገነዘባሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ የመረዳት አቅማቸው እየጠለቀ ሲሄድ ፊት ለፊት ያልተገለጡ ነገሮችን፤ መልዕክትን መረዳት የሚችለበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ሁኔታ ተማሪዎች ከጽሁፍ የተለያዩ መልዕክተቶችን ለማግኘት ሲሉ ጽሐፍችን በከፍተኛ ተነሳሽነት እንዲያነቡ ያስችላቸዋል፡፡

አንብቦ የመረዳት ችሎታና የመጻፍ ችሎታ ስነ-ልሳናዊ ግዛቤ ብቻ አይደለም፡፡ የጽሁፍን መልዕክት መረዳትን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ የይዘት ዕውቀት የቀረበውን ጽሐፍ አንብቦ ለመረዳት አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ Ghasemi (2011) Hammadouን በመጥቀስ ይገልጻል፡፡ በገለጻውም ለማስረዳት እንደሞከረው ዳራዊ እውቀት አንብቦ ለመረዳት ወሳኝ ነገር ነው፡፡ አንብቦ ለመረዳት ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ቢኖር የይዘት እውቀት ነው፡፡ አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የሚያስችልና የሚመቹ ደግሞ የስነ-ጽሁፋዊ ስራዎች ናቸው፡፡ በተለይም ደግሞ ልቦለድ መጠቀም የተማሪዎችን የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ለማሻሻል ያስችላል በማለት ያስገነዝባሉ

አጫጭር ልቦለዶች (ትረካዎች) እምቅ የሆኑ የስነ-ጽሁፍ አሃዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በግልጽ ያለንና ድብቅ ሆኖ የመጣን መልዕክት ለመረዳት በተነሳሽነት ያነባሉ፡፡ የሚነበበው ነገር የስነ- ጽሁፍ አሃድ ካልሆነ ግን ተማሪዎች የሚገነዘቡት ላዕላይ መልዕክትን ነው፡፡ የሥነ-ጽሁፍ አሃድ ያልሆኑ ጽሁፍች መልዕክትን በእምቅነት የማስተላለፍ አቅማቸው አነስተኛ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ አጫጭር ልቦለዶች ተነባቢ እንዲሆኑ ያስቻላቸው የሚለዩበት ባህሪያት ስላላቸው ነው፡፡ እነዚህም አጫጭር ልቦለዶች (ትረካዎች) ዓለምአቀፋዊ ባህሪ አላቸው፤ የሚያስተላልፉት መልዕክት የተስፋፋና ከተጠቀሱበት ቦታ፤ጊዜና ሁኔታ በአለፈ በሌላው ዘንድም ትርጓሜ መስጠት የሚቻልበት ደረጃ እንዳለ መረዳት ይቻላል፡፡ አጫጭር

ልቦለዶች(ትረካዎች) የተለያዩ እና ሳቢ ናቸው:: የተለያዩ የቋንቋ አጠቃቀሞችን የያዙና ለማንበብ ሳቢነት ያላቸዉ መሆኑን ይገልጻሉ (Ghasemi 2011) ፡፡ በተጨማሪም የእውነተኛ የሀሳብ ልውውጥን መፍጠር የሚያስችል፣ አንባቢ እራሱን ከጽሁፉ ታሪክ ጋር በማስተሳሰርና ከራሱ ዳራ በማገናኘት መልዕክትን ለመረዳት የሚጥርበት እንጂ ፍዝ አንባቢ አያደርገውም በማለት ያስረዳሉ (Ghasemi 2011) ፡፡

ከላይ የጠቀስዉን ሀሳብ የሚያጠናክርልን፣ ብቁ የሆኑ አንባቢዎች የጽሁፉን መልዕክት ለመገንዘብ ሁለት ሂደቶችን መከተል እንደሚችል (Ghasemi (2011)፣ Knutson (19993)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ አንደኛው መንገደ ታች ላይ ሂደት (bottom up process) ነው፡፡ ታች ላይ አንብቦ የመረዳት ሂደት አንባቢ እያንዳንዱ የጽሁፉን አካል በማገናኘት አጠቃላይ ትርጉምን ለመረዳት የሚቻልበት ስሌት ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ላይ ታች (up bottom process) አንብቦ የመረዳት ሂደት ነው፡፡በላይ ታች አንብቦ የመረዳት ሂደት አንባቢ ስለሚያነበው ጽሁፍ መላምት በመምታትና አስቀድሞ በመተንበይ ከዚያም ወደ ንባብ በመግባት ትርጉምን ለመረዳት ጥረት የሚያደርግበት ሂደት ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ስሌቶች በተመሳሳይ ጊዜ በመጠቀም የተሳካ ንባብ ማካሄድ ይቻላል፡፡ በእነዚህ ስሌቶች አንብቦ መረዳትን ለማሻሻል አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ስነ-ጽሁፍ ካልሆኑ ጽሁፎች የበለጠ ተስማሚ ናቸው፡፡ ቅድመ-ንባብ ተግባራትን በአጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ላይ መተግባር ይቻላል፡፡ እንዲሁም አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) ከርዕሳቸዉ ተነስቶ ለመተንበይ፣ ለመተንተን ተራኪ መዋቅር መኖሩ የላይ-ታች አንባቦ የመረዳት ሂደትን ያፋጥናል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በተከታታይ ከቀረቡት ገለጻዎች መረዳት እንደሚቻለዉ፣በመጀመሪያ ደረጃ አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች) የተለያዩ ሰዋዊ ጉዳዮችን የያዙና ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸዉን ግንዛቢዎች የሚያስገኙ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሳቢና ባጭር ጊዜ ውስጥ ሊነበቡ መቻላቸው፣ የሃሳብ ልውውጥን ስለሚከስቱ አንባቢ በንቃት እንዲወያይ፣ ሃሳብ እዲሰነዝር፣ እንዲከራከር ያስችላል፡፡ አጫጭር ልቦለዶች(ትረካዎች)በቂ ስነ-ልሳናዊ ቅርጽና የተለያዩ አገላለጾች ያካተቱ መሆናቸው፣ አስደናቂ እና ከዘመኑ ጋር የሚሄድ የተለያዩ ዓይነቶች መሆናቸው ሰዎችን ሙሉ ተሳተፉ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አንባቢ ፊት-ለፊት ከተገለጸው መልዕክት ስር ነጥረው ሊወጡ የሚችሉ ትርጉሞችንም መገንዘብ ያስችላል፡፡ አንባቢ ከራሱ ዳራዊ

እውቀትና ከዘመኑ ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰር የራሱን ትርጓሜ ለመስጠት እንደሚያስችሉት መረዳት እንችላለን፡፡

### 2.1.4 የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ሲባል በጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የተፈለገዉን መልእክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነዉ፡፡ በሌላ አባባል የሚፈለገዉን መረጃ ከአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ለይቶ ወይም አንጥሮ ማዉጣትን የሚጠይቅ ነዉ፡፡ አንባቢዉ በፍጥነት የሚፈልገዉን መረጃ የሚወስድበት የማይጠቅመዉን አንጓሎየሚያወጣበት ልዩ የመረዳት ዘዴ ነዉ William (1984) በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንደ Graham (1990) ገለጻ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ከሚነበበዉ ነገር፣ከሚነበብበት ዓላማ ከአንባቢዉ ዘዴ ሊለያይ ይችላል፡፡ ነገር ግን በአንድ ጽሁፍ ዉስጥ ሊተላለፍ የፈለገዉን መልእክት መገንዘብ ነዉ፡፡( Smith et al )እንደሚሉት ደግሞ አንብቦ መረዳት አንባቢዉ ይዞት ለሚነሳዉ ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነዉ፡፡ አንባቢ ለጠየቀዉ ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢዉና በጸሀፊው መካከል በአንብቦ መረዳት ተግባቦት መኖሩን ያሳያል፡፡ ከአንድ ምንባብ ዉስጥ የሚፈለገዉን መረጃ ለይቶ ማዉጣት መቻል አንብቦ መረዳት ማለት ነዉ ፡፡

እንደ Grellet (1981) አገላለጽ አንብቦ መረዳትን በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡ አንደኛዉ በምንባብ ዉስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዩችን መገንዘብ ነዉ፡፡ በስሩም በጽሁፍ ዉስጥ የቀረቡትን ዋናዋና ሃሳቦች መገንዘብ፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ ቅደምተከተል ማስታወስ ግልጽ የሆኑ አንድነቶችንና ልዩነቶችን መለየት፣ የምክንያትና ውጤት መሰናክልን ማስታወስ ነዉ፡፡ ሁለተኛዉ ደግሞ ተማሪዎች ጠያቃዊ እዉቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሁፍ ዉስጥ በግልጽ ያልሰፈሩ ሃሳቦችን አንብበዉ የሚረዱበትን ሁኔታ ያመላክታል፡፡ ከመረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ጭብጥ መለየት፣ ደጋፊ ጽሁፎችን ለይቶ ማወቅ፣ ከምክንያትና ዉጤት ጥብቅ ትስስር የተነሳ ቀጣዩን ነገር መገመት፣ በምንባቡ ዉስጥ በይፋ የሰፈረን ፍንጭ በመጠቀም የገጸባህርያትን ባህሪና የደራሲዉን የቋንቋ አጠቃቀም መረዳትን ይይዛል፡፡ ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መረዳት እንደሚቻለዉ አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሁፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ከመገንዘብ ባሻገር ጠቃሚ መረጃዎችን ለይቶ ለማዉጣት የሚያስችለንን ሁኔታ ያጠቃልላል፡፡እንግዲህ የሰዉ ልጅ እለት በዕለት ከምናደርገው የመማር ማስተማር ተግባር እንደምንገነዘበው ማንበብ መሰረታዊ ተግባር ነው፡፡ የተለያዩ ተግባራት ከንባብ እና አንብቦ መረዳት ጋር

የተያያዙ ናቸው፡፡ አንብቦ መረዳትን አስመልክቶ Agency (2002) እደሚከተለው አብራርቷል፡፡ ማንበብ ለማንኛውም ትምህርታዊ ተግባር መሰረትነው፣ የትምህርት ማዕከላዊ አካል ነው ማለት ይችላል፡፡ በትምህርት-ቤት በስራ ቦታ በአጠቃላይ በህይወት ውስጥ ዛሬም ሆነ ለወደፊት ህይወት ማንበብ ወሳኝ ነገር እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ በቴክሳስ ከ1996 ተጀምሮ የነበረውን የማንበብ ንቅናቄ መነሻ ሲጠቁም፣ በወቅቱ በአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ጆርጅ ደብሊው ቡሽ ‹‹ ማንኛውም ህፃን ማንበብን መማር አለበት›› የሚል አላማ አስቀምጠው እንደነበር ይገለፃል፡፡ ከዚህም በወቅቱ ለ አንብቦ መረዳት ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን መረዳት ይቻላል፡፡ አንብቦ መረዳት በማንኛውም የትምህርት ዘርፍ ውጤታማ ሆኖ ለመቀጠል መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን፣ በህይወት ውስጥ የተለያዩ መረጃዎችን በስፋትና በጥልቀት መገንዘብ፣ የተለያዩ ምርምሮችን ለማካሄድና የኑሮን አቅጣጫ መላምት አንብቦ መረዳት አብይ ትምህርታዊ ተግባር መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ከቴክሳሱ ትምህርታዊ ኤጆንሲ ዓላማ መገንዘብ የሚቻለው አንብቦ መረዳት ከትምህርት አጀማመር ጀምሮ ተማሪዎች እያደጉ በሚሄደባቸው የትምህርት እርከኖች ሁለ ወሳኝ ትምህርታዊ ተግባር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አንብቦ መረዳት አለመሻሻል ችግር በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ጎልቶ ሰለሚስተዋል በመጀመሪያ አንብቦ መረዳትን ምንነትና ስሌቶችን ማወቅና መተግበር መቻልን ይጠይቃል፡፡ በሁለተኛ ደ ረጃ አንብቦ መረዳትን ሊያሻሽለ የሚችሉ የማስተማሪያ ይዘቶችም እንድንመርጥም መንገደን ሊያመቻች ይችላሉ፡፡የቴክሳሱ ትምህርታዊ Agency (2002) በ1970ዎቹ የተጠና ጥናት ዋቢ በማድረግ እንደገለጸው፣ አንብቦ መረዳት ማለት አንድን የተሰጠ መመሪያ ወይም ቅደም ተከተል ጠብቆ የተሰጠ ተግባርን ሞልቶ መጨረስ ማለት እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የስነ-ልቦና የጥናት ቡድን፣ ስነ-ልሳን፣ የኮምፒዩተር ሳይንስ ተመራማሪዎች ትኩረት ያደረጉት አእምሮ እንዴት እንደሚሰራ፣ ሰዎች እንዴት እንደሚያስቡና እንደሚማሩ ይገልፃል፡፡ የስነ-አእምሮ ሳይንስ ትኩረት የሚያደርገው፣ አንባቢ ከሚያነበው ነገር ተነስቶ እንዴት ትርጉም መገንባት እሚንደቻል፣ የጥሩ አንባቢ አእምሮአዊ ተግባር ምን ምን እንደሆነ ገልጿል፡፡ እንደ አንብቦ መረዳት አዲስ ጽንስ ሀሳብ አንብቦ መረዳት ውስብስብና የሚከተለትን ትርጉም የመገንባት ተግባራት እንደሚያካትት እንዲህ ገልጿል፡፡

- አንባቢ ለሚያነበው ነገር ዓላማ ሊኖረው ይገባል፡፡
- ከሚያነበው ነገር ላይ ትርጉም ለማራጀት የተለያዩ የታቀዱ ስሌቶችን ሊጠቀም ይችላሉ፣
- አንባቢዉ ከጹሁፉና ከአዉዱ ጋር የመሄድና የመመርመር መፈጸም::

አንባቢ በአንድ ተግባር ላይ የተጠቀመበትን አንብቦ የመረዳት ስሌት በሌላ በተለየ ምንባብ ላይ ሊተገብረው ይችላል፡፡የቴክሳሱ ትምህርታዊ Agency (2002) ስለ ጥሩ አንባቢነት እንደገለፀው ጥሩ አንባቢዎች ቃላትን በትክክልና በፈጥነት ያነባሉ:: የቃላትንና የሀረጋትን ትርጉም ይረዳሉ፡፡ የአንደን ዓረፍተ-ነገር ትርጉም ከሌሎች ዓረፍተ-ነገሮች መልዕክት ጋር በማስተሳሰር መልዕክትን ይገነዘባሉ፡፡ ዳራዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው የጽሁፉን መልዕክት ያብራራሉ፡፡ እራሳቸውን ከጽሁፉ ጋር በማዋሃድ፤ ጥያቄ በመጠየቅ፣የወደፊቱን በመተንበይ፣ ስለ ጽሁፉ ሀሳብ በመሰንዘር መስተጋብር በመፍጠር ያለማቋረጥ ጽሁፈን ይመረምራሉ፡፡ ጥሩ ንባቦችን ከራሳቸዉ ዓላማ ጋር የተሳሰረውን መርጠው ያነባሉ፡፡ ብዙ ጊዜ በምንባቡ ላይ ተጨማሪ ትርጉም ይሰጣሉ፤ምዕናባዊ ምስሌ ይፈጥራሉ::የማንበብ ስሌቶችን ይጠቀማሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

በአንጻሩ ጥሩ ያልሆኑ አንባቢዎች ለንባባቸው ስሌት የላቸውም ፤ የአእምርአዊ ተግባር እውቂያና ስለሚያነቡት ነገር የተደራጀ ግብ የላቸውም፡፡ ባልቀለጠፈ ፍጥነት ያነባለ በዚህ የተነሳ ሀሳብን የመያዝና የመገንዘብ ችግር ይፈጠርባቸዋል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ማንበብ የተማሪዎችን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ለትምህርቱ አጋዥ ከሆኑ ከተለያዩ መጣጥፎች ጋር እንዲተዋወቁ በማድረግ በኩል ማንበብ ትልቅ ሚና ስላለው ነው፡፡ Hyland (1990) እና Poorahmadi (2012) እንደሚያስረዱት የማንበብ ክሒል ከሌሎች ችሎታዎች ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፡፡ በእርግጥ በትምህርት አለም የሚኖሩ ሰዎች በየጊዜው ከሚነበቡ ነገሮች ጋር ይገናኛሉ፡፡ ይሁን እንጅ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን መረጃ ሊገኝባቸው ከሚችሉ የተለያዩ ፅሁፎች ሀሳብ የሚወሰድበት መንገድ የሚፈለገውን እውቀት ለመገብየት ያስችላቸዋል ብሎ ለመናገር ያዳግታል፡፡

ባጠቃላይ በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ስር በመጀመሪያ ደ ረጃ ተደርጓል፡፡ በማስከተልም አጫጭር ልቦለዶችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የመጠቀም አስፈላጊነትን አጉልተው የሚያሳዩ ስራዎችን በመጥቀስ ለማብራራት ተሞክሩዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር አጭር

ልቦለደ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መጠቀም ያለውን ጠቀሜታና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን ተያያዥነት ያነሱ ጥናቶችን ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

ከዚህ በመነሳት ከዚህ ጥናት ጋር በተቀራረበ ሁኔታ የተሰሩ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡

## 2.2. ተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዛ ከተነሳችው የጥናት ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ሊዛመዱ የሚችሉ ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡ ቅኝቱ መሰረት ያደረገባቸው ነጥቦችም ከጥናቱ ርዕስ ፣ የጥናት አካላዮች ፣የጥናት ዘዴ፣ ከመረጃ መሰብሰቢያዎች አንጻር አንድነትና ልዩነትታቸውን በመዳሰስ ያለውን ክፍተት መሙላት ላይ ነው፡፡

በኢትዮጵያ የተጠኑ ጥናቶችን ስንፈትሽ፣አንብቦ መረዳትን በተመለከተ የተሰራጥናት የመንግስቱ (2008) ጥናቱ ዋና ትኩረት ያደረገዉ አማረኛ ሁለተኛ ቋንቋቸዉ ለሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለዉን ሚና መፈተሽ ሲሆን የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር ላይ ያለው ሚና መ ፈ ተ ሽ የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የሁለቱ ጥናቶች አቀራረብ ላይ ልዩነት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል፡፡የአጠናን ዘዴን በዋናነት መጠናዊን አይነታዊ የአጠናን ዘዴን ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ መጠናዊ ዘዴ የተከተለ ነው፣በሙከራ ላይ የተመሰረተ ፈተናን ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርገው የሚጠቀሙ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡ ዉጤቱም በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ መሻሻል እንዳለዉ አሳይቷል፡፡

በሪሃና (2007) "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸው አሃዶች መምረጫ መስፈርት ፍተሻ በድሬደዋ መሰተዳድር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት-ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ዋቢነት" በሚል ርዕስ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፣ የጥናቱ ዋና ትኩረቱ መምህራን ወደ ክፍል የሚወስዱዋቸውን ተጨማሪ የስነ-ጽሁፍ አሃዶች ምን ዓይነቶች እንደሆኑና አሀዶችን የሚመርጡባቸው መስፈርቶችን መፈተሽ ነው፡፡ አጥኚዋ በዋናነት የተጠቀሙት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ምልከታና የጽሐፍ መጠይቅ ናቸው፡፡

የጥናቱ ውጤት እንደሚያመላክተውም መምህራን በብዛት ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመርጡዋቸዉ የልቦለድ ድርስቶችን ሲሆን፣ መምህራን የስነ-ጽሁፍ አሃዶችን ሲመርጡ

ከተማሪዎች ሁኔታና ከመምረጫ መስፈርቶች አንፃር ሳይሆን ብዙውን ጊዜ በራሳቸው ልምድ በመመራት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር መምህራን የስነ-ጹሁፍ አሃድችን የማግኘት ችግር እንደሚያጋጥማቸውና በስነ-ጹሁፍ ቋንቋ ማስተማር በሚለው ጽንስ ሀሳብ ዙሪያም የግንዛቤ ችግር እንዳለባቸዉ አጥኛዋ አመላክተዋል፡፡

በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ ከስነ-ጽሑፍ ዘሮች አንዱ የሆነዉን አጭር ልቦለድን ለማስተማሪያነት ከአንብቦ መረዳት ጋር ያለውን ሚናና ተያያዥነት ለማጥናት መነሳሳትን ፈጥሮባታል፡፡

በቀጣይነት መሰረት (2007) በአንከሻ ወረዳ በሚገኙ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሂል የትምህርት አቀራረብ ቅኝት››በሚል ርዕስ ለድህረ ምረቃ የቀረበ ጥናት እናገኛለን፡፡ በመሰረታዊነት መምህራን ለማንበብ ክሂል የሚሰጡት ትኩረት ምን ያህል ነው? አቀራረባቸውስ ምን ይመስላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የተሰራ ነው፡፡ በዋናነት ጥቅም ላይ የዋሉት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ለመምህራን የቀረቡ የጽሁፍ መጠይቆችና ምልከታ ሲሆኑ የጥናቱ ውጤትም መምህራን ለማንበብ ክሂል ዝቅተኛ ትኩረት መስጠትና ለዚህም ሌሎች ተጽዕኖ አድራሽ ጉዳዮች እንዳሉ ተገልጿል፡፡

ከተሰጠው ማብራሪያ እንደምንመለከተው፣የ መሰረት (2007)ጥናት ገላጭ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ መጠናዊ የአጠናን ዘዴን የተከተለች በመሆኑ ልዩነት ይታይባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የዚህ ጥናት አቅራቢ አጫጭር ልቦለዶችን እንደ ቋንቋ ማስተማሪያ በመጠቀም በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ማዳበር ላይ ሊያመጣ የሚችለውን ሚና የሚፈትሽ ነው፡፡ የ መሰረት (2007)ጥናት ደግሞ የንባብ ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርን የሚመለከትና የሚገልጽ መሆኑ የአካሄድና የዓላማ ልዩነት አለዉ፡፡ እንድሪስ (2000) ጥናት ዋና ትኩረት የእንብቦ መረዳት ስሌቶችን ማስተማር የአንብቦመረዳት ችሎታን ሊጨምር ይችላል የሚል መላምት ይዞ የተነሳ ሲሆን የዚህ ጥናት አቅራቢ ደግሞ አጫጭር ልቦለዶችን ተጠቅሞ ተማሪዎችን ማስተማር የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለው ሚና ማዳበር መፈተሽ የሚል ነው፡፡ ስለሆነም የሁለቱ ጥናቶች አቀራረብ ላይ ልዩነት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል፡፡ የአጠናን ዘዴያቸዉ በዋናነት መጠናዊ የአጠናን ስሌትን የተከተለ መሆኑ፣በሙከራ ላይ የተመሰረተና ፈተና ወሳኝ የመረጃ መሰብሰቢያ አድርገው የሚጠቀሙ መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡

እንድሪስ (2000) የጥናት ውጤትም የአንብቦ መረዳት ስሌቶችን የተማሩ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ስሌቶችን ካልተማሩት ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዳመጡ አሳይቷል፡፡

ዘመንፌስ (1991) በስነጽሁፍ አማካኝነት የአማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልብወለድ ሚና በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ትኩረት በአጭር ልብወለድ አማርኛ ቋንቋን ማስተማር አባይትና ንኡሳን ክሂሎችን ለማዳበር ያለውን አስተዋጾ መመርመር ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በቁጥጥርና የሙከራ ሁለት ቡድኖች ላይ ነው፡፡ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ቅድመፈተና ተሰጥቶ ልዩነት አልታየም፤ ነገር ግን በተለያዩ ዘዴዎች ትምህርት ተሰጥቷቸው ሲፈተኑ ልዩነት መታየቱ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም በአጭር ልብወለድ የተማሩት በተለመደው ዘዴ ከተማሩት ቡድኖች የተሻለ ውጤት እንዳስመዘገቡ የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ውጤቱም አጭር ልቦለድን በመጠቀም ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ እንደሚያደርግ ያመለከተ ነው፡፡ ፈጠራዊ ዘዴን ተጠቅሞ በአጭር ልቦለድ አማካኝነት ቋንቋን ማስተማር ክሂሎችን በማጎልበት ረገድ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች እራሳቸውን ችለው እንዲማሩና እርስ በእርስ የመተጋገዝ ባህል እንዲያዳብሩ ለማድረግ ይረዳል፡፡አጥኚዋ ይዛ ከተነሳችዉ ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚዛመደ የውጭ ጥናቶችንም ቃኝታለች ይኸውም Kitab (2013) በጋራ አጭር ልቦለድንና ስነጽሁፍን መሰረት በማድረግ ቋንቋን ማስተማር በሚለው ጥናታቸው ላይ የሌሎችን አጥኚዎች የጥናት ውጤቶችን Sage (1999)፣ Abidat(1997)፣ Kusetodina etal (1998)፣ና Moredoch (2002)ን ዋቢ በማድረግና በራሳቸው የጥናት ውጤትም አጭር ልብወለድም ይሁን ስነጽሁፍን መሰረት በማድረግ ቋንቋን ስናስተምር ተማሪዎች ጠያቂ እንዲሆኑ፣ ለነገሮች ትርጉም እንዲሰጡ፣ ሐሳቦችን እንዲያዋህዱ፣ ቋንቋውን መገንዘብ እንዲችሉ ብሎም ተመራማሪ እንዲሆኑ፣ አራቱን የቋንቋ ክህሎቶቻቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋሉ፡፡ በተለይ በእርሳቸው የጥናት ግኝት ስነጽሁፍን መሰረት በማድረግ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንደሚያጎለብት ገልጸዋል፡፡

Khatib and Nasrollahi (2012) “አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን በማስተማር፣የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማሻሻል”በሚል ርዕስ በኢራን የተጠና ጥናት እናገኛለን፡፡ ጥናቱ፣ ስነ-ጽሁፍ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ያለውን ጠቀሜታ በመግለጽ፣ በአጫጭር ልቦለዶች ቋንቋን ማስተማር ከአንብቦ መረትዳ መሻሻል ጋር ያለው ዝምድና በሚለዉ ጽንሰ-ሀሳብ ላይ በማተኮር ሙከራዊ ጥናት ያደረገ ነው፡፡

የጥናቱ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴም ቅድመ- ትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተና ነው፡፡ ፈተናውም ቋንቋ ለማስተማር ከተዘጋጁ የተለያዩ መጽሐፍት የተውጣጡ ምንባቦች የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ድምዳሜ መሰረትም በስነ-ጽሁፍ ይዘቶች በተማሩት ተማሪዎችና በተለመደው መንገድ በተማሩ ተማሪዎች መካከል የጎላ የአንብቦ መረዳት ልዩነት እንዳልታየ ተገልጿል፡፡ ጥናቱ በርግጥ የዚህ ጥናት አቅራቢ ይዛ የተነሳችው ርዕሰ ጉዳይ ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም በውጭ አገር የተጠና መሆኑ፣ የቦታና የጊዜ ርቀት ክፍተት እንዳለ ማስተዋል ይቻላል፡፡ እላይ ካየነው በተጨማሪ በውጭ የተጠና ጥናት እናገኛለን ፣ ይኸውም በYeasmin (2011) Ferdoush December (2011)"በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር ሂደት ተገቢ የክፍል ውስጥ ተግባቦትን ማደራጀት"በሚል ርዕስ የተጠና ጥናት ነው፡፡ ጥናቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች በቋንቋ ማስተማሪያነት ሲያገለግሉ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች እንዳላቸዉ ያስረዳሉ፡፡ ዘርዘር አድርገው ለማሳየት እንደሞከሩት፣ አጫጭር ትረካዎች እና አጫጭር ልቦለዶች የእውነተኛ ቋንቋ አጠቃቀም ገጽታ ያላቸው፣ሳቢና የዘመኑን ሁኔታ የሚገልጹ፣ስሜት የሚገዙና ፈጠራን የሚያበረታቱ፣መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች ስሜታቸውን በመግለጽ በቡድን ውይይት ይሳተፊሉ፤ ተነሳሽነታቸውና የትምህርት ፍላጎታቸው ያድርጋል፤፤ ከነበረባቸዉ ፍርሃትና ጭንቀት ይላቀቃሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ ጥናቱም በመደምድሚያዉ እንደተመለከተው ስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ደረጃ ባገናዘበ ሁኔታ መሆን እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

ጥናቱ ትኩረት ያደረገዉ ከስነ-ጽሁፍ ይዘት በተለይ አጭር ልቦለድ ለማስተማሪያነት ለቋንቋ ማስተማሪያነት እንዴት ይመረጣል? የክፍል ውስጥ አደረጃጀትና አተገባበር ምን ይመስላል? በሚለው ላይ ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የስነ-ጽሑፍ ዘሮች በተለይም አጫጭር ልቦለዶች ለቋንቋ ማአስተማሪያነት መጠቀም የተማሪዎችን ስሜት በማነሳሳት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል፡፡ በስሜት ተማርከው የተለያዩ ተግባራትን ስለሚፈጽሙ ከነበረባቸው ጭንቀትም እንደሚላቀቁ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን ጥናቱ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይብቻ በማተኮር አጫጭር ልቦለዶችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት በመጠቀም አንብቦ መረዳት ምንያህል ማሻሻል እንደሚቻል የሚፈትሽ አይደለም፡፡በአጠቃላይ በእነዚህ ዳሰሳዎች መሰረት የስነ-ጽሁፋዊ ይዘቶች አቀራረብና አተገባበር ትኩረት እንደተሰጠው ማየት ተችሏል፡፡ ሌላው ደግሞ የንባብ

ክሂልና አንብቦ መረዳት ላይ ሰፊ ዳሰሳ መደረጉን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው  በተማሪዎች ላይ አንብቦ የመረዳት ችግር አሁንም በተለያዩ አካባቢዎችና የክፍል ደረጃዎች ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት የዚህ ጥናት አቅራቢ በተማሪዎች ዘንድ የሚታየውን የ አንብቦ መረዳት አለመዳበር ችግር ለመፍታት አጫጭር  ልቦለዶችን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ላይ ያለዉን ሚና ይፈትሻል::

# ምዕራፍ ሦስት፤ የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን ሚና ፍተሻ ነዉ፡፡የጥናቱ ንድፉ ከፊል ሙከራዊ ሲሆን መጠናዊ የምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ በሁለት ቡድኖች ማለትም የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን በቅድመ-ትምህርት ፈተና ና በድህረ-ትምህርት ፈተና ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የሙከራና የቁጥጥሩ ቡድን በቅድመ-ትምህርት ተመሳሳይ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን በተመሳሳይ ጊዜ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ቅድመ-ትምህርት ፈተናው የሁለቱንም (የሙከራና የቁጥጥር) ቡድኖች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ተመጣጣኝነት ለማረጋገጥ ያገለገለ ሲሆን ድህረ-ትምህርት ፈተናው የቁጥጥር ቡድኑ በመማሪያ መጻፍ በተለመደዉ ማስተማሪያ ዘዴ የሙከራ ቡድኑ በተጽኖ ፈጣሪው ማለትም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ በማስተማር ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድንና በተለመደው የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የቁጥጥር ቡድን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማነጻጸር አገልግሏል፡፡

## 3.2 የናሙና አመራረጥ ስልት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ክፍል የትምህርት ቤት አመራረጥ፣የክፍል ደረጃ አመራረጥ፣የተማሪዎች አመራረጥ ሶስቱ ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡

### 3.2.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

የጥናቱ አካላይ በደቡብ ምዕራብ ክልል፣ በቤንች ሸኮ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ ከሚገኙ አምስት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል የቢፍቱ ሚሊንየም አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአመች ንሞና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት አጥኚዋ ያስተማረችበት ትምህርት ቤት እና ችግሩን በስፋት ያስተዋለችበት በመሆኑ እንዲሁም ሙከራዊ ጥናቱን በቅርበት በእየለቱ ለመከታተል፣ ለማስተማር፣ለመፈተን ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም አመች በመሆኑ አጥኚዋ ለጥናቱ አስፈላጊ ነዉ ብላ ያመነችበትን አመች ናሞና ዘዴ ተጠቅማለች፡፡

### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

የጥናቱ ተሳታፊዎች በ2015 ዓ.ም በቢፍቱ ሚሊንየም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይህ የክፍል ደረጃ ለጥናቱ በአለማ ተኮር የተመረጠበት ምክንያት የአንብቦ መረዳት ችግር በሁለም ክፍሎች ቢኖርም በብዛት በ9ኛ እና የ11ኛ ክፊሎች ላይ በርካታ ጥናቶች ተደርጓል ነገር ግን ከዚህ ቀደም በነበረዉ የትምህርት ስራዓት 10ኛ እና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የቤሔራዊ ፈተና ተፈታኞች በመሆናቸዉ ትኩረታቸውን ሁሉ ለሀገር አቀፍ ፈተናዎች ብቻ ይሰጣሉ ተብሎ ስለሚታሰብ በርካታ ጥናቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች እና የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ተሰርቷል፡፡ነገር ግን የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለመዳበር ችግር በሁለም የክፍል ደረጃ ይታያል  እንዲሁም፣ አጥኚዋ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ስታስተምር በሁሉም ክፍሎች የአንብቦ መረዳት ችግር ያስተዋለች ቢሆንም በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ግን ጎልቶ በመታየቱ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም የክፍል ደረጃው አላማ ተኮር ንሞና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ

የጥናቱ አካላዮች በ2015ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ አስረኛ ክፍል 128 ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ውስጥ ይማራሉ፡፡ እያንዳንዱ ክፍል 64 ተማሪዎች ይዟል፡፡ ሁሉንም ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከሰው ሐይል አንጻር አስቸጋሪ ስለሚሆን በጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ ቀላል የእጣ ማውጣት ንሞና ዘዴ በመጠቀም ከሁለቱም ክፍሎች 64 ተማሪዎች የጥናቱ ተሳታፊዎች ሆነው ተመርጠዋል፡፡ ተማሪዎችን የሙከራና የቁጥጥር ብሎ ለመለየት የቅድመ-ትምህርት ፈተናውን መጀመሪያ ላይ በመስጠት 32 ተማሪዎች የሙከራ ቡድን እና 32 ተማሪዎች የቁጥጥር ቡድን ሆነዉ ተለይተዋል፡፡የጥናቱ አካላይ ከሆኑ 128 ተማሪዎች ዉስጥ 64 ተማሪዎች በናሙናነት በመመረጣቸዉ ከጥናቱ አካላዮች አንጻር በፐርሰንት ሲሰላ 50% ናቸዉ፡፡በልምምድ ጊዜ አጥኚዋ ተጠኝ ተማሪዎችን ለመቆጣጠር እና ተገቢዉን ትምህርት ለመስጠት በናሙናነት 64 ተማሪዎች መመረጣቸዉ በቂ ነዉ ማለት ይቻላል፡፡

### 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት

የጥናቱ ዋና አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፣አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለዉ ሚና ማረጋገጥ ነው፡፡ይህንን አላማ ግምት ውስጥ በማስገባት የጥናቱን መረጃ ለመሰብሰብ በተግባር ላይ የዋለው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ፈተና ነው፡፡መረጃን ለመሰብሰብ ከሚረዱን በርካታ ዘዴዎች መካከል ፈተና ጉልህ ድርሻ ይዞ ይገኛል፡፡ ፈተና በተለያየ መልክ ተዘጋጅቶ በጥንቃቄ ተቀናጅቶ አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

ፈተና የተወሰኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ወጥነት ባለው መንገድ የተፈታኞችን አእምሯዊ ዕዉቀት አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መመዘኛ ነው፡፡ፈተናው ለጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሰጠው በተመሳሳይ ሁኔታ በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ፣በተመሳሳይ የአፈታተንና የአስተራረም መንገድ፣ ተመሳሳይ የመልስ አሰጣጥ ፣ መመሪያና ከተቻለም በተመሳሳይ ፈታኝ ወይም ተቀራራቢ የአፈታተን ብቃት ባላቸው ሰዎች የሚካሄድ መሆኑን ለማመልከት ነው (ያለዉ 2009)፡፡

በዚህ ጥናት የአንብቦ መረዳት ፈተና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆን የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ ፈተናውም በአጥኝዋ ተዘጋጅቶ በአማርኛ ቋንቋ መምህራንና በአጥኝዋ አማካሪ ተገምግሞና የማሻሻያ ሃሳብ ተደርጎበት እንደገና ተዘጋጅቷል፡፡ ለአንብቦ መረዳት ፈተና የተዘጋጀው አጭር ልቦለድ ምንባብ ሲመረጥ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የክፍል ደረጃውን፣ ስርዓተ ትምህርቱን እና የስነጹሑፍ መምረጫ መስፈርትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

ይህ ፈተና ቅድመ-ትምህርት ፈተና እና ድህረ-ትምህርት ፈተናን አካቶ የያዘ ነው፡፡ ቅድመ-ትምህርት ፈተናው ተማሪዎቹ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ ከመማራቸው በፊት የነበራቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ያገለገለ ሲሆን ድህረ- ትምህርት ፈተናው ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ከተማሩ በኋላ ያላቸውን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ተግባር ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ ከጥናቱ ንሞና ውጭ ከሆኑ ስልሳ አራት ተማሪዎች ውስጥ ቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ በመጠቀም አስራ ሁለት ተማሪዎች በመምረጥ የቅድመ-ትምህት የፓይለት ፈተና አስተማማኝነት በክሮቮንች አልፋ ልኬት (0.754) በመሆኑ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡እንዲሁም የድህረ-ትምህርት የፓይለት ፈተና አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ ከጥናቱ ንሞና ውጭ ከሆኑ ስልሳ አራት ተማሪዎች ውስጥ

ቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ በመጠቀም አስራ ሁለት ተማሪዎችን መርጠ በመፈተን አስተማማኝነቱ በክሮቮች አልፋ ሲለካ (0.766) በመሆን አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡

## 3.3.1 ቅድመ- ልምምድና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎች

የቅድመ-ልምምድም ሆነ የድህረ-ልምምድ ፈተናዎች ዋና ትኩረት የተጠኝ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማደበር ያለዉን ሚና ለመመዘን ነው፡፡
በዚህም መሰረት አጥኚዋ የአንብቦ መረዳት ፈተናዎችን ስታወጣ፣ እነ (Pettit et al, 1997)ን በመጥቀስ የአንብቦ መረዳት ሞዴሎች የሚያካትቱትን ማለትም የጻሐፊዉን መልዕክት መረዳትን፣ ጸሐፊዉ ትኩረት ያደረገበትን ትርጉም መረዳትን፣ የጽሐፉን ዓላማ መገንዘብን መሰረት አድርጎ እና የትምህርት ቤቱን ፈተና ሞዴል በማድረግ ነዉ፡፡ (Pettit et al 1997) እንደገለጹት:: አንብቦ መረዳትን ጠቅለል ባለ ሁኔታ በሁለት ክፍሎች ለማስቀመጥ ሞክራለች፡፡ እነዚህም የምንባቡን ገጻዊ ወይም ቀጥተኛ መልዕክት መረዳትን እና በምንባቡ የተገለጸውን በመመርኮዝ በመተንበይ፣ በመገመት ጥልቅ ግንዛቤ ማግኘት የሚሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም (Pettit et al 1997) እንደሚያስረዱት፣ ለአንብቦ መረዳት ፈተና የሚመረጡ ምንባቦች ለተማሪዎች ሳቢ፣ግልጽና ቅርብ መሆን አለባቸው፡፡ የሚቀርቡ ጥያቄዎች በምርጫ እንዲሁም በመግለጽ የሚሰሩ ሆነው፣ ጥያቄዎቹ ጥልቅ ግንዛቤን፣ ዋና ሃሳብን ፣የድርጊት ቅደም ተከተልን፣ ማወዳደርን፣ የምክንያትና የውጤት ትስስርን፣ የገጸባህርያት ገለጻን ያካተቱ ናቸው፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢም እነዚህን ባህርያት መሰረት በማድረግ የቅድመ-ልምምድና ድህረ-ልምምድ ፈተናዎች ማዘጋጀት ተችሏል፡፡

### 3.3.1.1 ቅድመ-ልምምድ ፈተና

በመጀመሪያ ደረጃ ለተጠኝ ተማሪዎች የቀረበላቸዉ የቅድመ-ልምምድ ፈተና ነው፡፡ ይህ ፈተና ተጠኝ ተማሪዎች አስቀድሞ ያላቸዉን የአንብቦ መረዳት ችሎታ በመመዘን፣ በአንብቦ መረዳት ችሎታቸው መሰረት በችሎታ አቻ ወይም ተመጣጣኝ የሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ብሎ ለመመደብ ያስቻለ ፈተና ነው፡፡
ቅድመ-ልምምድ ፈተናው ለደረጃው በሚመጥንና በሚያመች መልኩ የፈተና ጥያቄዎች ተደራጅቷል፡፡ በዚህም መሰረት የተዘጋጁ ጥያቄዎች (የቅድመ-ልምምድ ፈተናው) የሙከራ ጥናቱ በቀጥታ ልምምዱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ለተጠኚ ተማሪዎች ተሰጥቷል ፡፡ ፈተናው ከልምምድ በፊት የሚሰጥበት ምክንያትም ተጠኝዎቹ ያላቸዉን የአንብቦ

መረዳት ችሎታ ለመመዘን ሲባል ነው፡፡ይህም ፈተና የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ የተለዩትም በዚሁ ዉጤት መነሻነት ሆኖል፡፡ የፈተና አደረጃጀቱ ቅድመ ፈተናዉ አንድ ምንባብ ያለዉ ሲሆን የአበዳሪዋ ጫና የሚለዉ ከአጭር ልበለድ የተወሰደ ምንባብ ሲሆን ምንባቦቹ ለደረጃዉ በሚመጥንና ለፈተና በሚያመች መልኩ ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡ እነዚህን 64 ተጠኚዎች የቁጥጥርና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመለየት ጥቅም ላይ የዋለዉ ቅደመ-ልምምድ ፈተና ነዉ፡፡ አጥኚዋ የለተያዩ አጭር ልቦለድን ተጠቅማ የተማሪዎችን ደረጃ በሚመጥን መልኩ ያሉበትን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊመዝን የሚችል ፈተና አዘጋጅታለች፡፡ ፈተናዉ ለተጠኚ ተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት ሁለተኛ ድግሪ ባላቸዉ በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በአጥኚዋ አማካሪ ተገምግሞ ማስተካከያዎች ተደርጎበት በማስተካከያዉ መስረት ተሻሽሎ ፈተናዉ ለተፈታኝ ተማሪዎች ቀርቦ ተፈትነዋል፡፡

የቅድመ-ልምምድ ፈተናዉ ‹‹የአበዳሪዋ ጫና›› በሚል ርዕስ ስር የጥያቄዎቹ አደረጃጀት ሃያ ምርጫ፣አስር በምንባቡ መሰረት እዉነት ወይም ሐሰት በማለት የሰጡትን መልስ በምክንያት አስደግፈዉ ማብራሪያ የሰጡበት ፣አምስት ጥያቄ አዛምድ፣ አምስት ጥያቄዎች የተለያዩ አዉዳዊ ፍች እና ሌሎች ማብራሪያ ና ገለጻ የሰጡበት ነዉ፡፡ ሁሉም ጥያቄዎች በምንባቡን መሰረት መልስ የተሰጠባቸዉ ናቸዉ፡፡ በአጠቃላይ የቅድመ-ልምምድ ፈተናዉ በድምሩ 40 ጥያቄዎችን የያዘ ነዉ አባሪ‹‹ሀ››ይመልከቱ፡፡ የቅድመ-ልምምድ ፈተናዉ ለተጠኝ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት በናሙናነት ካልተካተቱ 12 ተማሪዎች በተራ ዕጣ ንሞና ተመርጠዉ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ የፈተናዉ አስተማማኝነትም በክሮቮች አልፋ ቀመር ሲለካ /0.754/ ሆኖል ይህም የአስተማማኝነት ልኬታዉ ዉጤት ተገቢ ነዉ ማለት ይቻላል በመሆኑም ፈተናዉ ተጠኝ ተማሪዎች እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡ አባሪ‹‹መ››ይመልከቱ የቅድመ-ልምምድ ፈተና መጋቢት 23/7/2015 ለስልሳ አራት (64) ተጠኚዎች በሁለት የመፈተኛ ክፍሎች ከ8፡30 እስከ 10፡30 ባለዉ ጊዜ ዉስጥ ተሰጥቷል፡፡ በመቀጠልም በትምህርት ቤቱ በሚያስተምሩ ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እዲታረም ተደረጓል፡፡ ከዚያም የእያንዳንዱ ተማሪ ድምር ዉጤት ከ40 ስንት እንደሆነ ተመዝግቧልይህ ዉጤት የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኖችን በተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመደብ አስችሏል፡፡ይህ የቅድመ-ልምምድ ፈተና በተጨማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ዉጤት ከድህረ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መመዘኛ ፈተና ወጤት ጋር በማወዳደር ስታቴስቲካዊ ትንታኔ ለመስጠት አስችሏል፡፡

የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑን ለማዋቀር ተማሪዎች በቅድመ-ልምምድ ፈተና ባገኙት ዉጤት መሰረት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በቅደም ተከተል ተቀምጧል:: በመቀጠልም ከዝቅተኛ አንድ ከከፍተኛ አንድ በማጣመር ተጠኚዎቹ በዉጤታቸዉ መሰረት ከተጣመሩ በኃላ አንደ አንድ ጥንዶች በሁለት ረድፍ እዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመጀመሪያዉ ረድፍ 16 ጥንዶች ማለትም 32 ተማሪዎች፣ቀጥሎ ባለዉ ረድፍ ደግሞ 16 ጥንዶች ማለትም 32 ተማሪዎቹ በቡድን ደረጃ በዉጤት እኩል ሆነዉ ተመድበዋል፡፡ አንደኛዉ ረድፍ ‹‹ሀ›› ሁለተኛዉ ረድፍ‹‹ለ›› የሚል ስያሜ በመስጠት በድጋሜ ተራ የእጣ ንሞና በመጠቀም በረድፍ ‹‹ሀ›› ስር የተቀመጡት የቁጥጥር ቡድን፣በረድፍ ‹‹ለ›› ስር የተቀመጡት የሙከራ ተብለዉ ተለይተዋል፤ የቅድመ-ልምምድ የፈተና ዉጤት አባሪ‹‹ሰ››ተመልከቱ፡፡

### 3.3.1.1 ድህረ-ልምምድ ፈተና

የድህረ-ልምምድ ፈተናው መሰረት አድርጎ የተዘጋጀዉ የተሰጠውን ትምህርት (ልምምድን) መሰረት አድርጎ ነው፡፡ አጥኚዋ ልምምድ ከሚጠናቀቅበት ቀን አስቀድማ በሰጠችው የልምምድ አቀራረብና አተገባበር መሰረት የድህረ-ልምምድ ፈተና ጥያቄዎችን አዘጋጅታለች፡፡ ድህረ-ልምምድ ጥያቄዎች የክፍሉ ደረጃ በሚመጥንና የተማሪዎችን ዳራዊ ዕወቀት ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቷል፡፡ ፈተናዉ ሁለተኛ ድግሪ ባላቸዉ ከፈተኛ የማስተማር ልምድ ባላቸዉ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና በአጥኚዋ አማካሪ ተገምግሞ ማስተካከያዎች ተደርጎባቸዋል፡፡

በምንባቡ መሰረት ምርጫ ሃያ ጥያቄዎች ፣ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሐሰት›› በማለት በምክንያት አስደግፈው የሚመልሶቸዉ አስር ጥያቄዎች፣ በምንባቡ መሰረት ገለጻዎችንና ጽንሰ ሃሳቦችን በማዛምድ አምስት ጥያቄዎች፣ክፍት ጥያቄዎች፣ከምንባቡ የተረዱትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በጹሑፍ ማብራሪያ የሚሰጡባቸዉ አምስት ጥያቄዎች ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ በመቀጠልም የድህረ-ልምምድ ፈተናው ለተጠኚ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት፣ አስቀድሞ በተገለጸው መሰረት በ12 ተማሪዎች የፓይለት ፈተናዉ ተፈትሾ የፈተናዉ አስተማማኝነትም በክሮቮች አልፋ ቀመር ሲለካ (0.766) ሆኖል ይህም የአስተማማኝነት ልኬታዉ ተገቢ ነዉ ማለት ይቻላል በመሆኑም ፈተናዉ ተጠኝ ተማሪዎች በግንቦት 8/9/2015 ከስዓት በኋላ 8፡30 እስከ10፡30 በሁለት መፈተኛ ክፍሎች በአጥኚዋና በሁለት በትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲፈተኑት ተደርጓል፡፡

ይህ የድህረ-ልምምድ ፈተና በአባሪ ‹‹ለ›› ይመልከቱ፡፡ ይህ የድህረ-ልምምድ ፈተና ህያዉ ፍቅር በሚል ርዕስ ከተጻፈ አጭር ልቦለድ ምንባብ መሰረት ለደረጃዉ በሚመጥንና ለፈተና በሚመች መልኩ የተዘጋጀ ሲሆን ይህ ፈተና አንድ ክፍል ያለዉ በዉስጡ በምንባቡ መሰረት የተዘጋጁ አርባ ጥያቄዎችን የያዘ ነዉ፡፡በዚህ ፈተና ተጠኚ ተማሪዎች ስለምንባቡ አጠቃላይ ግንዛቤ ማግኘታቸዉን ያረጋግጣል፡፡

## 3.4 የምንባቦች አመራረጥ እና የትምህርት አቀራረብ

ለአንብቦ መረዳት የሚሆኑ ምንባቦች ሲመረጡ የተማሪዎችን እድሜ፣ አእምሯዊ ብስለት፣ ፍላጎት፣ ስነጽሁፋዊ ዳህራዊ እውቀት እንዲሁም ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸውን ያገናዘበ፣የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ የሚመጥን፣የምንባቦች የክብደት ደረጃ የተመጠነ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ያለው ተዛምዶ የምንባቦች ሳቢነት የሚሉትን ነጥቦች ያካተተ መሆን አለበት (Lazar 1993) እና (በድሉ 1996) በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በተያያዘም ለአንብቦ መረዳት የሚመረጡ ምንባቦች የደራሲውን አመለካከት ከራሳቸው ጋር ለማገናዘብ የሚረዱ አንድን ነገር በጥልቀት እንዲመረምሩ እንዲገመግሙ የሚያግዝ ጅምር ሀሳቦችን ለመቋጨት ፍላጎት የሚያሳድሩ፣ በከባድ ቃላት ያልተሞሉ ለቀጣይ ተግባራት ቀስቃሽ ሊሆኑ ይገባል በማለት (Madson 1983) ያስረዳሉ፡፡

በዚህ መሰረት ይህ ጥናት የሙከራ ቡድኑን በአጭር ልቦለድ ቋንቋን በማስተማር በተጠኝዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ በአጥኚዋ የማስተማሪያ ጽሐፍ(ቴክስት) ተዘጋጅቷል፡፡ ቴክስቱ ሁለተኛ ድግሪ ባላቸዉ አማርኛ ቋንቋ በሚያስተምሩ ሁለት መምህራን ተገምግሞ፣በአማካሪው አስተያየት ተጠሰጥቶበት፣ ማስተካከያዎች ተደርገውበት ተዘጋጅቷል፡፡የማስተማሪያ ቴክስቱን በአባሪ‹‹ሐ››ይመልከቱ፡፡የማስተማሪያ ጽሐፈ(ቴክስቱ) ሲዘጋጅ፣ የሙከራ ቡድኑን ለማስተማር የተመረጡና የተዘጋጁ ምንባቦች በዋናነት ትኩረት የተደረገባቸው ተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ለማስተማር በሚያስችል መልኩ ነው፡፡በመሆኑም ጽሐፈ(ቴክስቱ) አራት ምንባቦችን የያዘ ነው፡፡ አጫጭር ልቦለዶቹ በምንባብነት ሲመረጡ ከርዕሳቸው ጀምሮ ተማሪዎችን የሚያጓጉ፣ለንባብ የሚያነሳሱ እንዲሆኑ ትኩረት ተደርጎባቸዋል ፡፡የማስተማሪያ ጽሐፈ(ቴክስቱ) አደረጃጀት ከእያንዳንዱ ምንባብ በፊት ቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡የቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች ተግባርም ስለምንባቡ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጡ፣ተማሪዎቹ ወደ ንባብ ከመግባታቸው በፊት ዳራዊ እውቀታቸውን እዲመለከቱ የሚያስችሉ እና ስለምንባቡ ፍንጭ የሚሰጡ ሆነው

ተዘጋጅተዋል፡፡ ቀጥሎም የተቀመጡት የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ተማሪዎች ንባባቸውን ገታ አድርገው ስላነበቡት ሃሳብ ማጠቃለያ መስጠት የሚያስችላቸው ተግባር ነው፡፡ ከዚያም ቀጣዩ ምን መሆን እንደሚችል የሚተነብዩበት ክፍል ነው፡፡ ምንባቦችን ተከትለዉ በቀዳሚነት የተደራጁት‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሀሰት›› በማለት በምክንያት ተደግፈው መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ተማሪዎች በምንባቡ የተላለፉትን መልዕክቶች በውል በመገንዘብ በቂ ማብራሪያ መስጠት የሚያስችሉ ሲሆን፣ተማሪዎች ምንባቡን ደጋግመው እንዲያነቡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በመቀጠል የተደራጁት ደግሞ በምንባቡ መሰረት የሚሰሩ የምርጫና የማዛመድ መልመጃዎች ናቸው፡፡ በየምንባቦቹ የቀረቡት እነዚህ መልመጃዎች ተማሪዎች የነገሮችን ወይም የጽንሰ-ሃሳቦችን አንድነትና ልዩነት፣የሚያስተላልፈትን መልዕክት በስፋት በጥልቀት መመርመር የሚያስችሎቸው ናቸው፡፡ እነዚህ መልመጃዎች በሚስጢር ያለውን የሚፈቱበት፣ ጽንሰ-ሃሳቦችንና ባህሪያትን የሚያስታሰስሩበት ክፍል ነው፡፡ በመጨረሻ የተደራጁት ክፍት ጥያቄዎች ሲሆኑ፣አጠቃላይ የምንባቡን መልዕክት ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ትርጉም ለመስጠጥ ጥረት የሚደርጉበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ተማሪዎች ስለገጸባህሪያት ምንነት የሚገልጹበት፣በምንባቡ የተላለፈዉን መልዕክት መሰረት በማድረግ የራሳቸውን ሀሳብ አስተያየትና ድምዳሜ የሚሰጡበት ነው ክፍት ጥያቄዎች የተለያዩ ውይይቶችንና ክርክሮችን ለማድረግ የሚያስችሉና በቂ ግንዛቤ የሚያስገኙ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ምንባቦችን ተከትለዉ ለቀረቡት የመልመጃዎች ዝርዝር ዓላማ፣መመሪያ፣ የክፍለ ጊዜ ድልደላ እና አተገባበር በአባሪው ዉስጥ ተካቶ ቀርቧል፡፡

ይህን መስፈርት መሰረት በማድረግ ተማሪዎች አንድን ነገር በጥልቀት እንዲገመግሙ ጅምር ሐሳብ እንዲጨርሱ በምክንያት ና በዉጤት ላይ ምላሽ እድሰጡ በማድረግ ማህበራዊ፣ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ እውቀትን እንዲገኙ የሚያደርጉና የማንበብ ፍላጎት የሚያሳድሩ አጫጭር የልቦለድ ምንባቦች ተመርጠዋል፡፡

ተማሪዎች የቅድመ-ትምህርት ፈተናውን ከተፈተኑ በኋላ ለሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የማስተማሪያ ጹሑፎች ወይም ቴክስቶች በአጥኚዋ ተዘጋጅተዋል፡፡ ከአጫጭር ልቦለድ መጽሃፍ ተቀንጭበው የተወሰዱ ሲሆን የተማሪዎችን የክፍል ደረጃና ግንዛቤ መሰረት ባደረገ መልኩ

ተዘጋጅተዋል፡፡ ሁሉም የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ማስተማር የተዘጋጁ መልመጃዎችንና ተግባራትን ይዘዋል፡፡ቴክስቶቹ ለሙከራ ቡድኑ በትምህርትነት ከመቅረባቸው በፊት ሁለተኛ ዲግሪ ባላቸው ሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በአጥኚዋ አማካሪ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል እሱን ተከትሎም ማሻሻያ ተደርጎባቸው በተማሪዎቹ ልክ ተባዝተው ለእያንዳንዱ ተማሪ ተሰጥቷል፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስም በተቃራኒ ፈረቃ በሳምንት ሁለት ቀናት (ሰኞና አርብ) በቀን ለአርባ ደቂቃ ለአንድ ወር ከአስራ ምስት ቀን ማለትም ከመጋቢት 19/7/2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 5/9/2015 ዓ.ም በአጥኚዋ ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡ የተዘጋጀው ጹሑፍ ወይም ቴክስት ተማሪዎች አንብበው የተረዱትን ሃሳብ ምላሽ የሚሰጡበትና የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን የሚያዳብር ተግባራት የያዘ ሲሆን የማንበብ ተግባራትን ቅድመ-ንባብ፣ በንባብጊዜ እና በድህረንባብ በማስታዎስ የሚመለሱ ጥያቄዎች፣ እውነት/ሀሰት ጥያቄዎች፣ የተገነዘቡትን በጽሁፍ የሚገልጹባቸው ጥያቄዎች፣ የምርጫ ጥያቄዎች፣እማራዊና ፍካራዊ ፊች፣ አውድን በመጠቀም ፍችን እንዲሰጡና አንብቦ የመረዳት ተግባራትን ለማከናዎን የሚያስችሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በቡድን ሆነዉ እንዲወያዩ እንዲከራከሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች በመሆናቸዉ በቡድን የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸዉ እና ለመምህራናቸዉ እንዲያቀርቡ ተደርጓል፡፡

### 3.4.1 የምንባቦች አመራረጥ

አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የተመረጡ ምንባቦች ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ለደረጃው ከተመረጠው የትምህርት ዓላማ አንጻር እንዲሁም የክፍል ደረጃ ጋር የተገናዘቡ እንዲሆኑ ጥረት ተደርጓል፡፡ ምንባቦቹ ወይም አጫጭር ልቦለዶች ከተለያዩ የአጭር ልቦለድ መድብሎች ከርዕሳቸውና ከይዘታቸው ቅርበት አንጻር ተመርጠዋል፡፡ አጭር ልቦለዶቹ ላይ ያለው አቀነጃጀት፣ የቃላትና የተለያዩ ማብራሪያዎች ለማስተማርና ለተማሪዎች ተስማሚ ከማድረግ አንጻር ማሻሻያዎች ተደርገውባቸዋል፡፡ በተቻለ መጠን እንዲያጥሩም ተደርጓል፡፡

በዚህ መሰረት በአንድና በሁለት ክፍለ ጊዜ የሚለማመደዋቸው ሆነው ተዘጋጅተዋ (Ghasemi 2011) ማለት ይቻላል፡፡ ምንባቦቹ ሲመረጡም፣ (Hill 1986) Nuttall (1982)፣ (Lazar 1993) አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚያስችሉ ብለው ያስቀመጡዋቸውን የመምረጫ መስፈርቶች በማገናዘብ ነው፡፡ የምንባብ መምረጫ

መስፈርቶችም፡-

- ከተማሪዎቹ ማህበረ በህላዊ ልምድ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው፡፡
- ለተማሪዎች አዲስ ይዘትን የሚያስተዋውቅ ርዕስ ጉዳይ የያዘ፡፡
- ተማሪዎች የራሳቸውን አመለካከት ከሌሎች ጋር እንዲያነጻጽሩ እድል የሚፈጥር፡፡
- ከተማሪዎች የእውቀት አድማስ ጋር የሚጣጣም ይዘት ያለው፡፡
- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ማዘጋጀት የሚያስችል የሚሉት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም አጫጭር ልቦለዶች ሲመረጡ፣ ሳቢ፣ አንድን ነገር በተለያዬ መልኩ የሚገልጹ ከዘመኑ ሁኔታ ጋር የተዛመደና የዘመኑን አካባቢያዊ ባህል የሚገልጹ ለማሪዎች ቅርብ መሆናቸው ሊተኮርበት ይገባል፡፡ የልቦለዶች የቋንቋ ብቃት ለተማሪዎች የሚስማሙ፣ ተማሪዎች ለሰነጽሁፍ በቀረቡና በተጋለጡ ቁጥር በስነ-ጽሁፍ ተወዳዳሪና ብቁ ሊያደርጓቸው የሚችሉ መሆናቸው ሊጤን ይገባል፡፡ አጫጭር ልቦለዶቹ ከስነ-ልቦና አንጻር ተማሪዎችን የሚያረኩና የበለጠ ለማንበብ እንዲተጉ የሚያስችሉ መሆን እንዳለባቸው (Ghasemi 2011) ያስረዳሉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ ስነ-ጽሑፍዊ ምንባቦች ለቋንቋ ማስተማሪያነት ሲመረጡ ትኩረት የሚደረግባቸውን ነጥቦች (Brumfit 1986) በዝርዝር አስቀምጠዋል፡፡ እነዚህም የምንባቡ የቋንቋ መዋቅር ለተማሪዎች ተስማሚነት ያለው፤ ቋንቋው የዕለት ከዕለት የቋንቋ አጠቃቀም መገለጫ የሆነ፤አሉታዊ ያልሆነና አዎንታዊ ባህሪን የሚያስተምር፣በቂ የሆነ ባህላዊ ዳራዊ ዕውቀትን የሚያስገኝ፣ተማሪዎችን የሚያነሳሳ ሳቢነት ያለው፣ ለተማሪዎች ሰፊ እይታን መፍጠር የሚችል መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡ ስለሆነም ምንባቦቹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት አንብቦ መረዳትን ለማጎልበት ሲባል ከተለያዩ መድብልችና መጽሐፍች ለምንባብ በሚያመች መንገድ የቀረቡትን ንድፈ ሃሳቦች ላይ በመመስረት ማስተካከያዎች በማድረግ ተወስደዋል፡፡

### 3.4.2 የመልመጃዎች አዘገጃጀት

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በአጭር ልቦለድ አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የተለያዩ መልመጃዎች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ልምምዶችን ለመስራት የቡድን ተግባር በሚያከናውኑበት ጊዜ አንደ ቡድን፡አራት አባላትን የያዙ ስምንት ቡድኖች ተዋቅረዋል፡፡

ልምምዶችን ሲጀምሩ የልቦለዶች ኮፒዎች ለተማሪዎች እንዲዳረሳቸው ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ የመልመጃዎች አደረጃጀትና ልምምዶች በሶስት ተከፍለዋል፡፡እነዚህም ቅድመ-ንባብ፣የንባብ ጊዜ እና ድህረ ንባብ ተግባራት ናቸዉ፡፡ በዚህም (Ghasemi 2011) የተጠቀሙባቸውን የአዘገጃጀትና የአተገባበር ስሌቶች ተግባረዊ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል፡፡በየሂደቱ ተግባራዊ የሆኑ ድርጊቶች በቅደም ተከተል ተገልጽዋል፡፡

### 3.4.3 ቅድመ-ንባብ ተግባራት

ተማሪዎች ምንባቡን ከማንበባቸው በፊት የቀደመ-እውቀታቸውን መሠረት በማድረግ ስለምንባቡ ርዕሰ ጉዳይ ግንዛቤ የሚያገኙበት የቅድመ-ንባብ ተግባር ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች ስለ ታሪኩ ቅድመ ትንቢያ እንዲሰጡ ተደርጓል፣ ስለታሪኩ ዳራ በቅድመ-ምንባብ ጥያቄዎች መነሻነት በቡድን በመወያየት ሀሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ በቅድመ-ንባብ ጥያቄዎች አማካኝነት ከምንባቡ ርዕስ በመነሳት ቀጣዩ ምን ሊሆን እንደሚችል ፍንጭ እንዲያገኙ፣ ስለጭብጡ ግንዛቤ እንዲይዙ ያስችላቸዋል፡፡ ከቀረበው ምንባብ ተመርጠው ለወጡ ቃላት የነበራቸው እውቀት መነሻ በማድረግ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡ እንዲሁም የቃላትን ፍቺ ከምንባቡ አገባብ ባላቸው ፍች ተመስርተው ያዛምዳሉ፡፡

### 3.4.4 የንባብ ጊዜ ተግባራት

በዚህ ሂደት ተማሪዎች ወደ ንባብ ሲገቡ፣በቃል ድምጽ እያሰሙ እንዲያነቡ ተደርጓል፤ይህም የተማሪዎችን መናገርና የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሊያዳብር ይችላል፡፡እንዲሁም ምንባቦችን በጽሞና (ድምጽ ሳያሰሙ) ንባብ እንዲያነቡም ተደርጓል፤በዚህን ጊዜ ተማሪዎች የምንባቡን መልዕከት የበለጠ እንዲረዱ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ተማሪዎች በንባብ ሂደት ላይ እያሉ ንባባቸውን ቆም አድርገው ሁለት ወይም ሶስት ጥያቄዎች በማቅረብ እስከ አነበቡት ድረስ ባለው ማጠቃለያ እዲሰጡ ተደርጓል፡፡ በዚህ ዉሰጥ ጅምር ዓረፍተነገሮችን በመስጠት እንዲቋጩ ማድረግ፣ እንዱሁም ቀጣዩ የታሪኩ ክፍል ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲተነብዩ ተደርጓል፡፡ የተወሰኑ ቃላትና ሐረጋትን በመግለጽ ተማሪዎች ገፀ-ባህሪያትን እንዲገልጹ፣ ባአነበቡት ተግባር ጥልቅ ውይይት እንዲያደርጉ ጥረት ተደርጓል፡፡

### 3.4.5 የድህረ-ንባብ ተግባራት

ተማሪዎች (ተጠኝዎች) በድህረ ንባብ ተግባር ከምንባቡ ለወጡ ‹‹እውነት›› ወይም ‹‹ሀሰት›› በማለት ከመለሱ በኋላ የተብራራ ምክንያት የሚሰጡባቸው፣ የቃላትና የሀረጋትን ምንነትና በተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች ተደግፈው የቀረቡ የምርጫና የማዛመድ ጥያቄዎችን ትክክለኛ መልስ የሚመርጡበት፣በታሪኩ ላይ ጥልቅ እሳቤና ትንታኔ ለመስጠት የሚያስችል ክፍት ጥያቄዎች የተዋቀሩበት፣አጠቃላይ የሆኑ ጥያቄዎችን በመስጠት፣ውይይትና ክርክር እንዲያደርጉ የሚያስችሉ፣የምንባቡን የትኩረት ነጥብ ለመገንዘብ በሚያስችሉ ጥያቄዎች ተደራጅቶ ቀርቧል፡፡እንዲሁም በምንባቡ ማማብራሪያ መስጠት የሚያስችሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ በአጠቃላይ የመልመጃዎች አደረጃጀትና አቀራረብ (Lazar 1993) መሰረት በማዴረግ የተዘጋጀ ነው ፡፡

## 3.5 የአጠናን ሒደት

ጥናቱ ለተከታታይ በሳምንት ሁለት ቀን ለወር ከአስራምስት ቀን የተሰጠ ሲሆን ለትምህርት ቤት አመራሮች፣ ለተጠኝ ተማሪዎችና አስረኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን ለሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በሁሉም ተማሪዎች ና ክፍሎች ያልዳበረ እንደሆነ፣ የአንብቦ መረዳት ችግር በይበልጥ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ጎልቶ እንደሚታይ፣ ጥናቱ ለምን ዓላማ እንደሚውልና ችግሩን ለመቅረፍ ደግሞ ሙከራዊ ጥናት እንደሚያስፈልግ በአጥኚዋ መጋቢት 19/7/2015 ቀን ጥዋት 5፡00 እስከ 5፡30 ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ ተማሪዎችም ለመማር ፈቃደኛ መሆናቸውን ተጠይቀው ፈቃደኛነታቸውን ገልጸዋል፡፡

አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ላይ የተሻለ ግንዛቤ ያላት አጥኚዋ ስለሆነች ለሙከራ ቡድኑ በአጥኚዋ ትምህረቱ ተሰጥቷል፡፡ እንደዚሁም ለቁጥጥር ቡድኑ በትምህርት ቤቱ መምህራን በተለመደዉ መንገድ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡

ተማሪዎችን የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ብሎ ለመለየት ትምህርቱ ከመሰጠቱ በፊት ለመረጃ መሰብሰቢያ የሚሆኑ ምንባብ ለቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በአጥኚዋ ተዘጋጅቷል ምንባቡ ለቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ከመሰጠቱ በፊት በአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተመጣጣኝነታቸው ተገምግሞ ማሻሻያ ተደርጎባቸዋል፡፡ የፈተናዎቹ አስተማማኝነትም በክሮቮች አልፋ ተረጋግጧል፡፡መጋቢት 23/7/2015ዓ.ም የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በናሙናነት ለተመረጡ 64 ተማሪዎች በሁለት

የመማሪያ ክፍል በመክፈል በአጥኚዋና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲፈትኑ ተደርጓል፡፡

የቅድመ-ትምህርት ፈተናው ካበቃ በኋላ የመልስ ወረቀቶችን በአግባቡ በማሰባሰብና በማደራጀት እንዲሁም በሁለት መምህራን እንዲታረም በማድረግ በውጤታቸዉ ተመጣጣኝነት እና አቻነት የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተብሎ ተለይቶ በሰንጠረዥ ተመዝግቦ ተቀምጧል፡፡ ከዚያም አጥኚዋ የሙከራ ቡዱኑን ለማስተማር ከአጭርና ረጅም ልቦለዶች ቅንጫቢ በመውሰድ ምንባቦችን አዘጋጅታለች፡፡ ሁሉም ምንባቦች በሳምንት የሁለት ቀን ተግባር ያላቸውና በቀን ለአርባ ደቂቃ መሰጠት የሚችሉ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡የተዘጋጁትን የማስተማሪያ ጹሑፎች ለሙከራ ቡድኑ በተቃራኒ ፈረቃ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑን በተለመደው ማስተማሪያ ዘዴ የአስረኛ ክፍል መጸሐፍን በመጠቀምና በትምህርት ቤቱ መምህርት እንዲማሩ ተደርገዋል ፡፡

የሙከራ ቡድኑ የምንባቡን ታሪክ ና ጭብጡን፣ ገጸባህርይና መዋቅሩን በማገናዘብ ዋና ሐሳቡን መለየት፣በጥበቡና በታሪኩ መዋቅር መካከል ያለውን ዝምድና መተንተን እንዲችሉ፣ የገጸባህርይውን አለባበስ፣ አነጋገር፣ አስተሳሰብ የሚገልጹ ዝርዝሮችን እንዲያዘጋጁ በማድረግ የምንባቡን ዋና ፍሬ ሀሳብ ማዉጣት ፣ ንዑስ ሐሳቡን በመለየት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን እንዴት መስራት እንዳለባቸው ልዩ እገዛ እየተደረገላቸው ከመጋቢት 19/7/2015ዓ/ም እስከ ግንቦት 05/9/2015ዓ/ም ለአንድ ወር ከአስራ አምስት ቀን ያህል ትምህርቱን እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

በመጨረሻም የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ግንቦት 08/9/2015 ዓ/ም ከ8፡30 እስከ 10፡30 ሰዓት በአጥኚዋ ና በሁለት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ፈተናዉ በአግባቡ ታርመውና ተደራጅተው ለትንተና በሚመች መንገድ ቀርበዋል፡፡

### 3.6 የጥናቱ የመረጃ መተንተኛ ስልት

ከጥናቱ ተተኳሪዎች በፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች ከመተንተናቸው በፊት መልሶቹ ትክክለኛ በሆነ መንገድ መሞላታቸው ተረጋግጧል፡፡ መረጃው ለትንተና በሚያመች መልኩ ኮድ ተደርጎ በውጤት መመዝገቢያ ሰንጠረዥ ሰፍሯል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ የጥናቱን አላማ ማሳካት ይቻል ዘንድ ገላጭ እና ድምደሚዊ ስታትስቲክስ በመጠቀም ተተንትኗል፡፡በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር መቻል አለመቻሉን ለመለካት በቅድመ-ትምህርትና በድህረ-ትምህርት በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰበው መረጃ በገላጭ ስታትስቲክስ (በአማካይ በመደበኛ ልይይት)፣ የጉልህነት ደረጃውን ለማወቅ በነጻ ናሙና ቲ- ቴስትና በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት በድምደሚዊ ስታትስቲክስ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤትና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሰንጠረዥ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤትና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት እንዲሁም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤትና ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ደግሞ ለየብቻቸው ተነጻጽረው በገላጭ ስታትስቲክስ (በአማካይና በመደበኛ ልይይት)፣በድምደሚዊ ስታትስቲክስ የጉልህነት ደረጃውን ለማወቅ በዳግም ልኬት ቲ- ቴስት ተሰልቷል፡፡

# ምዕራፍ አራት :- የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ

## 4.1 የመረጃ ትንተና

ይህ ጥናት አላማ አድርጎ የተነሳው አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጾ መመርመር ነው፡፡ ይህን ለማሳካት በፈተና ከተሰበሰበው መረጃ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታም ለማዳበር አዎንታዊ ወይስ አሉታዊ የሚል አቅጣጫ የለሽ የምርምሩን መላምት ለመመለስ በቅድመ-ልምምድና በድህረ ልምምድ ፈተናዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ስለሆነም የመረጃው ውጤት በገላጭ ስታትስቲክስ በአማካይ፣በመደበኛ ልይይት፣ በድምደሚዊ ስታትስቲክስ በነጻ ናሙና ቲ-ቴስትና በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ቀርቧል፡፡

### 4.1.1.ከፈተናዎች የተገኘ የጥናቱ መረጃ ትንተና

በፈተናዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደየባህሪያቸዉ ተደራጅተዉ በቅደም ተከተላቸዉ መሰረት እደሚከተለዉ ተተንትነዋል፡፡ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑን ተጠኚዎች ከልምምዱ በፊት ያላቸዉን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና የቁጥጥር ቡድኑ ከ40 ያስመዘገበዉ ዉጤት በአባሪ ‹‹ሰ›› ተመላክቷል፡፡ የሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ዉጤት በአባሪ‹‹ሰ›› ተመላክቷል፡፡ በዚህ መሰረት የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ትምህርት ያስመዘገቡት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት በሰንጠረዥ 4.1.1.1 ቀርቧል፡፡

#### 4.1.1.1 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ- ትምህርት ፈተና

*ሠንጠረዥ 4.1.1.1 ፡-የቅድመ- ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤትየሙከራና የቁጥር ቡድን ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት*

| ቡድን | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የ t; test ዋጋ | የነጻነት ደረጃ (df) | የ"p; (tab) | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 32 | 17.41 | 2.928 | 0.72 | 64 | 0.943 | 0.943 >0.05 |
| የቁጥር | 32 | 17.38 | 2.893 | | | | |

*ምንጭ ፡ (ከአጥኚዋ የSPSS v, 26. 2015)*

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ የሚያሳየው የሙከራ ና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ውጤት ያለውን ልዩነት በአማካይ ፣በመደበኛ ልይይትና የልዩነታቸውን የጉልህነት ደረጃ በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት ስሌት ተመሳሳይነት ያላቸዉ ይመስላል ፡፡
በሰንጠረዠ ከሰፈረው ገላጭ ስታትስቲክስ መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (አማካይ=17.41) ፣የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (አማካይ=17.38) በ (አማካይ=0.31) አንሶ ይታያል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ በአማካይ ያለው ልዩነት ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=2.928) ከቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=2.893) በ (0.035) በልጦ ተገኝቷል፡፡ ይህም የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ከሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት ያለው ርቀት የጠበበ መሆኑን ያሳያል፡፡
በሰንጠረዠ 4.1.1.1 እንደተመለከትነዉ የተሳታፊ ተማሪዎች የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህልዩነት መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በነጻ ናሙና ቲ- ቴስት ተሰልቶ “t” (0.72), “p”=0.943) ሆኗል፡፡ይህም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት የሌለ መሆኑን ያሳያል፡፡ከዚህ የምንረዳዉ ተጠኝ ተማሪዎች ከልምምዱ በፊት በቡድን ደረጃ የአንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ ተመጣጣኝ እንደነበረ ያሳያል፡፡
ሌላዉ በፈተና የተሰበሰበ መረጃ የድህረ- ልምምድ የፈተና ዉጤት ነዉ፡፡የቁጥጥር ቡድኑ በመደበኛዉ መንገድ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ አጥኚዋ ባዘጋጀችዉ በአጭር ልቦለድ አማካይነት አማረኛ ቋንቋ ከተማሩ በኃላ ሁለቱም ቡድኖች አንድ አይነት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ተፈትነዉ ያስመዘገቡት ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የፈተና ዉጤት በአባሪ ‹‹ሸ›› ይመልከቱ፡፡የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የፈተና ዉጤት በአባሪ‹‹ሸ›› ይመልከቱ፡፡በዚህ መሰረት የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ልምምድ የፈተና ዉጤት ተነጻጽሮ በሰንጠረዥ 4.1.1.2 ቀርቧል፡፡ የድህረ-ትምህርት ፈተና የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

### 4.1.1.2 የሙከራና የቁጥጥር ቡድን የድህረ- ትምህርት ፈተና

*ሠንጠረዥ፡-4.1.1.2 የድህረ -ትምህረት አንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤት የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ንጽጽር በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት*

| ቡድን | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የ t; ዋጋ (test) | የነፃነት ደረጃ (df) | የ p ዋጋ (tab) | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የሙከራ | 32 | 24.94 | 3.893 | 11.429 | 62 | 0.000 | 0.000 < 0.05 |
| የቁጥጥር | 32 | 17.3 | 2.495 | | | | |

*ምንጭ ፡ (ከአጥኚዋ የSPSS v,26. 2015)*

ሰንጠረዥ 4.1.1.2፡- በድህረ-ትምህረት የአንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤት በሙከራ ቡድኑና በቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለዉ ልዩነት በገላጭ ስታትሰቲክስ (በአማካይ፣በመደበኛ ልይይት የልዩነታቸዉን ጉልህነት ደረጃ በነጻ ናመና ቲ-ቴስት ያሳያል፡፡ ከላይ ከሰንጠረዡ ገላጭ ስታትስቲክስ መረጃ መረዳት እንደሚቻለዉ የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ዉጤት (አማካይ=24.94) ፣የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ዉጤት (አማካይ=17.3) በ (7.64) በልጦ ይታያል፡፡ሰንጠረዥ 4.1.1.2 እንደሚያሳየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በአማካይ የሰፋ ልዩነት ይታይበታል፡፡ ልዩነቱ ጉልህ መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ሲሰላ “t” 11.429 “p”=.000) ነው፡፡የጉልህነት ደረጃው ከመቁረጫ ነጥቡ (p<0.05) (0.000 < 0.05) ስለዚህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

የቅድመ-ትምህረት ፈተና ዉጤትና የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑእና የቅደመ-ትምህርት ፈተና ዉጤትና የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት የሙከራ ቡድኑ ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ቀጥሎ ባሉት ሰንጠረዦች ቀርቧል፡፡

### 4.1.1.3 የቁጥጥር የቅደመ-ትምህረትና የድህረ-ትምህርት

*ሠንጠረዥ 4.1.1 .3፡- የቅደመ-ትምህረትና የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት የቁጥጥር ቡድኑ ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት*

| የቁጥጥር ቡድን | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የt ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የp ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | 32 | 17.38 | 2.893 | .503 | 31 | 0.618 | 0.618 >0.05 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | | 17.03 | 2.495 | | | | |

*ምንጭ ፡ (ከአጥኚዋ የSPSS v,26. 2015)*

ከላይ ከሰንጠረዡ  እንደሚታየው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ያለውን ልዩነት ለማነጻጸር በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይትና  የልዩነታቸውን የጉልህነት ደረጃ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ነው፡፡ በሰንጠረዡ ከሰፈረው ገላጭ ስታትስቲክስ መረዳት እንደሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት (አማካይ=17.38) ከድህረ ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (አማካይ=17.03) በ (0.35) በልጦ ይገኛል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ በአማካይ ያለው ልዩነት ሲታይ የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ- ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=2.893) ከድህረ-ትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=2.495) በ (0.398) አንሶ ይገኛል፡፡ በዚህ ሰንጠረዥ እንደተመለከተው የቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት እና  ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት መካከል ያለው ልዩነት የጎላ መሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥም መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ሲሰላ “t”503,“p”=0.618) ሆኖ በመገኘቱ የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ትምህርትና ድህረ- ትምህርት ፈተናዎች መካከል ጉልህ ልዩነት የሌለው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ማለትም የቁጥጥር ቡድኑ የቅድመ-ትምህርት ከድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት ያለው ልዩነት ተቀራራቢ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም እንደልዩነት አይቆጠርም፡፡

የአንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤት የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህረት እና ድህረ-ትምህርት ንጽጽር በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ቀጥሎ ባለዉ ሰንጠረዥ 4.1.1.4 ቀርቧል፡፡

### 4.1.1.4 የሙከራ ቡድኑ የቅደመ-ትምህረትና የድህረ-ትምህርት

ሠንጠረዥ4.1.1 4፡-የሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ትምህርትእና የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ዉጤት ንጽጽር በዳግም ልኬት ቲ-ቴስት

| የሙከራ ቡድን | ናሙና | አማካይ | መደበኛ ልይይት | የt ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የp ዋጋ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ቅድመ ትምህርት ፈተና ውጤት | 32 | 17.41 | 2.928 | 11.429 | 32 | 0.000 | 0.000<0.05 |
| ድህረ ትምህርት ፈተና ውጤት | | 24.94 | 3.893 | | | | |

ምንጭ ፡ ከአጥኚዋ የSPSS v, 26. 2015

በሰንጠረዥ 4.1.1.4 እንደሚታየው የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ያለውን ልዩነት ለማነጻጸር በገላጭ ስታትስቲክስ በአማካኝ መደበኛ ልይይትና የልዩነታቸውን የጉልህነት ደረጃ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ነው፡፡ከሰንጠረዡ ገላጭ ስታትስቲክስ መረዳት እንደሚቻለው የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይውጤት (አማካይ=24.94) ከቅድመ-ትምህርት ፈተናው አማካይ ውጤት (አማካይ=17.41) በ(7.53) በልጦ ይገኛል፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎች ያስመዘገቡት ውጤት ከአማካይ ውጤቱ በአማካይ ያለው ልዩነት ሲታይ የሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=3.893) ከሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርት ፈተና መደበኛ ልይይት (sd=2.928) በ(0.965) አንሶ ይገኛል፡፡ ከሰንጠረዡ እንደሚታየው የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ከቅድመ-ትምህርት ፈተና በአማካይ ውጤት ሰፊ ልዩነት ታይቶበታል፡፡ በመሆኑም ልዩነቱ ጉልህ መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ መረጃው በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ሲሰላ "t"11.429, "p"=0.000) ሆኗል፡፡ ይህም በቅድ-መትምህርትእና ድህረ-ትምህርት ፈተናዎች መካከል ጉልህ ልዩነት ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡ይህም የሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ ተማሪዎች ከተማሩ በኋላ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ውጤት የተሻሻለ መሆኑን ያሳያል፡፡የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያዳብር ይሆን? የሚለው መሰረታዊ መላምት አዎንታዊ ምላሽ አግኝቷል፡፡ ምክንያቱም የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኑ

በቅድመትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ጉልህ ልዩነት አልነበራቸውም፡፡ ነገር ግን በድህረ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ ይህም በሙከራ ቡድኑ የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ላይ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

በውጤት ትንተናው የታየው አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚኖረውን አስተዋጾ መመርመር ነው፡፡ ስለሆነም በአንብቦ መረዳት ፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ስታትስቲክስ ተተንትነው ማብራሪያ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ እና የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤትና የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና ውጤት በነጻ ናሙና ቲ-ቴስት ሰሌት በመጀመሪያ የታየው የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ንጽጽር ነው፡፡ በዚህ ንጽጽርም የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት (በሰንጠረዥ 4.1.1.1) በጣም ተቀራራቢ ሆኖ ስለተገኘና ጉልህ ልዩነት የማይታይበት በመሆኑ ሁለቱም ቡድኖች ተቀራራቢ የሆነ ውጤት ማስመዝገባቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በቡድኖች መካከል ምንም አይነት የማስተማር ልዩነት ሳይፈጠር በመቅረቱ ነው፡፡

በሰንጠረዥ 4.1.1.2 የሙከራና የቁጥጥር ቡድኑ ድህረትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ንጽጽር እንደሚያመለክተው በሁለቱ ቡድኖች መካከል ባለው የፈተና ውጤት ከፍተኛ የሆነ ልዩነት እንዳለ የቀረበው የስታትስቲክስ ስሌት ያመለክታል፡፡ የሙከራ ቡድኑ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ በማስተማር ዘዴ በመማሩ እና በተለመደው መንገድ የአንብቦ መረዳት ማስተማሪያ ዘዴ ሲማር ከቆየው ከቁጥጥር ቡድኑ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ ውጤቱም (መንግስቱ., 2008)፣ (Jeni, 2020) (hasibuan, 2019) ከገለጹት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ቋንቋን ማስተማር ውጤታማ ነው ከሚለው ሃሳብ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመቀጠል የታየው በሰንጠረዥ4.1.1.3 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት፤በሰንጠረዥ 4.1.1.4 ደግሞ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤቶች ለየብቻ በዳግም ልኬት ናሙና ቲ-ቴስት ተነጻጽረው ቀርበዋል፡፡የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-

ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ልዩነቱ ተቀራራቢ ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ውጤት ከቅድመ-ትምህርት ፈተና ውጤት በአማካይ በልጦ ተገኝቷል፡፡ በልጦ የተገኘው የድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ($p < 0.05$) ሆኖ መገኘቱ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያሻሻለ መሆኑን አመላክቷል፡፡

በጥናቱ ውጤት መሰረት አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ መሻሻል የታየው አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ ለማስተማሪያነት የቀረቡ ጹሑፎች ሳቢ እና አዝናኝ ፣ፈጠራ የተሞላበት በመሆኑ፣ ባህል፣ወግ የገጸባህርያትን እንቅስቃሴ ፣መልክ፣ተክለሰውነት፣ባህርይና አመለካከት በትኩረት እንዲገነዘቡ የሚያደርጉና በጽሁፍ ወይም በምንባቡ ውስጥ ያለን መረጃ ለመረዳት የሚያበቁ በመሆናቸው የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነት በመጨመሩ ለዚህ ውጤት አብቅቷቸዋል ማለት ይቻላል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ጉልህ ሚና አለው፡፡ ይህም በሙከራና በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤትና በሙከራ ቡድኑ ቅድመ-ትምህርትና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታትስቲክስ ጉልህ ልዩነት ታይቷል፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር አዎንታዊ ምላሽ አለው የሚል አንድምታ ይኖረዋል፡፡ለዚህም የአንብቦ መረዳት ፈተና የሙከራ ቡድኑ የድህረ-ትምህርት አማካይ ውጤት በስታትስቲክስ ጉልህ ሆኖ መታየቱን ያስረዳል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡-ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳቦች

በዚህ የጥናት ምዕራፍ ስር የጥናቱ ማጠቃለያ፣መደምደሚያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች

ቀርበዋል፡፡በመጀመሪያ ማጠቃለያ በሚለዉ ንዑስ ርዕስ ስር ከጥናቱ ዋና አለማ፣ዝርዝር አለማ መላምቶች በመነሳት የጥናቱ ዘዴና የተገኙ ዉጤቶችን ለማሳየት ተችሏል፡፡በጥናቱ የተገኙ ዉጤቶችን መሰረት በማድረግ ማብራሪያዎች ተጠቃለዉ ቀርበዉ መደምደሚያ እንዲሰጥበባቸዉ ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም ከጥናቱ አጠቃላይ ግኝት በመነሳት አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማሪያ ዘዴ ጋር የተያያዙ አስተያየት ተሰንዝረዋል፡፡

## 5.1 ማጠቃለያ

ምዕራፍ አንድ ላይ እንደተገለጸዉ የዚህ ጥናት ዋና አላማ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ አማርኛ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በማዳበር ረገድ የሚኖረውን አስተዋጾ መመርመር ነበር፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ሁለት አበይት መላምቶችን አማራጭና አልቦ መላምቶች በጥናቱ ዉስጥ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

በጥናቱ የተሳተፉት በደቡብ ምዕራብ ክልል በቤንች ሸኮ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ በቢፍቱ ሚሊንየም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ የትምህርት ቤቱ የናሙና አመራረጥ በአመች ናሙና አመራረጥ ዘዴ የተመረጠ ነዉ፣ምክንያቱም አጥኚዋ የሙከራ ትምህርቱን በተገቢዉ ሰዓትና ወቅት ለማከናወን ስለሚያመቻት በተጨማሪም ከዚህ ቀደም ስታስተምርበት የቆየችበት ትምህረት ቤት በመሆኑ በአመች የናሙና ዘዴ ተመጧል፡፡ እንዲሁም የክፍል ደረጃዉ በአላማ ተኮር የአመራረጥ ዘዴ ተመርጧል ምክንያቱም አጥኚዋ በተለያዩ የክፍል ደረጃዎች ስታስተምር በሁሉም ክፍሎች የአንብቦ መረዳት ችግር ያስተዋለች ቢሆንም በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ግን ጎልቶ በመታየቱ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም የክፍል ደረጃው አላማ ተኮር ንሞና ዘዴን በመጠቀም ተመርጧል፡፡

የጥናቱ አካላዮች በ2015 ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ በዚህ የክፍል ደረጃ የሚገኙ 128 ተማሪዎች በሁለት የመማሪያ ክፍሎች ይገኛሉ፡፡ ከሁለቱም ክፍል ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጭ ናሙና የተመረጡት 64 ተማሪዎችን የቁጥጥር ና የሙከራ ቡድን ብሎ ለመክፈል ቅድመ-ትምህርት ፈተና አገልግሎት ላይ ዉሏል ፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎችም በተዘጋጀላቸው አጭር ልቦለድ ከመማራቸው በፊት ቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና በትምህርት ቤቱ የቋንቋ መምህራንና በጥናቱ

አማካሪ ማስተካከያ ታክሎበትና የቅድመ-ልምምድ ፈተናዉ ለተጠኝ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት በናሙናነት ካልተካተቱ 12 ተማሪዎች በተራ ዕጣ ንሞና ተመርጠዉ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ የፈተናዉ አስተማማኝነትም በክሮቮች አልፋ ቀመር ሲለካ/0.754/ ሆኖል ይህም የአስተማማኝነት ልኬታዉ ተገቢ ነዉ ማለት ይቻላል በመሆኑም ፈተናዉ የተጠኝ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የቁጥጥር እና የሙከራ ቡድኑን ለማዋቀር ተማሪዎች በቅድመ-ልምምድ ፈተና ባገኙት ዉጤት መሰረት ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በቅደም ተከተል ተቀምጧል፤ በመቀጠልም ከዝቅተኛ አንድ ከከፍተኛ አንድ በማጣመር ተጠኚዎቹ በዉጤታቸዉ መሰረት ከተጣመሩ በኃላ አንደ አንድ ጥንዶች በሁለት ረድፍ እዲቀመጡ ተደርገዋል፡፡ በዚህ መሰረት በመጀመሪያዉ ረድፍ 16ጥንዶች ማለትም 32 ተማሪዎች፣ቀጥሎ ባለዉ ረድፍ ደግሞ 16 ጥንዶች ማለትም 32 ተማሪዎቹ በበድን ደረጃ በዉጤት እኩል ሆነዉ ተመድበዋል፡፡ አንደኛዉ ረድፍ ‹‹ሀ›› ሁለተኛዉ ረድፍ‹‹ለ›› የሚል ስያሜ በመስጠት በድጋሚ ተራ የእጣ ንሞና በመጠቀም በረድፍ ‹‹ሀ›› ስር የተቀመጡት የቁጥጥር ቡድን፣በረድፍ ‹‹ለ›› ስር የተቀመጡት የሙከራ ተብለዉ ተለይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት የቅድመ-ፈተና ዉጤት የቁዋዋር ቡድኑ 17.38 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ 17.41 ሆኖል ተማሪዎች በቅደመ-ፈተና ዉጤታቸዉ ተመጣጣኝ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ መሆናቸዉን ያስገነዝበናል፡፡

በመቀጠልም የድህረ-ትምህርት ፈተናዉ የሙከራ ቡድኑን ለማስተማሪያነት በተዘጋጀው አጫጭር ልቦለድ ምንባቦች (ቴክስት) ለስድስት ሳምንት ከተማሩ በኂላ የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለመደዉ መንገድ ተምረዉ የድህረ-ትምህረት ፈተና ለተጠኝ ተማሪዎች ከመሰጠቱ በፊት በናሙናነት ካልተካተቱ 12 ተማሪዎች በተራ ዕጣ ንሞና ተመርጠዉ እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ የፈተናዉ አስተማማኝነትም በክሮቮች አልፋ ቀመር ሲለካ/0.766/ ሆኖል ይህም የአስተማማኝነት ልኬታዉ ተገቢ ነዉ ማለት ይቻላል በመሆኑም ፈተናዉ የተጠኝ ተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት ተግባራዊ ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት የድህረ-ትምህርት ፈተና ዉጤት በአጭር ልቦለድ የተማሩት የሙከራ ቡደኑ አማካይ ዉጤት 24.94 በተለመደዉ መንገድ የተማረዉ የቁዋዋር ቡድኑ 17.3 አማካይ ዉጤት አስመዝገበዋል፡፡

በዚህ ፈተና አማካኝነት የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለው አሰተዋጾ ምን እንደሆነ ለማረጋገዋ መረጃው በአማካይ፣በመደበኛ ልይይት፣ በነጻ ናሙና ቲ- ቴስትና በዳግም ልኬት ቲ- ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህም በሙከራ ቡድኑ ድህረትምህርት ፈተና

24.94 አማካይ ውጤትና በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ-ትምህርት ፈተና 17.3 አማካይ ውጤት መካከል 7.64 በልጦ ይታያል፡፡በሙከራ ቡድኑ ቅድመትምህርትና ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ውጤት መካከል በስታቲስቲክስ ($p<0.05$) ጉልህ ልዩነት በመታየቱ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታን እንደሚያጎለብት ለመረዳት ተችሏል፡፡

የጥናቱ ዋና አለማ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለዉን አስተዋጾ መመርመር ነበር፡፡ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ ከመነሻዉ አልቦ እና አማራጭ መላምቶችን ተቀምጧል፡፡አጥኚዋ ይዛ የተነሳችዉ መላምት ከሙከራ ጥናቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑም ሆነ በቁጥጥሩ ቡደድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም (H0=አልቦ መላምት) በሰንጠረዥ 4.1.1.1 እንደተመለከትነዉ የተሰላ የቲዋጋ (0.72) ሲሆን የ "ፒ" ዋጋ (0.943) ሆኖ ታይቷል ይህም በቁጥጥር ቡድኑም ሆነ በሙከራ ቡድኑ የቅድመ-ፈተና ዉጤት ላይ ልዩነት አይታይም በዉጤቱ መሰረት አልቦ መላምቱ አዎንታዊ ምላሽ አስገኝቷል፡፡ከሙከራ ጥናቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑም ሆነ በቁጥጥሩ ቡድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ አይታይም (H0=አልቦ መላምት)

በሰንጠረዥ 4.1.1.2 እንደተመለከትነዉ የተሰላ ቲዋጋ 11.429 ሲሆን የ"ፒ"ዋጋ (0.000) ሆኖ ታይቷል ይህም በሙከራ ቡድኑ እና የቁጥጥር ቡድኑ በድህረ-ትምህረት ፈተና ዉጤት ልዩነት ይታያል በዚህ ዉጤት መሰረት አማራጭ መላምቱ አዎንታዊ ምላሽ አስገኝቷል፡፡ ከሙከራ ጥናቱ በኋላ በሙከራ ቡድኑም ሆነ በቁጥጥሩ ቡድኑ መካከል የችሎታ መበላለጥ ይታይል (H1=አማራጭ መላምት)

በአጠቃላይ የጥናቱ ትንተና ውጤት የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴን መሰረት ያደረገ ቢሆንና ለተማሪዎች የሚቀርቡ ጹፎችም የአጭር ልቦለድ አቀራረብን መሰረት አድርገው ቢዘጋጁ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል ጥናቱ ያመላክታል፡፡

## 5.2 መደምደሚያ

ይህ ጥናት ዋና አላማዉ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ አማርኛ ቋንቋ ማስተማር የአስረኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ክሂልን ለማዳበር የሚኖረዉን አስተዋጾ መመርመር ነበር፡፡ ጥናቱ ያስገኘዉን የመረጃ ትንተና እና የዉጤት ማብራሪያ መነሻ በማድረግ የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ተደርሶል፡፡

የሙከራ ቡድኑ በአጭር ልቦለድ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማሩ በኋላ የአማርኛ ምንባቦችን ወይም ጹሑፎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ መዳበር አማካይ ዉጤት በተለመደዉ የማስተማሪያ ዘዴ ከተማረዉ የቁጥጥር ቡደን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ መዳበር አማካይ ዉጤት ጋር ሲነጻጸር ጨምሮ ታይቷል፡፡ይህም ዉጤት በፈተና በተሰበሰበዉ መረጃ መስረት ማለትም በቅድመ ፈተና እና በድህረ ፈተና የተገኘዉ ዉጤት በአማካይ፣ በመደበኛ ልይይት፣በነጻናሙና ቲ-ቴስት፣በዳግም ልኬት ተሰልቶ የተገኘዉ ዉጤት በአጭር ልቦለድ የማስተማሪያ ዘዴ የተማሩት የሙከራ ቡድኑ ዉጤት በድህረ ፈተናዉ ያስመዘገቡት በልጠ ታይቷል፡፡ ከዚህም የምንረዳዉ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉልህ ድርሻ ያለዉ መሆኑን ያመላክተ ነዉ፡፡ ይህም አጭር ልበለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ ሳቢ፣ናማራኪ በመሆኑ ተማሪዎች እየተዝናኑ የሚማሩበት ከመሆኑ ባሻገር እንዲወያዩ፣እዲከራከሩ፣ሀሳባቸዉን በነጻነት የሚገልጹበት ፣ልብ አንጠልጣይ፣በመሆኑ ተማሪዎች የደራሲዉን ሀሳብ፣መልዕክት ለማግኘት ሙሉትኩረታቸዉን በሚያነቡት ምንባብ ላይእዲያደርጉ ከማስቻሉም በላይ ምናባዊ ምስል እየፈጠረ የጋሀዱን አለም እዉነታን ሰለሚስተዋዉቃቸዉ የማንበብ ተነሳሽነት ፍላጎታቸዉ እንዲጨምር በማድረግ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ ዳብሮ ታይቷል፡፡ ስለዚህ ይህ የማስተማሪያ ዘዴ ተግባር ላይ ቢዉልና በስፋት ቢሰራበት ዉጤታማ ያደርጋል የሚል አንድምታን ያሳያል፡፡

የጥናቱ ውጤትና ማብራሪያ መሰረት በማድረግ የሚከተለው መደምደሚያ ተሰጥቷል፡፡ አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማርን ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉልህ ሚና አለው፡፡ ይህም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር አዎንታዊ ሚና አለው የሚል ነው፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሃሳቦች

በጥናቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚከተሉት የመፍትሄ ሃሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

- የቋንቋ መማሪያ መጽሃፍትን የሚያዘጋጁ ባለሙያዎች የክፍል ደረጃዉን የሚመጥን፣ የተማሪዎችን የዕወቀት ዳራ ያገናዘበ፣ሳቢ፣ማራኪ ተማሪዎችን ለማንበብ የሚያነሳሳ፣ በአጠቃላይ ወደ መማሪያ ክፍል ለማስተማሪያነት የሚዉሉ የስነጹሑፍ መስፈርቶችን ያሟሉ በቂ አጫጭር ልቦለድችን አካቶ ቢያዘጋጁ፡፡
- መምህራን አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ ማስተማር ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር ያለውን አስተዋጾ በመገንዘብ የአጭር ልቦለድ ማስተማሪያ ዘዴን ተጠቅመዉ ቢያስተምሩ፤ ተማሪዎችም በሚያነቡበት ጊዜ ሳቢና ማራኪ በመሆናቸዉ ተነሳሽነትን የሚፈጥሩላቸዉ ከመሆናቸዉም ባሻገር የተማሪዎችን የመረዳት፣ የመተርጎም፣ የመተንበይ፣ጥልቅ ሃሳቦችን የመረዳት፣በምክንያት መልሰ የመስጠት፣እማራዊ እና ፍካራዊ ፍች የማወቅ፣ሚሰጥራዊ የሆኑ ሃሳቦችን የመረዳት አቅማቸዉን የሚያዳብር በመሆኑ ትኩረት ቢሰጠዉ፡፡
- አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴን ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ስልጠና ቢሰጥ፡፡
- በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች መማሪያ መጽሃፍ ውስጥ በምን ያህል መጠን መዘጋጀት እንዳለበት ቀጣይ ጥናት በስፋት ቢካሄድ የተሻለ ሆኖ ሊተገበር ይችላል፡፡
- ትምህርት ቤቶች በቤተ መጻሐፍት ዉስጥ የተማሪዎችን የእዉቀት ዳራ፣ዕድሜ፣እና ሌሎችንም መስፈርቶችን የሚያሟሉ የአጫጭር ልቦለድ መፃሐፍቶችን እንዲኙ ቢያደርጉ የተማሪዎችን የማንበብ አድማሳቸዉን ፣ባህላዊ ዕዉቀታቸዉን፣ ማህበራዊ መስተጋብራቸዉንና የማንበብ ተነሳሽነታቸዉ እንዲጨምር ይረዳል፡፡
- ይህ ጥናት አጭር ልቦለድን ተጠቅሞ የማስተማሪያ ዘዴ በአንብቦ መረዳት ላይ ያለዉን ሚና ብቻ ነዉ ትከረት ያደረገዉ ሌሎች ክሂሎችና ሁለቱ እዉቀቶች ላይ ጥናት ቢደረግ በተማሪዎች ዕዉቀት ላይ ጉልህ ሚና ሊኖረዉ ይችል ይሆናል፡፡
- ለስረዓተ ትምህርት ባለሙያዎች፣ ለመምህረን እና በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ምርምር ለሚያካሂዱ ባለሙያዎች እንደመነሻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

# ዋቢ


Agency, T. E. (2002). *Comprehension instruction.* revised Editoin.

Arigol. (2001). the effect of short stories on students reading comprehension skills. *SAG*.

Atkins. et al ,. (1996). *n skills Development Methdology.* Addis Abeba:: Addis Abeba printing Press.

Bachman. (1999). *Fiction; An introductionto short stories.* Chicago.: NTC Contemperery published group;.

Bintiz, W. (1997). Exploring Reading Night Mares of Middle and Secondary School. *Teacher's Jornal of Adolescent and Adult literary 411, 23-24.*

Brumfit. (1986). *Literature and Language Teaching.* : Oxford University Press.

Carter et al,. (1986). *Literature and Language Teaching.* Oxford New York: Oxford \ Univerisity Press.

Conely, M. (1992). *in Content Reading Instruction Communication Approch.* Mc Graw-Hill inc.

Duff maley et al, . (2005). *Literature in Language Education.* Chicago.

Ghasemi. P. (2011). Teaching L2 Reading Comprehension through Short Story. *journal of readIng Behavior,*.

Graham. (1990). *ontention of Meaningt Reading and The Reac.*

Grellet. (1981). *Teaching literatrure in a second language.* Edinbergh: Edinbergh university press.

hasibuan. (2019). the effect of short stories on the student reading comprehension at madrasah tsanawiyah islamiyah. *SAG*.

Hernandez, J. (2011). The Role of Literature and culture in English Language Teaching. *htt;//relinguistica.azc.no.007/artog.htm.*

Hill, J. (1986). *Using Literature in Language Teaching.* London: : Macmillan Publishers Ltd.

Hismanoglu, e. a. (2005). Teaching English through literature. *Journal of Language and Linguistic Studies,,*.

Hyland, K. (1990). *Purposes and Strategy Teaching Extensive Reading Skills.* English Teachinf Forum XXVIII (2), 14-17.

Hyland, K. (1990). Purposes and Strategy Teaching Extensive Reading Skills. *English Teachinf Forum XXVIII (2), 14-17.*

Jeni, Y. (2020). The Using of Short Stories to Enhance Students' Reading. *Borneo Educational Journal (Borju),, . Vol.02 No. 02.*

Khatib, M and Nasrollahi,A. (2012). enhancing reading comprehension Through shortstories in Iranian EFL learners. *Borneo Educational Journal (Borju), Vol.2,pp.240- 246.*

Kitab, M. (2013). short Story Based Laguage Class room? *International Jornal of Basic Scince and Educational Technology.*

Krashen, S. D. (1982). *Principles and practice in second language acquisition.* New York: .: Prentice-Hall.

Lazar, G. (. (1993). *Literature and Language Teaching.* United kingdom:: CombrIdge university press.

Lumquinga, P. . (2012). he Use of Graphic Organizers to Improve Reading Comprehension Skills With Students of 1-2 Intensive Course ot Espe. *Unpublished Master Thsis, Sangolq Ui Ecuador.*

Madarega et al. (2010). literature and language teaching. *teacher's Jornal of Adolescent and Adult literary*.

Madson, M. (1983). *Teachique in Testing.* New York: : Oxford University Press.

Murdoch. (2002). Exploiting well-known short stories for language skills. *IATEFL LCS SIG Newsletter 23.*

Pettit et al, .. (1997). A factor study of literal reading Comprehension Test and the inferential Reading comprehension Test. *journal of readIng Behavior, VI, 1;ijl sesepub.*

Poorahmadi, M. (2012). Investigating the Efficiency of Task Based Instruction in Improving Reading Comprehension Ability . *. Islamic Azad University.*

Sage, G. (1999). In Incorporating literature in ESL Instruction. *UpperSaddle River: NJ: Prentice Hall.*

Slater, C. a. (1987). *Literature in the language classroom A resource book.* New York.:: Cambridge University press.

Smith,M et al. (n.d.). *Fresh Task on Teaching Literary Elements.* hacettp University dergessis say, .

Turker, et al. (1991). Using Literture in language teaching. *hacettp University dergessis say,.*

William. (1984). *Using Literary texts in Language Teaching.*

Yeasmin, N. (2011). Teaching Language through Literature;Desig Appro Priate classroom Activities. *ASA Universtiy Revew,, vol.5 No.2.*

ታደስ (1952). *ሌላው መንገድ፡ .* አዲስ አበባ: ንግድ ማተሚያ ቤት.

መሰረት. (2007). በአንካሻ ወረዳ በሚገኙ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ክሒል ትምህርት አቀራረብ ቅኝት፡. *ባህር ዳር ዩዩኒቨርሲቲ( ያልታተመ.*

መንግስቱ. (2008). ቋንቋን በአጭር ልቦለድ፣ማስተማርአማርኛ ሁለተኛቋንቋቸዉ ለሆኑ ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለዉን ሚና መፈተሽ. *ጅማ ዩንቨርሲቲ (የማስተርድግሪ የመመረቂያ ጹሑፍ) ያልታተመ.*

ሚኒስቴር, ትምህርት. (1997). *ዘጠነኛ ክፍል የተማሪው መጽሐፍ.* አዲስ አበባ: ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡.

በሪሃና. (2007). *አማርኛ ቋንቋ መምህራን በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ሲያስተምሩ የሚጠቀሙባቸዉ* አህድች መምረጫ መሰረት ፍተሸ. *በህርዳር ዩኒቨርስቲ፡የማስተርስ የመመረቂያ ጽሐፍ) ያልታተመ፡፡. የማስተርስ የመመረቂያ ጽሐፍ) ያልታተመ፡፡.*

ደረጀ (1988). *ህያው ፍቅር.* አዲስ አበባ: ሜጋ ኪነ ጥበባት ማእከል.

በድሉ. (1996). *በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር፡.* አዲስ አበባ:.

ተሾመ. (1997). ከንባታና ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነት፡. *ለድህረ ምረቃ ቴሲስ፣ ባህርዳር*

*ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ).*

ታፈረ. (2000). በዳንግላ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ዳራና የአንብቦ መረዳት ችሎታ፡. *ባር ዳር ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጸሁፍ (ያልታተመ).*

ሀዲስ ( 1958). *ፍቅር እስከመቃብር.* አዲስ አበባ: ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት.

እንድሪስ. (2000). የአንብቦ መረዳት ብላሃቶችን መማር ከአንብቦመረዳት ችሎታ ጋር ያለው ዝምድና. *ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ (የማስተርስ የመመረቂያ ጽሑፍ) ያልታተመ፡፡.*

ዳንአል (1995). *አንድ ገመድ .* አዲስ አበባ: ንግድ ማተሚያ ቤት.

ዳኛቸው (1982). *አደፈርስ.* አዲስ አበባ : ንግድ ማተሚየት ቤት.

ዘመንፈስ. (1991). በስነ-ጽሁፍ አማካኝነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና፡፡. *አድስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡.*

ዘሪሁን. (2007). *የስነጽሑፍ መሰረታዊያን፡፡.* አዲስ አበባ: : ንግድ ማተሚያ ድርጅት.

ያለዉ. (2009). የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር. *ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡.*

# አባሪ

## አባሪ "ሀ "

## የቅድመ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለዉ ሚና በሚል ርዕስ ለተካሄደው ምርምር መረጃ እንዲያስገኝ ለአአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ድህረትምህርት ፈተና ከ(40)፡፡

መለያ ቁጥር--------------------ክፍል----------------------ሴክሽን---------------------

የፈተናው መነሻ ስዓት፡-8፡30

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፡-10፡30

**አጠቃላይ መመሪያ**

ይህ ፈተና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በቀረበው የምንባብ ሀሳብ መሰረት የሚመለሱ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ለያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አስፍሩ፡፡

**ምንባብ**

**ያበዳሪዋ ጫና**

"በጣም ኩሩነህ ስለዚህ ነው ችግር የገለሰሰህ… ግን ምን ታደርግ 'አውራ ዶሮ በየፍት ክምር ላይ ቆም ይጮሃል' … እኔን ተመልከተኝ፤ ለምሳሌ፡- አዎ፣ እግዜር ሞገስን ንጉሡ ነገሥቴ ክብርን አልነሱኝም፡፡ ሆኖም አልኮራም፤ እንዴት ልኮራ እችላለሁ? ማነኝና! ትል ለራሴ! ትንሽ ፍጥረት፣ምናምን! ግን እንደምታየው ራሴን ዝቅ ዝቅ በማድርጌ እግዜርና ንጉሤ ከፍ ከፍ አደረጉኝ በፊታቸው … በሰማያዊ ኃይል የጐለበተ እንዲህ ነው ይኸውልህ… እግዜር ሞገሱን ሰጥቶ በንጉሤ ፊትም ሞገስ እንዳገኝ አደረገኝ…

"… እና አሁን ታዲያ የመጣኸው ትንሽ ዘንጋዳ ለመበደር ነው አልክ…?"

" ነበራ እመየቴ ማስቸገሬ ባይሆን…"

" ለመግዛት ነው የምትፈልገው …?"

" ከየት እቴ እመይቴ ብሩ ከየት ተገኝቶ? በዚያው ባይነት ለመክፍል ነው እንጂ በትሣሥ…"

" ነገር ማሞድሞድ ገንዘብ አይሆንም፤ ይኸውልህ፣ 'ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው፣ ቀንዱ ይከለክለዋል' ነው"

" መቼምኮ የሚሉት ሳይገባኝ ቀርቶ አይደለም… ብቻ እንዲያው ሰኔና ሰኞ…"

" አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምር፤ 'በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አያደምቅ ቢበሉበት አያደቅ…'!"

"ታዲያ ምን ተሻለኝ ይመስልዎታል አሁን…?"

"መከልከሌ አይደለምኮ! 'ሰው ሆኖ የማያስብ እንጨት ሆኖ የማይጨስ'!፣ 'ሰው ከስህተት ብረት ከዝገት…'

"ታዲያ ያሉትን ብለውኝ ብሄድ…"

ብረት ካልፈላ አይላላ' … እንዲህ ልክ ገባህ ይኸውልህ…

"ድሮምኮ ቢሆን … እንዲያው ባንጣጣም ይሆናል…"

"ያለፈው አለፈ፤ አሁን አንድ ልልህ የምፈልገው… ምን ነበር እቴ! አዎ ለሁሉ እግዚአብሔርን…ማለቴ ከሆነ ወዲያ 'ደም ማልቀስ ድንጋይ መንከስ' አያስፈልግም… 'ወረቱን እንደተቀማ ነጋዴ፣ ዋግ እንደመታው ስንዴ' መዋሰስ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም… ያሁኑ ወራት ስህተትህን ማረሚያ ነው፡፡ 'ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ' መሻሉን መገንዘብያህ … እንዲያ ተንገፍባረህብኝ የነበረው ሰውዬ ቢኖረኝ ነው የመጣኸው … 'ተሰካር ያየ ተማሪ ሸቀጥ ያየ አጣሪ…'

"የመሄጃ እጦት ነው እመየቴ…"

"ትዕቢተኛነትህን ትንሽ አብርዶልሃል፤ መቼስ ጨርሶም ባይጠፋ፡፡ አዎ! ለወደፊቱ መንገድ ስንገናኝም ቢሆን ከፊትለፊቴ ሸረር ብለህ መንገዱን ብትለቅልኝ ነውር የለውም፤ አንዳንዴ እንደሚማልግ ነብር እንዳንዴ እየተፍረገረገ እንደሚለማመጥ ድመት መሆን ያስተዛዝባል… አዎ ፊት ማጭገግ ወይም መሰንገጭም በእኔ አይደለም… ከግንባርህ ትህትናን አታጥፋ…

"እመየቴ መቼም ከዚህ በፊት አላስቸገርኩዎትም… "

" እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ…!"

"ታዲያ ታዝኑ…"

"እንዴታ! በርግጥ ታሳዝነኛለህ፤ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ 'እህል ያለው ፈርዛዛ ፣ገንዘብ ያለው ቀበዝባዛ'… የተቻለኝን ባደረግሁልህ… እንደምታውቀው ግን ዘንጋዳው ተወዷል፤ የሚሆንልህ ቢሆን ጥሬው ገንዘብ ይሻለኝ ነበር፡፡ ሳት ሆኗል ዘንጋዳ… እንደ ዘንድሮ ሆኖም አያውቅ… ምን ይመስልሃል ታዲያ…? ደግሞስ ደግሞስ ሰማህ ሆይ፣

መረዳዳትን የመሰለ ምን ዓለም አለ? መረዳዳቱ አይከፋም… ዛሬ ባበድርህ ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልልህ እመጣ ይሆናል…

" ይሆን ይሆን እመየቴ … መቼስ…"

" አይ ይሆናል እንኳ ብዬ አይደለም… "ያልጠረጠረ" ለማለት ያህል ነው… እና ታዲያ አሁን የምትፈልገው አስራ አምስት ቁና መሆኑ ነው…?"

"አዎ እመየቴ ፈቃድዎ ከሆነ…"

" ጥሩ ነው… አስራ አምስት ቁና… ዘጠኝ ቁና እሰጥሃለሁ ማለት ነው፤ በትሣሥ አስራ አምስት አድርገህ ትመልሳለሁ…"

"አይ እኔ እንኳን…"

" እንደምታየው ወለድ አልፈልግም ያው ዓይነት ባይነቱ ነው፣ በብዛት አምርተህ ከምታገባው፡፡ አዎ፣ ብዙ አይደለም፡፡ ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል፤ 'ወዶ የዋጡት ቅልጥም ከፍርምባ ይጥም'

"ትንሽ አልበዛም እመየቴ…?"

"በዛ? አይ እንግዲያው ከበዛ ሌላ ሰው ብትጠይቅ ይሻላል፡፡ እኔ እስከዚህ የምጓጓለት ነገር አይደለም፤ ስላዘኔታዬ ነው የማበድርህ፡- አንተ መጣህብኚ እኔ አልመጣሁብህም…"

"መቼም እመየቴ አዜኔታዎን አልኩ እንጂ…"

"አዘኔታዬ አልተለየህም… ደግሞም ነገር ቢዘበዝቡት ምን ያደርጋል…"

"እርግጥ ነው ብቻ የምመልሰው ትንሽ የበዛ መሰለኝ…"

"አይ፣ አይ፣ አይ፣ እንግዲህ በነገር አትጐሽምጠኝ፡፡ መንግስት ከፈቀደልኝ በላይ የምወስድብህ አራጣ በሊታ ማድርግህ ነው? አጉል ተናገርክ፡፡ እኔ ደሞ ጥንክር ሰው ስትመስለኝ ወስዋሳና ተልካሻ ወጣህ ልበል…?"

"ዋ፣ እመየቴ መቼም ያላቅሚ…"

"ምነው ቢገባህ እኔስ በምን ልኑር ትላለህ? ስንት መሰለህ የሚተኮሰው ጉዳዬ… የየቁረንጮው ግብር ራሴን ሊያዞረው ነው፡፡ በዚህ ላይ የሮማን ሡርግ ደርሷል… የየመነኮሳቱ ድርጐ አለብኝ… ስንቱን ልበልህ… አዎ፣ ባይሆን ለወደፊቱ በየቦታው ከማዘጥዘጥ ጠንከር ብሎ መስራት ይኖርብሃል፡፡ 'ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም…'

"መቼስ ምን ይደረጋል ይሁና ከጨከኑ …"

"ጭካኔ! የምን ጭካኔ? ጭካኔን ምን አመጣው…? አይ አድራጎቴ ጭካኔ ከመሰለህ ብትተወው ይሻላል…"

"ማለቴኮ እመየቴ…"

"ሰማሁኮ ያልከውን…"

"ይሁና እንግዲያው መቼስ ምን አደርጋለሁ…?"

"አዎ! እንዲያ ይሻላል… ዘንድሮ አምናን አይደለም፤ የምታደርገው ነገር የለም… "በነገራችን ላይ እኔ ላንተ አንድ ነገር ስውልልህ ፣ አንተም ለኔ መዋል ሳይኖርብህ አይቀርም… የክርስቲያን ምልክቱ ነው፡፡"

/አደፍርስ፣ ከገጽ8-12

ትዕዛዝ አንድ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛዉን መልስ ምረጥ/ጪ

1.ባይሆን ለወደፊቱ በየቦታው ከማዘዋዘዋ ጠንከር ብሎ መስራት ይኖርብሃል፡፡
ሀ.'ወስፌ ቢለግም ቅቤ አይወጋም… ለ.እንጨት ቢለግም ዉሃ አይወጋም ሐ.ዉሃ ቢለግም መርፌ አይወጋም መ.ዉሃ ቢለግም ቅቤ አይወጋም
2. "አይ፣ አይ፣ አይ፣ እንግዲህ በነገር አትጐሽምጠኝ፡፡ መንግስት ከፈቀደልኝ በላይ የምወስድብህ-------------- በሊታ ማድርግህ ነው?
ሀ.ገንዘብ ለ.እንጀራ ሐ.አራጣ መ.ነገር
3. አጉል ተናገርክ፡፡ እኔ ደሞ ጠንካራ ሰው ስትመስለኝ ወስዋሳና ተልካሻ ወጣህ ልበል…?"
4.በዚህ ላይ የሮማን ሥርግ ደርሷል… የየመነኮሳቱ-------------- አለብኝ… ስንቱን ልበልህ…
ሀ.ብድር ለ .ድርጐ ሐ.ስጦታ መ.እህል
5. ደግሞ በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሰፈርልሃል፤ 'ወዶ የዋጡት ቅልጥም---------------- ይጥም'
ሀ. አጥንት ለ.ጉምድ ስጋ ሐ.ከሻኛ መ. ከፍርምባ
6.'ወረቱን እንደተቀማ ነጋዴ፣------------------------------------ የወንድ ልጅ ተግባር አይደለም… ያሁኑ ወራት ስህተትህን ማረሚያ ነው፡፡ 'ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ' መሻሉን መገንዘብያህ …
ሀ.ዋግ እንደመታው ስንዴ' መዋሰስ ለ.ዋግ እደመታዉ በቆሎ መቀንጠስ ሐ.ዋግ እደመታዉ ገብስ መሽመድመድ መ. ዋግ አደመታዉ ባቄላ መሰበር
7. "አዎ ካጡ ወዲያ ማንኛውም ነገር አያምር፤
ሀ.የቸገረዉ ዱቄት ንፋስ ይጠጋል ለ.አባይ ማደሪያ የለዉ ግንድ ይዞ ይዞራል ሐ.የቸገረዉ እርጉዝ ያገባል መ. 'በሰም የተጣበቀ ጥርስ ቢስቁበት አያደምቅ ቢበሉበት አያደቅ…'!"
8. "በጣም ኩሩነህ ስለዚህ ነው ችግር የገለሰሰህ… ግን ምን ታደርግ --------------በየፍጉ ክምር ላይ ቆም ይጮሃል' …
ሀ. አንበሳ ለ. ድመት ሐ.ነብር መ.አዉራ ዶሮ
9. 'ከዝንጀሮ ጋሜ ያንበሳ መላጣ' መሻሉን መገንዘብያህ … እንዲያ የነበረው ሰውዬ ቢኖረኝ ነው የመጣሽው …
ሀ.ተመጻድቀህ ለ.ተዝናንተህ ሐ.ተቸግረህ መ.ተንገፍገሀብኝ
10."አዘኔታዬ አልተለየህም… ደግሞም ነገር___________ምን ያደርጋል…"
ሀ. ነገር ቢቀዱ ለ. ነገር ቢሰፉ ሐ. ነገር ቢዘበዝቡ መ. ነገር ቢጋግሩ
11. በምንባቡ መሰረት አራጣ ምን ማለት ነው?
ሀ.ብድር ለ.ስጦታ ሐ.ልገሳ መ.ብድርን ከእጥፍ በላይ መክፈል
12. ሰው ሆኖ የማያስብ እንጨት ሆኖ የማይጨስ የለም ለሚለዉ ምሳላዊ ንግግር ተመሳሳይ
ሀ.ከሰውስህተትከብረትዝገት ለ.ላምባልዋለበትኩበትለቀማ
ሐ.የቆጡን አወርድ ብላ የበብብቷን ጣለች መ. እጸድቅ ብዬ ባዝላት

13. አጉል ኩራተኛ ስለሆንህ ችግር ይገለስስሃል፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው? ሀ.ይጎዳሀል ለ. ይወድሃል ሐ.ይጥልሃል መ.ይገጥምሃል

14. ዘንጋዳው በደንብ እየተንቸረፈፈ ይሡፈርልሃል፡፡ የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው? ሀ. ጎደሎ ለ. በድንብ ተሞልቶ ሐ.በድርበቡ መ.በግማሽ

15. በምንባቡ ውስጥ ነገር ወዲያ ወዲህ ሆኖብኝ ነው እንጂ ሲል ምንን ለመግለፅ ፈልጎ ነው?

ሀ. ግራ ተጋብቼ ለ.ተወዛግቤ ሐ.ተረጋግቼ መ.ተረድቼ

16. ባለፈው ዓመት ጤፍ አጨዳ ዋልልኝ ብልህ እንዲያ ተንዠባረህብኝ የሄድኸው ሰውዬ ዛሬ ተመልሰህ መጣህ? የተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍች ምንድን ነው?

ሀ.ኮርተህብኝ ለ. ዘንጠህብኝ ሐ.አክበረኸኝ መ.አንብድደህልኝ

17"እንዴት አዝን ይመስልሃል እንዲህ ተቆራምደህ ሳይ…!"የተሰመረበት ቃል ፊች በምንባቡ መሰረት መልሱ

ሀ.ተደስተህ ለሞልቶልህ ሐ.ተርፎህ መ.ተጎሳቁለህ

18.ብረት_______________አይላላ' ሀ.ካልተጠበሰ ለ.ካልተቀቀለ ሐ.ካልተቆላ መ.ካልፈላ

19. ችግረኛዉ ሰዉዘንጋዳ__________ለማምጣት ነዉ የሄደዉ

ሀ. በስጦታ ለ.በብደር ሐ.በገንብ ለመግዛት መ.ቀምቶ

20.አንበሳ ነዉ፡፡ አማራዊ ፊች ስጡ

ሀ.ገበዝ ለ.ሰነፍ ሐ.ደካማ መ.ብልጥ

**ትዕዛዝ ሁለት ፤በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነዉን እዉነት ትክክል ያልሆነዉን ሀሰት በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልስ ሰጡ**

1.አበዳሪዋ ለተበዳሪዉ ክፉ ደግ ሳይናገሩ ነዉ ያበደሩት፡፡

2.ተበዳሪዉ ዘንጋዳ በአይነታዉ እዲየበድሩት ነዉ የጠየቀዉ፡፡

3.ተበዳሪዉ ለበደር የጠየቀዉ ጤፍ ነዉ፡፡

4. በጣም ኩሩ ነህ ያሉትአበዳሪዋ ሲሞግሱት ነዉ፡፡

5. ለአስራ አምስት ቁና… ዘጠኝ ቁና እሰጥሃለሁ ማለት ነው፤ በትሣሥ አስራ አምስት አድርገህ ትመልሳለሁ…" ሲሉ አበዳሪዋ ያለትርፍ ትመለሰኛለህ ማለታቸዉ ነዉ፡፡

6.ዘንጋደዉ ሳት ሆኖል ሲሉ ተወዷል ማለታቸዉ ነዉ፡፡

7. ከፊትለፊቴ ሸረር ብለህ መንገዱን ብትለቅልኝ ነውር ሲሉ ብታከብረኝ ማለታቸዉ ነዉ፡፡

8. ዛሬ ባበድርህ ነገ ደግሞ እኔ አበድረኝ ልልህ እመጣ ይሆናል ማለታቸዉ ነገ ላይ ማጣታቸዉ አሳስቧቸዉ ነዉ፡፡

9.በምንባቡ ዉስጥ ትቢዕተንነት ማለት መልካምነት ለማለት ተፈልጎ ነዉ፡፡

10.ምንባቡ የሚያወረዉ ታሪክ ስለ ፍቅረኛሞች ነዉ፡፡

**ትዕዛዝ ሶስት፣** በምንባቡ መሰረት በ "ሀ" ስር ያሉትን በ"ለ"; ስር ካሉት ጋር አዛምድ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1.ሰዉ ከስህተት | ሀ.ያንበሳ መላጣ ይሻላል |
| 2.አራጣ | ለ.ብረት ከዝገት |
| 3.ከዝንጀሮ ጋሜ | ሐ.ቀንዱ ይከለክለዋል |
| 4.ለቀንዳም በሬ ቤት አትከልክለው፣ | መ.ወሬ አመላላሽ፣የማይረባ |
| 5. ወስዋሳና ተልካሻ | ሠ.በትርፍ አበዳሪ |
| | ሰ. የበግ መላጣ |

***ትዕዛዝ አራት፡- ከላይ በቀረበው ምንባብ አንብባችሁ ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡***

1. ልቦለዱ በየትኛው የአደራረስ ስልት የተጻፈ ነው?
2. በምንባቡ ውስጥ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው የዘይቤ ዓይነት የትኛው ነው ምሳሌ ጥቀሱ?
3. የመጀመሪያው አንቀፅ የሚያስረዳው ምንን ነው?
4. በምንባቡ ውስጥ የክርስቲያን ምልክት ነው የተባለው ጉዳይ ምንድን ነው?
5. የምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው?

## አባሪ "ለ"

## የድህረትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት፤አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ማስተማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለዉ ሚና በሚል ርዕስ ለተካሄደው ምርምር መረጃ እንዲያስገኝ ለአአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ድህረትምህርት ፈተና ከ(40)፡፡

መለያ ቁጥር--------------------ክፍል----------------------ሴክሽን---------------------

የፈተናው መነሻ ሰዓት፡-8፡30

ለፈተናው የተሰጠው ጊዜ፡-10፡30

**አጠቃላይ መመሪያ**

ይህ ፈተና የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለመለካት የቀረበ ነው፡፡ ጥያቄዎቹ በቀረበው የምንባብ ሀሳብ መሰረት የሚመለሱ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ ምንባቡን በጥንቃቄ በማንበብ ለያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ መስጫ ወረቀት ላይ አስፍሩ፡፡

## ህያዉ ፍቅር

አብነት በአባቷ መኪና ወደ ስራ ስትሄድ ልቧ እንደሰጋ ነበረች፡፡ ትላንት ምሽት አባቷ መኝታቤት ድረስ መጥተው ‹‹ነገ የምንነጋገረው ብርቱ ጉዳይ አለ›› ብለዋታል፡፡

መሀል ፒያሳ ከሚገኘው ትልቅ ህንጻ ስር ደርሰው መኪናይቱ ስትቆም አባቷ ፈጥነው በመውረድ ወደ መግቢያው በር እየተጣደፉ አመሩ፡፡ አብነት ቦርሳዋን አንግታ እጅጌ ጉርድ ሸሚዟን እያስተካከለች ተከተለቻቸው፡፡

ዘወትር እንደምታደርገው ሁሉ ቀና ብላ አንደኛው ፎቅ ላይ በጥቁር መስታወት ላይ በወርቃማ ቀለም የተጻፈውን ማስታወቂያ ተመለከተች፤ ‹‹አብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት››ይላል፡፡ እንደወትሮው የኩራት ስሜት አልተሰማትም፡፡ ሃሳቧ ሁሉ ዛሬ ከአባቷ ጋር በሚፈጠረው ውዝግብ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡

ቢሮዋ በር ላይ ጸሐፊዋ ቅድስት በፈገግታ ተቀብላ አስገባቻት፡፡ ጠበብ ያለችው ቢሮዋ በቆዳ የተለበጠ መጠነኛ ጠረጴዛና ወንበሮች፣የፋይል ካቢኔትና የመጻህፍት መደርደሪያ ይዛለች፡፡ ስትገባ ቀዝቃዛ አየርና አናአና የሚል ሽታ ተቀበላት፤በመስኮቱ ዘልቃ የምትገባው የጥዋት ጸሀይ ገና ሙቀቷን በመርጨት ለቢሮዋ ድምቀትንና ሙቀትን አልቸረቻትም፡፡ አብነት ቦርሳዋን ከጠረጴዛዋ ላይ አስቀምጣ የማሞቂያውን ሶኬት ተከለችና ሻይ አዝዛ ተቀመጠች፡፡

የአብነት መደበኛ ተግባር የድርጅቱን ሂሳብ መከወን ነው፡፡ ትልቁን መዝገብ ጠረጴዛው ላይ ዘርግታ በማቀፊያ ካከማቸቻቸው ሰነዶች ላይ የወጭና የገቢውን ሂሳብ መመዝገብ ጀመረች፡፡ የምትሰራው ሂሳብ የተጭበረበረ መሆኑን ስለምታውቅ በዚያ ቢሮ ውስጥ የምታሳልፈው ጊዜ ሁሌም ይቆጫታል፡፡ እርሷ የምትሰራው ሂሳብ ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው መጠነኛ ትርፍ፣አንዳንድ ጊዜም ኪሳራ ሲሆን፣የድርጅቱ ገቢ ግን ቁጥር ስፍር እንደሌለው ታውቃለች፡፡ አባቷን ስለዚህ ጉዳይ ጠይቃ የተሰጣት መልስ ‹‹አንድ ቀን ትረጅዋለሽ›› የሚል ነበር፡፡ ያ‹‹ቀን››ግን እጅግ ስለራቀባት የተጭበረበረ ሂሳብ ስታገላብጥ የምታቃጥለው ጊዜ ያንገበግባታል፡፡

የዘረጋችውን መዝገብ በንዴት አጥፋ እጆቿን አጣምራ ተቀመጠች፡፡ ጠረጴዛዋ ላይ ያለው ካላንደር ሜይዴይን አስታወሳት፡፡ ሜይደይም ቻርሊን፤ቻርሊም ዛሬ ከአባቷ ጋር የምታደርገውን ውዝግብ፡፡ በሜይዴይ ሰልፍ ላይ ከተካፈለች ወዲህ አባቷ አነጋግረዋት አያውቁም፡፡ ፊታቸውን በጥላቻ እንዳጠቆሩባት ነበሩ፡፡

ስለአባቷ ጭካኔ እንድታስብ የሚያደርጋት አንድ ድርጊት ምን ጊዜም ከህሊናዋ አይጠፋም፡፡

ከሁለት አመታት በፊት፣በድርጅቱ ውስጥ ስራዋን የጀመረች ሰሞን ነው፡፡ አባቷ ቢሮ ውስጥ ተቀምጣ ስለሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስትወያይ፣ የቢሮው በር ተንኳኩቶ አንድ ጎስቋላ ሰው ይገባል፡፡ የለበሰው ሰማያዊ ቱታ እላዩ ላይ ነትቧል፤ ጫማወቹ ተበጣጥሰዋል፤ በተገለጠው ደረቱ ላይ አጥንቶቹ ፈጥጠዋል፡፡ ረዘም ያለ ከሲታ ፊቱ ላይ አይኖቹ በስጋትና በጥርጣሬ ይቁለጨለጫሉ፡፡ በራ ጭንቅላቱ ላይ ደግሞ የደም ስሮቹ ትር ትር ትር ሲሉ ይታያሉ፡፡

አብነት ድንግር ብሏት አንዴ አባቷን፤ መልሳ ጎስቋላውን ሰው ስትመለከት ቆየች፡፡ አባቷ ሰውየውን በዝምታ ከተመለከቱት በኋላ ‹‹ከዚህ በፊት ውሳኔየን አሳውቄሀለሁ አላሳወቅኩህም?›› ሲሉ ተቆጥተው ጠየቁት፡፡

ሰውየው እያጎነበሰ ‹‹ጌታየ…›› ከማለቱ የጀመረውን ሳያስጨርሱት ‹‹የጠየኩህ አጭር ጥያቄ ነው፡፡ አጭር መልስ ብቻ ስጠኝ?›› ሲሉ አፈጠጡበት፡፡

‹‹አሳውቀውኛል ጌታየ…!›› አለ በመርበትበት፡፡ ‹‹ታዲያስ አስራ አምስት ዓመት ሙሉ ድርጅቱ ውስጥ ስትሰራ፣ አንድ ቀን እንኳን ለቃሌ ሳልታመን፣ የተናገርሁትን ሳልፈጽም የቀረሁበት ጊዜ አለ?›› ሲሉ ግንባራቸውን ቋጥረው ጠየቁት፡፡

‹‹የለም ጌታየ!››

‹‹እንግዲያ፣ ከስራ ካሰናበትሁህ በኋላ ምን ልትፈጥር መጣህ?! ማሰብና መጨነቅ የነበረብህ እኮ የድርጅቱን አስር ብር እንኳን የማያወጣ እቃ ለመስረቅ እጆችህን ስትዘረጋ ነበር፡፡ በታታሪና በቅን ሰራተኛነትህ ያላደረኩልህ ነገር አልነበረም፡፡ አስረኛ ክፍል ድረስ ልዩ ወጭ እየሰጠሁ አስተምሬሀለሁ፤ ቤተሰቦችህን እንደቤተሰቤ ቆጥሬ ረድቻቸዋለሁ፡፡ አንተ ግን አስር ብር ለማያወጣ ንብረት ታማኝነትህን አጎደልክ፡፡ አሁን ልወቅስህ አልፈልግም፤ ሁሉን ነገር ጨርሰናል›› አሉና ተሽከርካሪ ወንበራቸውን አዙረው ጀርባቸውን ሰጡት፡፡

ሰውየው እንዳቀረቀረ ‹‹ጌታየ ጥፋተኛ ነኝ!›› አለ፡፡ ‹‹ጥፋተኛነትህን ያወቅከው ዛሬ በመሆኑ በራስህ ልታዝን ይገባል፡፡ ጥፋት ከፈጸሙ በኋላ በጥፋታቸው የሚያዝኑ የዋሆች ናቸው፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ የተሰጠው ክፉውን ከደጉ አመዛዝኖ እንዲለይበት አይደለም?! ወዳጄ፤ በእኔ ህይወት እና በድርጅቴ ውስጥ ለየዋሆች የሚሆን ቦታ የለም!›› አሉት ፊታቸውን እንዳዞሩ፡፡

‹‹ጌታየ ምህረት ያድርጉልኝ?!›› አለ ሰውየው እንባ እየተናነቀው፡፡ አልመለሱለትም ‹‹ ሚስቴ ወልዳ አራስ ቤት ነች፣ ሶስቱ ልጆቼ የሚልሱት የሚቀምሱት ርጋፊ ዱቄት እንኳ የላቸውም፡፡ አይነስውር እናቴ ዛሬ ጠዋት ጠኔ ይዟት ከተኛችበት የቦንዳ አልጋ ላይ አልተነሳችም፡፡ እኔም እራሴ እህል ከቀመስኩ ዛሬ ሶስተኛ ቀኔ ነው.... ስድስት ወር ሙሉ ያለስራ......›› ንግግሩን ሳይጨርስ እንባ ቀደመው፡፡

አብነት እንባዋን እየታገለች አቀረቀረች አባቷ ግን ጆርባቸውን ሳያዞሩ ‹‹እኔ መንገኛ ከደሙ ንጹህ ነኝ፡፡ መሳሳት አልነበረብህም፣ ከተሳሳትክ ደግሞ የስህተትህን ዋጋ በጸጋ መቀበል አለብህ፡፡ አሁን ስራ ስለያዝኩ ቢሮየን ለቀህ ውጣልኝ!›› አሉት በቁጣ፡፡

ሰውየው ፊዞ ባዶ ስሜት ባዘሉ አይኖቹ ጆርባቸውን ሲመለከት ከቆየ በኋላ እንባውን እያባበሰ የቢሮውን በር ከፍቶ ወጣ፡፡

አብነት ራሷን መቆጣጠር አልቻለችም ‹‹ አባባ! ይህንን ምስኪን ይቅርታ አድርገህለት የነዚያን ሁሉ ምስኪን ፍጥረታት ህይወት ብታድንስ?!›› እያለች ማልቀስ ጀመረች፡፡

አባቷም ፊታቸውን ወደ እርሷ መልሰው፣ ‹‹ይቅርታን ማድረግ የሚችል ሩህሩህ ልብ ቢኖረኝ ኖሮ ዛሬ ከደረስኩበት መድረስ ባልቻልኩም ነበር፡፡›› አሏት ሀዘን፣ ቅሬታና ድል አድራጊነት በተሞላበት ትንሽ ፈገግታ፡፡

አብነት በፍጥነት ወጥታ ደረጃውን እየተንደረደረች በመውረድ ሰውየውን ህንጻው መውጫ በር ላይ አስቆመችው፡፡ ተስፋና ጥርጣሬ በተደባለቀባቸው አይኖቹ እየተመለከታት ኪሶቿን ሁሉ እያገላበጠች መፈተሽ ጀመረች ኪሷ ውስጥ ያገኘችው ግን አንዲት የተጣጠፈች ብር እና ሃያ ሳንቲሞች ብቻ ነበር፡፡ ቦርሳዋን ቢሮ ትታዋለች፡፡

ምን እንደምትሰጠው ጨንቋት ስታስብ የሃያ አንደኛውን አመት ልደቷን ስታከብር ከቤተሰቦቿ የተበረከተላትን የወርቅ አምባር እጇ ላይ ተመለከተችው፡፡ አሰበች፡፡ ምርጫ አልነበራትም፡፡ ሳታመነታ አምባሯን አውልቃ ሰጠችው፡፡ ‹‹ይህን ሽጠህ ቤተሰቦችህን መግባቸው ስራ እስክታገኝ ድረስ ምናልባት አትራቡም ይሆናል፡፡››

‹‹ደህና ሁን!›› ብላው ፎቁን መውጣት ስትጀምር ተከትሎ አስቆማትና ‹‹እመቤት፣ አንችን የማመሰግንበት አንደበት የለኝም፡፡ ምን እንደምናገር እንኳን አላውቅም..... እግዚአብሔርን የምለምነው ሰው ሆኜ ውለታሽን የምመልስበትን ቀን እንዲሰጠኝ ብቻ ነው፡፡›› አላት ሳግ ከሚያፍነው ልሳኑ ጋር እየታገለ፡፡

ምንጭ፡-ደረጀ በቀለ (1988) ህያው ፍቅር፡፡ ለፈተና እንዲመች ተሻሽሎ የቀረበ፡፡

መመሪያ፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰርት ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ አብነት ቢሮ ውስጥ የማይገኝ የቱ ነው?

ሀ.በቆዳ የተለበጠ ጠረጴዛ ለ.የፋይል ካቢኔት ሐ.የመጽሃፍ መደርደሪያ መ.ሶፋ ወንበር

2. የአብነት መደበኛ ስራ ምንድን ነው?

ሀ. የድርጅቱን ገቢ ማሳደግ ለ. የድርጅቱን ሂሳብ በትክክል መስራት

ሐ. ሂሳቡን በማስተካከል ትርፉን መጠነኛ ማድረግ መ. ድርጅቱን ከክስረት ማዳን

3. ቢሮ አንኳኩቶ የገባውን ሰው በትክክል የማይገልጸው የቱ ነው?

ሀ.ጫማዎቹ ተበጣጥሰዋል ለ. ረዘም ባለ ጠይም ፊቱ ላይ ውበት ይነበባል

ሐ.በተገለጠው ደረቱ ላይ አጥንቶቹ ፈጥጠዋል መ. በራ ጭንቅላቱ ላይ የደምስሮቹ ትርትር ሲሉ ይታያሉ

4. በእኔ ህይወትና በድርጅቱ ውስጥ ለየዋሆች የሚሆን ቦታ የለም በማለት የተናገረ ማን ነው?

ሀ.አቶ ቻርሊን ለ.አብነት ሐ.አቶ መንገሻ መ.የድርጅቱ ዘበኛ

5. ቢሮ ውስጥ ገብቶ ይቅርታ እንዲያደርጉለት ሃላፊውን የጠየቀው ሰውዬ ከስራ የተባረረው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. በስርቆት ወንጀል ለ. ተገቢ የሆነ የስራ ልምድ ስለሌለው

6. ሐ. የስራ ችሎታ ስለሌለው መ. ታታሪና ቅን ስላልሆነይቅርታ ማድረግ የሚችል ሩህሩህ ልብ ቢኖረኝ ኖሮ ዛሬ ከደረስሁበት መድረስ አልችልም ነበር ማለቱ ምንን ያሳያል?

ሀ. በጥረቱ ያፈራው ሃብት ንብረት መሆኑን ለ. ከቤተሰቦቹ በውርስ ያገኘው መሆኑን

ሐ. በህገወጥ መንገድ ያገኘው ሃብት መሆኑን መ. በእውቀቱ ያፈራው ሃብት መሆኑን

7. አብነት ደረጃውን ወርዳ ሰውየውን ያሥቆመችው ለምን ነበር?

ሀ. አባቷ ይቅርታእንዳደረጉለት ለመግለጽ ለ. አባቷ የላኩትን ገንዘብ ለመስጠት

ሐ. ያላትን የወርቅ አንባር ለመስጠት መ. ሁለተኛ ቢሮ እንዳይመጣ ለማስጠንቀቅ

8. ጠረጴዛላይ ያለው ካላንደር አብነትን በቅደም ተከተል ምን ምን እንድታስታውስ አደረጋት?

ሀ.ሜይደይን--ቻርሊን--ከአባቷ ጋር የምታደርገውን ውይይት

ለ.ከአባቷ ጋር የምታደርገውን ውይይት--ቻርሊን--ሜይደይን

ሐ.ቻርሊን--ሜይደይን--ከአባቷ ጋር የምታደርገውን ውይይት

መ.ሜይደይን--ከአባቷ ጋር የምታደርገውን ውይይት--ቻርሊን

9. ሰውየውን ተሰናብታ ደረጃውን መውጣት ስትጀምር ተከትሎ ያስቆማት ለምን ነበር?

ሀ. ስጦታውን ለመመለስ ለ. ከድርጅቱ ውስጥ እንድታስቀጥረው ለመማጸን

ሐ. ስጦታውን ስለሰጠችው ለማመስገን መ. እንደሚወዳት ለመግለጽ

10. አብነትን አባቷ አነጋግረዋት አያውቁም የተባለው ከመቼ ጀምሮ ነው?

ሀ. ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ ለ. ከሜይደይ ሰልፍ ጀምሮ

ሐ. በድርጅቱ ውስጥ ስራ ከጀመረች ጀምሮ መ. የወርቅ አምባሯን ከሰጠች ጀምሮ

11. ከስራ የተባረረው ሰውየ የሚያስተዳድራቸው የቤተሰብ አባላት ስንት ናቸው?

ሀ. ሰባት ለ. ስድስት ሐ. አምስት መ. አራት

12. የድርጅቱ ሒሳብ በትክክል አለመሰራቱ ይበልጥ የሚጎዳው የትኛውን ነው?

ሀ. ድርጅቱን ለ. መንግስትን ሐ. ቤተሰቡን መ. የድርጅቱን ሰራተኞች

13. አብነት ‹‹አብነት አስመጭና ላኪ ድርጅት›› የሚለውን ስታነብ እንደወትሮው ኩራት ያልተሰማት ለምንድን ነው?

ሀ. ሀሳቧ ሁሉ ከአባቷ ጋር በሚፈጠረው ውዝግብ ላይ ስለነበረ

ለ. ሀሳቧ ከስራ ከተሰናበተው ሰውየ ላይ ስለነበር

ሐ. የድርጅታቸው ክስረት ስላሳሰባት

መ. ሻይ ሳትጠጣ ከቤት ስለወጣች

14. የድርጅቱ ገቢ <u>ስፍር ቁጥር</u> የለውም፡፡ ከሚለው ውስጥ የተሰመረበት አውዳዊ ፍቺ ------------- ነው፡፡

ሀ. በጣም ትንሽ ለ. የተመጠነ ሐ. በርካታ መ. ኢምንት

15. አብነት የዘረጋችውን መዝገብ በንዴት አጥፋ እጆቿን አጣምራ የተቀመጠችው ለምንድን ነው?

ሀ. ጠረጴዛው ላይ ያለውን ካሌንደር ለመመልከት ለ. የተጭበረበረ ሒሳብ መስራቷ ስላናደዳት

ሐ. የድርጅቱ ገቢ አጥጋቢ ባለመሆኑ መ. በድንገት ቻርሊን ስላስታወሰች

16. የአብነት አባት በአብነት ላይ ፊታቸውን ያጠቆሩበት ጉዳይ ምን ነበር?

ሀ. ስራዋን ባለማክበሯ ለ. ከስራ ለተሰናበተው ሰውየ ስጦታ ስለሰጠች

ሐ. በሜይደይ ሰልፍ ላይ ስለተሳተፈች መ. የድርጅቱን ሒሳብ በትክክል ስላልሰራች

17. ለአብነት እጅግ በጣም የራቀባት ቀን የትኛው ነው?

ሀ. ሜይደይ የሚከበርበት ቀን ለ. ስለድርጅታቸው ትክክለኛ አሰራር የምታውቅበት ቀን

ሐ. ስራ የምትለቅበት ቀን መ. ከቻርሊ ጋር የምትገናኝበት ቀን

18. ከስራ የተባረረው ሰውየ ይቅርታ ለመጠየቅ ቢሮ ውስጥ ሲገባ አብነት ምን እያደረገች ነበር?

ሀ. ከአባቷ ጋር ስለድርጅቱ ሒሳብ አያያዝ እየተነጋገረች

ለ. በጠረጴዛው ላይ የሚገኘውን የጊዜ ሰሌዳ እየተመለከተች

ሐ. የድርጅቱን የሒሳብ መዝገብ እያገላበጠች

መ. የማሞቂያውን ሶኬት ሰክታ ሻይ እያዘዘች

19. ከስራ የተባረረው ሰውየ ይቅርታ ለመጠየቅ የመጣው ያለ ስራ ምን ያህል ወራትን ካሳለፈ በኋላ ነው?

ሀ.አራት ለ. አምስት ሐ. ስድስት መ. ሰባት

20. ከስራ የተሰናበተው ሰው አብነትን ያመሰገነበት መንፈስ ምንድን ነው?

ሀ. እውነተኛ ለ. ሽሙጥ ሐ. ቁጭት መ. በተስፋ

**መመሪያ ሁለት የሚከተሉትን ጥያቄዎች እዉነት ሀሰት በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልሰ ስጡ**

21. አብነት ከአባቷ የምትለየው በመልኳ ነው

22. ከስራ የተባረረው ሰውየ በድርጅቱ ውስጥ 20 ዓመት ሰርቷል

23. አብነት በስራዋ በጣም ደስተኛ

24. የአብነት አባት  እጅግ ስቅስቅ ብሎ እንዲያለቅስ ያደረገዉ የአብነት የጭካኔ ተግባር ነዉ፡፡

25. አብነት የምትሰራው ሂሳብ ብዙውን ጊዜ የሚያሳየው ኪሳራ ወይም መጠነኛ ትርፍ ነው፡

26. አብነት ወደቢሮ ስትሄድ የሰጋችበት ምክንያትስዓት አሳልፋ በመግባቷ  ነበር

27.አብነት 21ኛ ዓመት ልደቷን ስታከብር ከቤተሰቦቿ የተበረከተላት የወርቅ አንባር ነበር፡

28.የአቶ መንገሻ ድርጅት የሚገኘው ጎተራ ነው፡፡

29.አብነት ከስራ ለተባረረው ሰውየ ልትረዳው አልፈለገችም ነበር ምንድን ነው፡፡

30.ከአብነት ህሌና የማይጠፋውና ስለአባቷ ጭካኔ እንድታስብ የሚያደርጋት ጉዳይ የተከሰተው ከቀናት በፊት ነበር፡፡

*መመሪያ ሶስት፣ በምንባቡ መሰረት  በ “ሀ” ስር ያሉትን በ”ለ”; ስር ካሉት ጋር አዛምድ*

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. አልቸረቻትም | ሀ.መቁለጭለጭ |
| 2. ኦና | ለ.መፍራት |
| 3. የነተበ | ሐ.ተዘግቶ የቆየ ቤት |
| 4. በራ ጭንቅላት | መ.መላጣ |
| 5. መርበትበት | ሠ.የሳሳ ብንያለ ጸጉር |
| | ረ.መልኩን የቀየረ የሳሳ |
| | ሰ.አልሰጠቻትም |

## መመሪያ-አራት በምንባቡ መሰረት ግልጽ እና  የተብራራ መልሰ ስጡ

1.ህያዉ ፍቅር ማለት ምን ማለት ነዉ በምንባቡ መሰረት አብራሩ

2.ከምንባቡ የተረዳችሁትን በአጭሩ ግለጹ

3.እናተ ለወደፊት እንደ አብነትአባት ነዉ መሆን የምትፈልጉት ወይስ እንደ አብነት ለምን?አብራርታችሁጻፉ

4.በምንባቡ ዉስጥ እኔ መንገሻ ከደሙ ንጹህ ነኝ ሲል ምንማለቱ ነዉ በምንባቡ መሰረት አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

5.ከስራ የተባረረዉ ሰዉ ያጋጠመዉ ምንድ ነዉ አብራርታችሁ ጻፉ

## አባሪ "ሐ"

## አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ለማስተማር የቀረቡ ቴክስቶች

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ  የማስተማር ዘዴ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለውን አስተዋጽኦ ለማወቅ ለሚሰራ የምርምር ጥያቄ አጭር ልቦለድ ተጠቅሞ ለማስተማር የተዘጋጀ የማስተማሪያ ቴክስት

የትምህርት ክፍለ ጊዜያት፡- ሰኞና ሐሙስ /በቀን ለ40 ደቂቃ/

የመማሪያ ክፍል፡- የቲቶሪያል መስጫ ክፍል

ጠቅላላ የትምህርቱ ስዓት፡- 8፡00

### ክፍለ ትምህርት አንድ

የትምህርት ርዕሶች፡

- የጽሁፉን ፍሬ ሃሳብ ተረድተው በራሳቸው አባባል መግለጽ
- ለቃላት እማራዊና ፍካራዊ ፍች መስጠት
- ገጸባህርያቱን በማወዳደር የሃሳባቸውን አንድነትና ልዩነት መለየት
- ያዳመጣችሁትን ፍሬ ሃሳብ ትጽፋላችሁ
- ለአዳዲስ ቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍች መስጠት

ትምህርቱ የሚወስደው ጊዜ ፡- 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

- -የጽሁፉን ፍሬ ሃሳብ ተረድተው በራሳቸው አባባል ይገልጻሉ
- ምንባቡ ውስጥ ያሉ ገጸባህርያት ከጭብጡና ከመዋቅሩ ጋር ያላቸውን ትስስር ይገልጻሉ
- ገጸባህሪያትን በማወዳደር የሃሳባቸውን አንድነትና ልዩነት ይገልጻሉ
- ስለገጸባህርያቱ ተገቢ መረጃዎችን ይሰበስባሉ
- ከምንባቡ ለወጡ አዳዲስ ቃላትና ሃረጋት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. ጋብቻ ምንድን ነው?
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ፈቃደኝነት ላይ ካልተመሰረተ ምን ችግር የሚፈጠር ይመስላችኋል?
3. ስልጣንና ጋብቻ በዘር ሀረግ ቢሆን ኑሮ ምን ሊፈጠር ይችል ነበር?

## ምንባብ

በዛብህ በባሉ ሳመንት ለፊትአውራሪ መሸሻ እጅግ ባለሟል ሆኖ ሳይለይ ሰነበተ፡፡ ከባሉ ውጭ ወደተማሪ ቤቱ ለመመለስ ሲሰናበት፡-

‹‹ ግርግር ሆነና ለብቻ ተገናኝተን አላነጋገርሁህም አገርህ ወዴት ነው?›› አሉት ፊትአውራሪ፡፡

‹‹ አገሬ ማንኩሳ ነው ጌታዩ››አለ በዛብህ፡፡

‹‹ እዚህ አያሌ ለመቆየት ታስባለህ?››

‹‹ እኔ አንድ አመት ለመቆየት አስባለሁ ነገርግን ፈጻሚው እግዚአብሄር ነው፡፡››

‹‹ እዚህ በምትቆይበት ጊዜ ቤታችን ቤትህ ነው፤አትለየን እንዳትሰቀቅ እንኩዋን ላንተ ላንዱ ለብዙ እንሆናለን፡፡›› አሉ ፊታውራሪ መሸሻ ረዥም ጢማቸውን በግራ እጃቸው ወደታች እየላጉ፡፡ በዛብህ እጅ ነስቶ ስለሽልማቱና ስለመስተንግዶውም አመስግኖ ወደተማሪ ቤቱ ሄደ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ለፊታውራሪ መሸሻና ለወይዘሮ ጥሩአይነት ለቤተሰቡም በሙሉ ቤተኛ ሆነ፡፡ ለምሳ ባይሆን ለራት ለራት ባይሆን ለምሳ ከፊትአውራሪ መሸሻ ቤት አይጠፋም አንዳንድ ጊዜም ሳይመጣ ውሎ ያደረ እንደሆን እንደወለዱት ልጅ ተጨንቀው እተማሪ ቤቱ ድረስ ጠያቂ ይልኩ ነበር፡፡

ፊታውራሪ መሸሻ በባላባትነታቸው እጅግ የሚኮሩ መኮንን ነበሩ፡፡ ከትግሬ፣ከሽዋ፣ከጎንደር ነገስታት ጋር ያላቸውን ዝምድና ቁጭ ብለው እንደውዳሴ ማርያም መድገም የጀመሩ እንደሆነ ሰሚ የሚሰለቸው አይመስላቸውም፡፡ እሳቸው እንደሚተርኩት የሆነ እንደሆነ በትግሬም ሆነ በሽዋ ወይም በጎንደር መንገስ ቢቀርባቸው እንኩዋ ቀጥሎ ያለው ቦታ ለሌላ መሰጠቱን እንደየግፍግፍ ይቆጥሩት ነበር፡፡ ነገርግን ምን ይደረጋል በድል እንጂ በትግል የማይገኝ ነገር! ‹‹እኔ መሸሻ፣ እኔ የደፋር ጌታ በዘር ይሁን በሙያ እንኩዋን የሚበልጠኝ የሚተካከለኝ እንደሌለ ማንም ያውቃል፡፡ ዳሩ ምንይሆናል! ሰው በዘሩና በጋሻው የሚመረጥበት ጊዜ አልፎ እነሆ እንደኛ ያለን ሰዎች እዚህ በባላገር ከገበሮችና ከባሮች ጋር ተሰማርተናል!›› ብለው እንደመቆጣት ሲሉ አሽቃባጮቻቸው ‹‹ግዴለም ጌቶች ጊዜ ያልፋል፤ እንዲህ እንደሆን አንቀርም፡፡›› ይሉዋቸውና ወዲያው ይጽናናሉ፡፡

ዘር በመቁጠር ምሽታቸው፤ ወይዘሮ ጥሩአይነትም ከባላቸው ምንም ያክል አይሰንፉም ነበር፡፡ ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩአይነት ሰብለወንጌል የምትባል አንዲት ሴት ልጅ ብቻ ነበረቻቸው፡፡

ሰብለወንጌል ሳትረዝም ሳታጥር፣ ሳትቀጥን ሳትወፍር በመጠኑ የተሰራች ውበት ከደምግባት ተባብረው ያስጌጡዋት እጅግ ያማረባት ልጅ ነበረች፡፡ ከዚህም በላይ ጠባይና ትህትና በሰፊው የታደለች ስለነበረችና በባህርይ ትምክህት የምትጠላ፣ ከወላጆችዋ ፈጽማ የተለየች ነበረች፡፡

ሰብለወንጌል በአስራ አራት አመትዋ በመኩዋንንት ልጆች ወግ ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም፣ መልከማሪያም፣ መልከ እየሱስና መልከ ጊዮርጊስ አወቀች፡፡ ከወይዘሮ ጥሩአይነትም ኩራታቸውንና ግብዝነታቸውን ብቻ ለሳቸው ትታ የቤት ባልትናቸውንና ሌላ መልካም ሙያቸውን ሁሉ ጠንቅቃ ስለተማረች ይህ ይቀራታል የማትባል ሙሉ ነበረች፡፡ ስለዚህ በዲማና ባካባቢው የሚያዉቁዋት ወይም ወሬዋን የሰሙ መኩዋንንት ሁሉ ገና አስራ አንድ አመት ሲሆናት ጀምረው ልጆች የነበሩዋቸው ለልጆቻቸው፣ ልጆች ያልነበሩዋቸው ለዘመዶቻቸው ደጅ ይጠኑ ነበር፡፡ ነገር ግን ወላጆችዋ እንደእሾህ አጥር ዙሪያዋን ከበው እየተከላከሉ ውበትዋ የጠራቸው ጎበዛዝት ሁሉ ጎምዥተው ዳርዳር ሲዞሩ ያች ያማረች፣ የጎመራች የገነት ፍሬ የመበያዋ ወራት አለፈ፡፡

- የንባብ ጊዜ **ጥያቄዎች**
- ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ አድርጋችሁ እስካሁን ካነበባችሁት ምንባብ ምን እንደተረዳችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ?
- ታሪኩንከማንባችዉ በፊት የገመታችሁት ትክክል ሆነ ወይስ አልሆነም?በማስረጃ ግለጹ፡፡
- በልቦለዱ የእሰካሁን ክፍል ምንምን ተነሱ?

ፊታውራሪ መሸሻና ምሽታቸው ወይዘሮ ጥሩአይነት በዘር ያክለናል፣ ይመስለናል የማይሉት ሰው ልጃቸውን ለጋብቻ ሲጠይቅ እንኩዋንስ ሊሰጡ መጠየቃቸውን እንደ ብርቱ ውርደት እየቆጠሩት እጅግ ያዝኑ ነበር፡፡

‹‹ ወየው ጉድ! ጆሮ አልሰማም አይልምኮ እናንተ?›› ይላሉ ፊታውራሪ መሸሻ ከውጭ ሲገቡ፡፡

‹‹ ዛሬ ደግሞ ምን ሰሙ ጌታየ?›› ይላሉ ባለቤታቸው ወይዘሮ ጥሩአይነት፡፡

‹‹ ቀኛዝማች እገሌ ሰብለወንጌልን ለልጁ ለመነኝ››

‹‹ ቀኛዝማች እገሌ የማን ልጅ ነው?››

‹‹ አባቱን እንኩዋን እኔ እሱም አያውቀው፡፡››

‹‹ ትልቅ ድፍረት!›› ይላሉ ወይዘሮ ጥሩአይነት፡፡

‹‹ ግራዝማች እገሌ ልጅህን ስጠኝ አለኝኮ ጥሩ››

‹‹ የማን ልጅ ነው ጌታየ?››

‹‹ አባቱ ሰው አይደለም ገበሬ ነው፡፡››

‹‹ ይህን ሳልሰማ በሞትሁ!››

‹‹ ፊታውራሪ እገሌ ልጄን ለልጁ ለመነኝ››

‹‹ የማን ልጅ ነው?››

‹‹ አባቱ መጫኛ ነካሽ ነጋዴ ነበር፡፡››

‹‹ ምነው ከምታሰድበን ባልተወለደች፡፡››

‹‹ ባላምበራስ እገሌ ልጅህን ስጠኝ ብሎ አማላጅ ላከብኝኮ ሀ . . ሀ . . ሀ . ወይ ጊዜ !››

‹‹ የማን ልጅ ነው?››

‹‹ አባቱ ብዙ ላም የነበረው ባለጌ ባላገር ነበር እሱ ሲሞት ላሙን ሁሉ አውርሶት ሞተ፡፡ አሁን አገዋቱን በፋጋ እዬጠጣ ሆዱ ሲነፋ ጊዜ ከሰው እኩል የሆነ መስሎት ይሄዋ የኛን ልጅ ይለምን ጀመር!››

‹‹ ይበለን፤ ኸረ ይበለን ሲያንሰን ነው፤ ሲያንሰን ነው፤ ለቀን ሰው ወዳለበት እንዳንሄድ እንደ ታሰርን ሁሉ

ይህን አገር መልቀቅ አቅቶን የባላገር መጫወቻ ሆን፡፡›› ይላሉ ወይዘሮ ጥሩዓነት እንባ እዬተናነቃቸው

‹‹አይ ያንች ነገር ሰው ወዳለበት የምትይ ዛሬ የሰው ምርት አልቆ ግርዱ በቀረበት ዘመን ምን ሰው አለ? የትም ብትሄጂ ቢበዛ አባት እንጂ አያት ያለው ሰው ይገኝ መሰለሽ?››

‹‹እንዴት?››

‹‹እንዴትማ እንደምታውቂው አንዱ እህሉን፣ አንዱ ጥጡን፣ አንዱ ቅቤውን፣ አንዱ ቆዳውን ሸጦ ጉቦ እየሰጠ ባላምበራስ፣ ግራዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪ ይባልና ልጁ የባላምባራስ እገሌ፣ የግራዝማች እገሌ፣ የቀኛዝማች እገሌ፣ የፊታውራሪ እገሌ ልጅ ይባላል፡፡ የሳውቅዮሽ የጨዋታ ቀኛዝማች ግራዝማች! እዚህኮ እኛ ግቢ የነሰጠኝና የነአረሩ ልጆች ፊታውራሪ፣ ቀኛዝማች፣ ግራዝማች እየተባባልን እንጫወት እንደሚሉት ያለ ነው!፡፡ ከአጥንትና ከደም ያልተወረሰ በጥጥና በቆዳ የተገዛ ፊታውራሪነት፣ ቀኛዝማችነት፡፡ ሆሆ! ኸረ ምን ዘመን መጣብን? ይሄውልሽ የነዚህ ልጆች ናቸው የኛን ልጅ ለማግባት የሚጠይቁ! እንዲህ ያሉት ልጆች እድሜ ለቆዳ፣ እድሜ ለጥጥ አባቶቻቸው ግራዝማች፣ ቀኛዝማች እንዳንዶችም እንደኛ ፊታውራሪ ተብለውላቸዋል፤ አያት ግን የላቸውም፡፡ ታዲያ ለነዚህ ልጄን ልስጥ? የእሌኒን፣ የገላውዴዎስን፣ የሱስንዮስን ልጅ ለገበሬ ነጋዴ

ልስጥ? እነሱ ባያዩ፣ ባይሰሙ አጥንታቸው አይከሰኝም? አይወቅሰኝም?›› ይላሉ ፊታውራሪ መሸሻ በቁጣ ደማቸው ፈልቶ ራሳቸውን እየነቀነቁ፡፡

‹‹ እርስዎም ልስጥ ቢሉ እኔን መቃብር ሳይጫነኝ ልጀ አጥንተ ሰባራ አታገባም! እንዲያውም አላቻዋ አግብታ ዘር ከምታበላሽ የሚያክላት የሚመስላት አጥታ ሳታገባ ቀረች ብትባል ክብርዋን ይጨምረዋል እንጂ አይቀንሰውም፡፡››

*ምንጭ፡- ሐዲስ አለማየሁ (1958፡ 83-87) ፍቅር እስከ መቃብር*

***መመሪያ አንድ፣ ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት በምክንያት አስደግፋችሁ መልሱ፡፡***

1. እኔን መቃብር ሳይጫነኝ ልጀ አጥንተ ሰባራ አታገባም በማለት የተናገሩት ወይዘሮ ጥሩአይነት ናቸው፡፡
2. ፊት አውራሪ መሸሻ በባላባትነታቸው እጅግ የሚኮሩ መኮነን ነበሩ፡፡
3. ይህንን አገር መልቀቅ አቅቶን የባላገር መጫወቻ ሆን ያለች ሰብለወንጌል ናት፡፡
4. ለምሳ ባይሆን ለራት ለራት ባይሆን ለምሳ ከፊት አውራሪ መሸሻ ቤት አይጠፉም የተባለው በዛብህ ነው፡፡

5.ሰብለ ወንጌል ከወይዘሮ ጥሩአይነት የወረሰችው ኩራታቸውንና ግብዝነታቸውን ነው፡፡

***መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ ዓ/ነገር ስሩባቸው፡፡***

1. አያሌ
2. ግብዝ
3. ትምክት
4. ጎመገ
5. ፋጋ

***መመሪያ ሶስት ፡-በሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡***

1. እንደምንባቡ ያጋመረችና ያማረች የገነት ፍሬ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. እንደ ፊታውራሪ መሸሻ አስተሳሰብ በባላገር ከገበሮችና ከበሮች ጋር ተሰማርተው የሚኖሩበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ወይዘሮ ጥሩአይነትና ፊታውራሪ መሸሻ የሚመሳሰሉት በምንድን ነው? የሚለያዩትስ?
4. ሰብለዎንጌል ከቤተሰቦቿ የምትለየው በምንድን ነው?

**መመሪያ አራት፡- ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ የምንባቡን ሃሳብ መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. ፊታውራሪ መሸሻ እጅግ የሚኮሩት በምንድን ነው?

   ሀ. በሐብታቸው ለ. በባላባትነታቸው ሐ. በሐገራቸው መ. በልጃቸው

2. ሳትረዝም ሳታጥር፣ ሳትቀጥን ሳትወፍር በመጠኑ የተሰራች ውበት ከደምግባት ተባብረው ያስጌጡዋት ማንን ነው ?

   ሀ. ወይዘሮ ጥሩአይነትን ለ ሰብለወንጌልን ሐ. ሐብትሽን መ. አረሩን

3. ሰብለወንጌል በመኳንንት ልጆች ወግ ውዳሴ ማርያምና መልከጊዮርጊስ ያወቀች በስንት አመቷ ነው? ሀ. በአስራ ሶስት ለ. በአስራ አንድ ሐ. በአስራ ሁለት መ. በአስራ አራት

4. ፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩአይነት ልጃቸውን ለጋብቻ ሲጠየቁ እንደውርደት ቆጥረው እጅግ የሚያዝኑት ማን ሲጠይቃቸው ነው? ሀ. በእድሜ አቻዋ ያልሆነ ሰው ለ. በዘር ያክለናል ብለው የማይሉት ሰው ሐ. ሐብት የሌለው ሰው መ. መልከ ጥፉ የሆነ ሰው

5. በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ምንድን ነው?

   ሀ. ጋብቻ በዘር ሀረግ መሆን እንዳለበት ለ. ያላቻ ጋብቻ መቆም እንዳለበት ሐ. ሰዎች የፈለጉትን ማግባት እንዳለባቸው መ. ጋብቻ በተጋቢዎች ፍላጎት እንደሚወሰን

6. ፊታውራሪ መሸሻ ‹‹እንኩዋን የሚበልጠኝ የሚተካከለኝ የለም›› ያሉት በምንድን ነው?

   ሀ. በሀብት ለ. በዘር ሐ. በመልክ መ. በእድሜ

7. ሰብለወንጌልን ገና በአስራ አንድ ዓመቷ ጀምረው ልጆች የነበሩዋቸው ለልጆቻቸው ያልነበሩዋቸው ደግሞ ለዘመዶቻቸው ደጅ ይጠኑ የነበረው ለምንድን ነው ?

   ሀ. ሰብለም እንደወይዘሮ ጥሩአይነት ኩሩ ስለነበረች

   ለ. ሰብለ እጅግ ውብ ስለነበረችና በትህትና የታደለች ስለነበረች

   ሐ. ሰብለ የተማረችና እጅግም ባለሙያ የነበረች ስለነበረ

   መ. ለና ሐ መልስ ናቸው

8. ፊታውራሪ መሸሻ ‹‹ቢበዛ አባት እንጂ አያት ያለው ባላምበራስ፣ ግራዝማች፣ ቀኛዝማች፣ ፊታውራሪ አይገኝም›› ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. አብዛኞቹ ማረጉን ያገኙት በጉቦ ስለሆነ ለ. አብዛኞቹ ማረጉን ያገኙት በዘር ሀረግ ስለሆነ ሐ. አብዛኞቹ ማረጉን የሚያገኙት በጦርነት ስለሆነ መ. አብዛኝኞቹ ማረጉን ያገኙት በእድሜ ስለሆነ

9. ፊታውራሪ መሸሻ ምን አይነት ሰው ናቸው?

ሀ.ውሐ ቀጠነ ብለው የማይከራከሩ ለ. ከእኔ በላይ ሰው የለም ብለው የሚያስቡ

ሐ. በትህትና የተሞሉ ቅን ሰው መ. ሰርተው የሚያሰሩ በሰው ዘንድ የሚወደዱ

10. እንደ ምንባቡ ከሚከተሉት አንዱ ትክክል አይደለም፡፡

ሀ. አጥንተ ሰባራ አግብቶ ዘር ከማበላሸት ይልቅስ የሚያክለው አጥቶ ቀረ መባል የተሻለ ክብር አለው፡፡

ለ. የዘመኑ መሳፍንት በአብዛኛው ስልጣን የያዙት በጉቦ ነው፡፡

ሐ. ወይዘሮ ጥሩአይነት የፊታውራሪ መሸሻን ያህል ሐረግ የመምዘዝ ፍላጎት የላቸውም፡ ፡

መ. በዛብህ ከበዓሉ በኋላ የነፊታውራሪ መሸሻና ወይዘሮ ጥሩአይነት ቤተኛ ሆኖ ነበር፡፡

**መመሪያ አምስት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡**

1. ተገቢ መረጃዎችን በመሰብሰብ የሰብለወንጌልን ተክለሰውነት ግለጹ?
2. ከምንባቡ የተረዳችሁትን መልክት ባጭሩ ግለጹ?
3. የፊት አውራሪ መሸሻ አመለካከት ተገቢነው? ወይስ አይደለም? ለምን?

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡- ፍቅር እስከ መቃብር

ግምገማ፡- የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መልስ መገምገም

-የግል ስራዎችን ማረም

-የቡድን ስራዎችን መገምገም

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

የትምህርቱ ርዕስ፡- - ስለገጸባህርያት እንቅስቃሴና አመለካከት በአዕምሮ ምስል መፍጠር

-እማራዊ እና ፍካረዊ ፊች መስጠት

- የገጸባህርያትን መልክ፣ጸባይና ባህርይ መለየት

- ያነበቡትን ምንባብ ጭብጥ በአጭሩ መግለጽ

- - ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት

ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ፡- 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ክፍለጊዜ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

-ስለገጸባህርያት እንቅስቃሴና አመለካከት በአዕምሯቸው የሚፈጠረውን ምስልይገልጻሉ፡፡

-የገጸባህርያትን መልክ፣ጸባይና ባህርይ ይለያሉ፡

-ያነበቡትን ምንባብ ጭብጥ በአጭሩ ይገልጻሉ፡፡
-ለቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

1. እውነት ተደብቆ የሚቀር ይመስላችኋል?

2. በጣም የምትወዱት ጓደኛችሁ ዋሽቷችሁ ብታገኙት ምን ታደርጋላችሁ?

3. በጓደኞች መካከል በግልጽ መነጋገር ከሌለ ምን ሊፈጠር የሚችል ይመስላችኋል?

**ምንባብ**

በጣም ቆንጆ ነበረች፡፡ ሰዎች ስለአይኖቿ፣ስለጥርሶቿ፣ስለከንፈሮቿ፣ስለባቶቿ፣ስለዳሌዋ፣ በጠቅላላው ስለደም ግባቷ ይነጋገሩበት ነበር፡፡ እድሜዋ አስራ ስምንት ዓመት፣ቁመቷ ደልዳላ ነበር፡፡ ልብሶቿ ደግሞ በከፍተኛ ሞዴል የሚሰፉ ነበሩ፡፡ ስሟም አልማዝ ደምሴ ይባል ነበር፡፡

አባትየው አቶ ደምሴ አበበ፣ጠይም ደግሞም በጣም ወፍራም ሰውነታቸው ከብዷቸው፣ ሲተነፍሱ ኩንታል ተጭና አቀበት እንደምትወጣ አህያ የሚያቃስቱ ላባቸው ደግሞ እንዲሁ ከሜዳ ደርሶ በአንድ በኩል ቢሉት በአንድ እያመለጠ የሚንርፍባቸው ሰው ነበሩ፡፡ አቶ ደምሴ ሞልቶ የተረፋቸው ጌታ ነበሩ፤ በማነኛውም ስዓት እያቃሰቱ ከየትኛውም ኪስ ሲገቡ እጃቸው መዞት የሚወጣው ገንዘብ የአስር የሃምሳ ደግሞም የመቶብር ኖት ብቻ ነበር፡፡ አልማዝ ሃያ ብር ስትጠይቅ የምትሰጠው ሃምሳ፣ስልሳአምስት ስትጠይቅ መቶብር ነበር፡፡

የታሪካችን አንዱ ሌላው ጎልማሳ አድማሱ አየለ ግን ከትምህርት ቤት ስራ ሊይዝ በወጣበት ጊዜ ወር እስኪደርስ የሚጠጋበት የወላጆቹ ፍቅርና የዘመድ ቤት አልነበረውም፡፡

አባቱ አቶ አየለ የሞቱት እሱ ገና የአራት ዓመት ህጻን ሳለ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ አድማሱ እንዲህ ቀላል ልጅ አልነበረም እርግጥ ከትምህርት ቤት ሲወጣ ኑሮ ጭንቅ ሁኖበት ነበር፡፡ ግን እያደር ሁሉንም በቶሎ ተላመደው፡፡ ስራ በያዘ በሁለት ዓመቱ ጥርሱን ነክሶ ገንዘብ በመቆጠብ ቤትና መኪና ገዛ፡፡ ከዚህ በላይ ደግሞ በስራውና በግብረገብነቱ በአላፊዎች ዘንድ በጣም የተመሰገነና ሁልጊዜም ለከፍተኛ ደረጃ የሚታጭ ነበር፡፡

ለአንድ መልከ መልካም ኑሮውእንደዚህ ለተቃናለት ጎልማሳ ደግሞ የስመለከተው ደጉ ነገር በልጅነት በህግ አግብቶ ወንድም ወይም እህት ከአብራኩ ማድረስ ነበር፡፡ አድማሱ አንድ ቀን ከስራው በአስራ ሁለት ስዓት ወጥቶ በመኪናው ወደቤቱ ሲሄድ አልማዝን ከራስ መኮነን ድልድይ ወደሳባ ደረጃ ስታቋርጥ አገኛት፡፡

በአንድ ጊዜም ልቡ ስንጥቅ አለበት፡፡ ደም ግባቷና አቋምዋ ማረከው፡፡ መኪናውን ወደ አንድ ጥግ ቦታ አቁሞ ቤቷን የዚያኑ እለት ኋላ ኋላዋ ተከትሎ ሂዶ አየው፡፡ ማታውንም የፍቅር ደብዳቤ ጽፎ አድሮ ጧት ከቤቷ ስትወጣ ተጠባብቆ ሰጣት፡፡ በወርም ውስጥ የከንፈር ዎዳጆችም ሆኑ፡፡ ወደሽርሽር ቦታዎች በየሳምንቱ ይዟት ይሄድ፣ደግሞም ብዙ ለመታሰቢያ የሚሆኑ ነገሮች ይገዛላት ጀመር፡፡ አገባታለሁ ብሎ በቆረጠም ጊዜ ለወዳጆቹ ሁሉ ያስተዋውቃት ደግሞም ስለሷበሰፊው ያወራላቸው ጀመር፡፡ ነገር ግን አንድአንድ በጣም ወዳጆቹ የሆኑ ሰዎች አድማሱ ከአልማዝ ጋር በመተዋወቁ አልተደሰቱም ነበር፡፡ ምክንያቱም በጣም ቀረብ ብለው የሚያውቋት ሰዎች በአልማዝ ላይ ብዙ ነውር ነገር ያወሩባት ነበር፡፡ መጥፎ ልጅ ነች ከየግብዣው አትታጣም ብዙ የከንፈር ወዳጆች አሏት፡፡ እሷ ግን ከሁሉም አብልጣ የምትወደው ተሰማ የሚባለውን ልጅ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ይህንኑ ለአድማሱ አምጥተው ይነግሩት ነበር፡፡ ከነዚህም ሰዎች መሀል አንዱ ደበበ የተባለው የአድማሱ የቅርብ ጓደኛው ነበር፡፡ አንድ ቀን ሁለቱ አድማሱና ደበበ ከቤት ቁጭ ብለው ሲጨዋወቱ ከጭዋታ የተነሳ ደበበ ብድግ አድርጎ ፡-

‹‹አድማሱ ስማኝ ይች ልጅ ትቅርብህ፡፡ እርግጥ ነው ቆንጆ ናት፡፡አባቷም ሀብታም ናቸው፡፡ነገር ግን እሷ የምታመጣልህ ሀብት ደግሞ መልኳም ቢሆን ምንም አያደርግልህም፡፡ ነግሬሀለሁ ኋላ ትጸጸታለህ፡፡ እሷ ለራሷ በጣም የምትወደው ተሰማ የተባለ የከንፍር ወዳጅ አላት አሉ፡፡››አለው፡፡

አድማሱ መጀመሪያ ዝም ብሎ ደበበን ሲያዳምጠው ቆይቶ በኋላ እሱም በበኩሉ ብድግ ብሎ እየተንጎራደደ‹‹ሀሰት ነው ደበበ አትስማ፣የሰው ወሬ ነው እሷ የምትወደው እኔን ብቻ ነው፡፡ ደግሞም መጀመሪያውኑ እንደተዋወቅን ጊዜያት ሌላ የጠየቃት ወይም እሷ የምትወደው ልጅ ድንገት እንዳለ ብየ ጠይቂያታለሁ፡፡ነገር ግን አንድም ሰው የለኝም ብላኛለች፡፡››አለው፡፡

ደበበም ባለመስማማት አኳኋን እራሱን እያከከ ‹‹እሷ ምናሞኝነውና አለኝ ትልሃለች››አለው፡፡‹‹በግድ አልያዝኋት ለምን አትለኝም ደግሞም እውነቱን ባትነግረኝም እሱን እግዚአብሄር ይወቀው፡፡ እኔ ግን የምወዳትን ለጋብቻም የማስባትን ልጅ የምትነግረኝን ሁሉ ማመን አለብኝ፡፡››

‹‹እንግዲህ አንተ!እሷፈጽማ ከቃሌ ወጥታ አታውቅም፡፡ ደግሞም አትወጣም፣ተሰማ የሚባልም የከንፈር ወዳጅ ውሸት ነው የላትም …አይደለም የምትለው››ብሎ ጠየቀው፡፡

‹‹አዎ፡፡››

‹‹እሽ፡፡ እሱ እንዳልክ ይሁን፡፡ ነገር ግን እኔ አንድ ነገር እንድታደርግልኝ ብጠይቅህ ለኔ ስትል ታደርግልኛለህ?››አድማሱም አይሆንም በማለት ሊያስቀይመው ስላልፈለገ የጠየቀውን ነገር ሊፈጽም ‹‹እሽ አደርጋለሁ››አለው፡፡

‹‹የፊታችን ቅዳሜ የነአልማዝ ትምህርት ቤት የዳንስ ቀን ነው፡፡ የሚደረገውም በእቴጌ ሆቴል ነው፡፡››

አድማሱ ተገርሞ፡-‹‹አወ ነግራኛለች፡፡ግን አንተ እንዴት አወቅህ? ››ብሎ ጠየቀው፡፡

‹‹ግድ የለህም እሱን፡፡የነገረችህ እዚያ አብራችሁ እንድትሄዱ ነው?››

‹‹አዎን ብቻ እኔ ገና አልቆረጥሁም፡፡››

‹‹ደግ እንግዲያውስ አትሂድ፡፡ እሷንም አትሂጅ በላት፡፡››

‹‹ለምን?››

ልነግርህ አይደለም፡፡ እሷን አትሂጅ ካልሀት በኋላ አንተ ማታውኑ እቴጌ ሆቴል ሄደህ እበሩ አጠገብ ተደብቀህ ጠብቃት፡፡ምን አለ በለኝ አድማሱ ሀሰት ቢሆን፡፡እሷን እዚያው ተሰማ ከሚባለው ልጅ ጋር ስትገባ ታገኛታለህ፡፡

አድማሱ በዚህ ጊዜ ደበበ አልማዝ ላይ ስላለው ዝቅተኛ ግምት በጣም አዘነ፡፡ ሆኖም ቃል ገብቶለት ነበርና እንዳለው አደረገ፡፡ አልማዝ ግን ከዚያሁሉአዳራሹ በየደቂቃው በበሩ እየተቀበለ ከሚያስገባው አጀብ ከአንዱም ዘንድ አልነበረችም፡፡ከምሽቱ አራት ስዓት ሲሆን የደስታው ተካፋይዎች መምጣትን ፈጽመው እንዳቆሙ አድማሱ ተነስቶወደቤቱ ሄደ፡፡ ደበበንም ሰምቶአልማዝን በመጠርጠሩ ሌሊቱን በሞላ ሲያዝን አደረ፡፡ በበነጋው ጥዋት አድማሱ ከመኝታው ሳይነሳ በር ተንኳኳ ያንኳኳውም ደበበ ነበረ፡፡ እንደገባም አድማሱን፡-

***ደበበ አድማሱን ይህንን ያህል የሚወተውተው ለምን ይመሰስላችኋል?**

***አድማሱ የደበበን ሃሳብ ተቀብሎ እቴጌ ሆቴል ሂዶ ተደብቆ ማየት አለበት ብላችሁ ታምናላችሁ?ለምን?**

***አድማሱ አልማዝን ከተሰማ ጋር ቢያገኛት ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?**

***ከቀሪው የምንባብ ክፍል ምን ትጠብቃላችሁ?**

‹‹ታዲያስ!ትላንት ማታ ሂደህ ነበር ወይ!››ብሎ ጠየቀው፡፡

አድማሱም ረጋ ብሎ፡-‹‹አዎ ሂጀነበር፤ነገር ግን አንተ እንዳልከው አልማዝ እዚያ አልመጣችም››አለው፡፡

ደበበ ግን በማንጓጠጥ አኳኋን አፉን ገጥሞ አፍንጫውን ነፋ አድርጎ ‹‹አልማዝ ትላንትና ማታ እዚያ ነበረች አለው፡፡››

አድማሱ በዚህ ጊዜ ደሙ ፈላ፡፡ ያንቀጠቅጠውም ጀመር፡፡

‹‹ውሸታም ነህ!፡፡እኔ ይህንኑ ፈርቼ ከምሽቱ እስከ አራት ሰዓት ተሩብ እዚያው ነበረሁ፡፡ እንግዲህ አጭሩን ልንገርህ ስማ፡፡ አልማዝ አንተ እንደምታስባት አይደለችም ደግሞም እዚያ አልነበረችም››አለው፡፡

‹‹ነበረች አልሁህ፡፡››

‹‹አድማሱም እንደዚያው አይኖቹ በንዴት ደም እንደለበሱ ሆኖ፡፡››

‹‹ዝም በለኝ አንተ ሰው፡፡ በቅቶኛል የአንተ ንግግር፡፡››አለው፡፡

ደበበ ግን ምንም ቅር ሳይሰኝ ቀጠል አድርጎ፡-

‹‹ሦስት ሰዓት ከሩብ ላይ አንዲት ሴት ልጅ ረዥም የተንዘረፈፈና ኩፍ ያለቀሚስ ለብሳ ጥቁር የጌጥ ባርኔጣ አድርጋ ፊቷን ከባርኔጣው ዙሪያ በተዘረፈፈው ጥቁር ዓይነእርግብ ሸፍና የአንድ ጥቁር ሱፍ ከላይ እስከታች የለበሰ ረዘም ያለ መልከ ቀና ወጣት ክንድ እቅፍ ስትገባ አላየህም?››ብሎ ጠየቀው፡፡

አድማሱም ይችን ደበበ የገለጻትን ልጅ አይቷት ነበር፡፡ማየቱን ሊገልጽለት ፊቱን መለስ አደረገ፡፡

‹‹ይኸውልህ እሷልጅ አልማዝ ነበረች፡፡እኔም ይኸው ይፈጠራል ብየ በማሰብ ከአዳራሹውስጥ ገብቼተደብቄ እጠባበቅ ነበር፡፡አይነእርግቡንና ቆቡን ስታነሳ ለየኋት፡፡ ክንዱንም ያቀፈችው ልጅ ተሰማ የተባለው ነው፡፡››

አድማሱ ምንም ሳይል ወደ በሩ ተነስቶሄዶ መዚጊያውን ከፍቶ ደበበን ‹‹ከቤቴ ውጣልኝ ይህንን ጊዜ የምትተበትበው ማን ያውቃል ከኔጋር አጣልተህ አንተ ልታገባት አቅደህ ይሆናል፡፡››አለው፡፡

‹‹እኔ!››

‹‹አዎ አንተ፡፡››

‹‹አድማሱ እንደዚህ አልክ!››

‹‹አዎ አለኩ፡፡››

ከዚያ በኋላ አድማሱና ደበበ ተቆራረጡ፡፡ የሰርጉ ዝግጅት በሁለቱም ቤት ተጧጡፎ ቀጥሎ ሳለ አልማዝ አንድቀን ጧት እቤቷ ከማድቤት ወደአዳራሽ ስታልፍ አደናቅፏት ወድቃ በጣም ታመመች፡፡ ሀኪም ቤት ቢወስዷት ትርፍ አንጀት ነው ተባለ፡፡ በዚህ ጊዜ ለሰርጋቸው የቀረው ሃያ አንድ ቀን ብቻ ነበር፡፡ነገርግን የግድ ከሰርጋቸው በፊት አልማዝ ሆዷን የምትቀደድ ሆነች፣እሷም በጣም ፈርታ ነበር፡፡ አድማሱም አይዞሽ አትፍሪ

ቀላልነው፡፡ እሩቅ ሳትሂጅ እኔ እራሴ የዛሬ ስድስት ዓመት ተቀድጄ ነበር እይው ጤናማ ሁኘእስካሁን አለሁ፡፡ እርግጥ እንደተቀደድሽ ለሃያና ለሰላሳ ደቂቃዎች ያህል እራስሽን ሳታውቂ ትቃዣለሽ፡፡ እኔ ለምሳሌ በተቀደድሁበት ጊዜ ከትምህርት ቤታችን አንደኛ ቡድን ኳስ ተጫዋቾች አንዱ ነበርኩ፡፡ ልቀደድ በተኛሁበት ሳምንት ታዲያ የኛ ቡድንና የአንድ ሌላ ትምህርት ቤት አንደኛ ቡድን የመጨረሻ የብር ዋንጫ ሽልማት ግጥሚያ ነበር፡፡ ሰሞኑን ከተጫዋቾች ጓደኞቹ መሃል ጥቂቶቹ ሀኪም ቤት ድረስ እየመጡ በእንዴት ያለ ዝግጅት መግጠም እንዳለባቸው እንነጋገር ነበር፡፡ እኔም መሰንበቻውን ሁሉእንዳንሸነፍ በጣም ሳስብ ነበር፡፡ የተቀደድሁ እለት ታዲያ እየጮህኩ‹‹መሸነፍ የለብንም!መሸነፍ የለብንም!ዋንጫው ከእኛ እጅመውጣት የለበትም!››አልሁኝ አሉ፡፡

አልማዝም የምትቀደድበት ቀን ደረሰ፡፡ ኦፕራሲዎኑም የአርባ ደቂቃ ጊዜ ወሰደ፡፡ አድማሱም በዚህ ጊዜ ጨንቀት ወዲያና ወዲህ እየተንቆራረጠ ይጸልይ ነበር፡፡ ከመቀደጃውም ቤት ወደክፍሏ መለሷት፡፡አድማሱም እስክትነቃለት ድረስ ከእናትና ከአባቷጋር ክፍሏ ውስጥ ገብቶብቻውን ወዲያና ወዲህ ሲቆራጠጥ ቆየ፡፡ ከሃያ ደቂቃ በኋለም አልማዝ ተንቀሳቀሰች፡፡ አድማሱም የደስታ እንባ አንቆት አልጋው ስር ሂዶ ተንበረከከ፡፡ ቀጥሎም ከአልማዝ ድምጽ ወጣ፡፡

ተሰማ!...ተሰማ!...ተሰምዬ!

ምንጭ፡-(ታደሰ ሊበን፣1952፣ሌላው መንገድ፣ገጽ 15-31) ለማስተማሪያ እንዲመች ተሸሽሎ የተወሰደ፡፡

**መመሪያ አንድ፡- ቀጥሎ የቀረቡ ጥያቄዎችን በምንባቡ መሰረት ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡**

1. ደበበ አድማሱ አልማዝን እንዲተዋት የሚወተውተው እሱ ሊያገባት ስለፈለገ ነው፡፡
2. አልማዝ ፈጽሞ ተሰማ የሚባል ልጅ አታውቅም ብሎ መደምደም ይቻላል፡፡
3. አድማሱ ደበበ ‹‹የምልህን አድርግልኝ›› ሲለው እሽ ያለው በነገሩ አምኖበት ሳይሆን ማስቀየም ስላልፈለገ ነው፡፡
4. ለአድማሱ አልማዝ ትቅርብህ ብሎ አስተያየት የሰጠ ደበበ ብቻ ነበር፡፡
5. አድማሱ አልማዝን ከማደንዘዣ እስከምትነቃ ይጠብቅ የነበር ከጓደኞቹ ጋር በመሆን ነው፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡**

1. አልማዝ አድማሱን የተዋወቀችው በስንት አመቷ ነው?
2. አድማሱና ደበበ የሚጨቃጨቁት በምን ምክንያት ነበር?
3. የአልማዝ ቀዶ ጥገና ምን ያህል ጊዜ የፈጀ ነበር?
4. አድማሱ አልማዝን ለመጀመሪያ ጊዜ ያያት የት ነበር?
5. የአድማሱና የደበበ ጓደኝነት የተጀመረው ከየት ነው?
6. አድማሱና አልማዝ የከንፈር ወዳጅ ለመሆን የፈጀባቸው ጊዜ ምን ያህል ነበር?
7. አልማዝ የታመመችው ምን ነበር?
8. የነአልማዝ ትምህርት ቤት የዳንስ ቀን የተከበረው የት ነበር?

***መመሪያ ሶስት፡- ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡***

1. ‹‹ሰዎች ይነጋገሩበት ነበር›› የተባለው በምኗ ነው?
   ሀ.በባህሪዋ ለ.በትምህርቷ ሐ.በቁንጅናዋ መ.በህመሟ
2. አድማሱና ደበበ የተቆራረጡት በምን ምክንያት ነው?
   ሀ.ደበበ አድማሱን በመዋሸቱ ለ.አድማሱ ደበበን ሚስጥር በመደበቁ
   ሐ.ደበበ ለአድማሱ አልማዝ እንደማትሆነው በመግለጹ መ.ደበበ ራስ ወዳድ በመሆኑ
3. የአድማሱ አባት አቶ አየለ የሞቱት አድማሱ የስንት ዓመት ህጻን እያለ ነበር?
   ሀ.የአስር ዓመት ለ.የአራት ዓመት ሐ.የስምንት ዓመት መ.የስድስት ዓመት
4. ተጭና አቀበት ከምትወጣ አህያ ጋር የተወዳደረው ማን ነው?
   ሀ.አድማሱ ለ.አቶ ደምሴ ሐ.ደበበ መ.ተሰማ
5. በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልክት ምንድን ነው? ሀ.ጓደኛ በትዳር ውስጥ ጣልቃ መግባት እንደሌለበት ለ.ትዳር ለመመስረት መጠናናት እንደሚያስፈልግ ሐ.የፍቅር ጓደኛ የሚለውን ሁሉ ማመን ተገቢ መሆኑን መ.ሰዎችን መጠራጠር ተገቢ አለመሆኑን
6. አድማሱ ቤትና መኪና የገዛ ስራ በያዘ በስንት ዓመቱ ነው? ሀ.በአምስት ለ.በአስር ሐ.በአራት መ.በሁለት
7. አድማሱ ለአልማዝ የፍቅር ደብዳቤ የሰጣት በአያት በስንተኛ ቀኑ ነበር? ሀ.በወሩ ለ.በዓመቱ ሐ.በሳምንቱ መ.በማግስቱ
8. አድማሱ ከአልማዝ ጋር በመተዋወቁ የአድማሱ ጓደኞች ያልተደሰቱበት ምክንያት ምን ነበር?

ሀ.አልማዝ በትምህርቷ ጎበዝ ስላልነበረች    ለ.አልማዝ የሀብታም ልጅ ስላልነበረች

ሐ.አልማዝ ቆንጆ ልጅ ስላልነበረች  መ.አልማዝ በባህሪዋ ምስጉን ስላልነበረች

9. በደበበ አባባል አልማዝ ከተሰማ ጋር ወደ እቴጌ ሆቴል የገባችው በስንት ሰዓት ነበር?

ሀ. በሦስት ሰዓት ከሩብ        ለ. አራት ሰዓት ከሩብ

ሐ.ሁለት ሰዓት ተኩል        መ. በአንድ ሰዓት ተኩል

10.አልማዝና አድማሱ በትዳር እንደማይቀጥሉ የሚያመላክተው አንቀጽ የቱ ነው?

ሀ.የመጀመሪያው   ለ.የሶስተኛው   ሐ.የመጨረሻው   መ.ስድስተኛው

***መመሪያ አራት፡-ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡***

1.አብራክ

2.መታሰቢ

3.ደሙ ፈላ

4.ዓይነ እርግብ

5.ጥርሱን ነክሶ

***መመሪያ አምስት፡-ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ መልስ ስጡ፡፡***

1. ስለአልማዝ ተገቢ መረጃዎችን በመሰብሰብ ውስጣዊና ውጫዊ ማንነቷን ግለጹ፡፡

2. እንደደበበ አይነት ጓደኛ እንዲኖራችሁ ትፈልጋላችሁ? ለምን?

3. እናንተ አድማሱን ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

መርጃ መሳሪያ፡- ሌላው መንገድ

ግምገማ ፡-የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መልስ መገምገም

- የግል ስራቸውን ማረም

-የቡድን ስራ

**ክፍለ ትምህርት ሶስት**

የትምህርት ርዕስ፡-የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በአጭሩ በግለጽ

-ስለገጸባህርያቱ በአዕመሯቸው ምስል ይፈጥራሉ

-የገጸባህርያትን እንቅስቃሴና አመለካከት መለየት

-የገጸባህርያትን የአካልና የማንነት ገለጻ ከታሪኩ ሁነቶች ጋር ያለውን መያዝ መለየት

-ያነበቡትን ልቦለድ ታሪክ በጊዜና በቦታ ቅደምተከተል ማቅረብ

-ለቃላት አውዳዊ ፍች መስጠት

ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ ፡- 1፡20

የትምህርቱ አላማ ፡-ከዚህ ክፍለጊዜ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

-የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በአጭሩ ይገልጻሉ

-የደራሲዉን ሀሳብ ወይም መልክት ይረዳሉ

-ለአዳዲሰ ቃላት አዉዳዊ ፍች ይሰጣሉ

-የገጸባህርያትን የአካልናየማንነት ገለጻ ከታሪኩ ሁነቶች ጋር ያለውን ትስስር ያስረዳሉ

--ያነበቡትን ልቦለድ ታሪክ በጊዜና በቦታ ቅደም ተከተል ያቀርባሉ፡፡

-ለቃላት አውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፡፡

***ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች***

1. ባህል ምንድን ነው?
2. በአካባቢያችሁ ያሉ ጠቃሚና ጎጅ ባህሎች ምን ምን ናቸው?
3. ጋብቻ በተጋቢዎች ፈቃደኝነት ላይ ካልተመሰረተ ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?
4. የምታውቁትን አንድ ብሔረሰብ የጋብቻ ባህል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ?

## አንቻቦ

በዐይነ ሕሌናው አያት-ጋንዘርን፡፡ አስር አመት ያህል በእድሜ ይበልጣታል፡፡ በኦሞ ወንዝ ዳርቻ ከብቶቻቸውን ጨሌ ሲያግጡ፣ እዚያው ከብት ከሚጠብቁበት ስፍራ ላምም ሆነ ፍየል አልበው በአንድ ጮጮ ወተት ጠጥተዋል፡፡ እንደ አብዛኞቹ የሙርሲ ልጃገረዶች ረዘም፣ ፈርጠም ያላለች፣ከንፈሯደም እንደቋጠረ ስጋ ያላበጠ፣ ጥርሷ ከንፈሯን አልፎ ያላገጠጠ በጥቁር አካሷ ላይ በስሱ የሚፍለቀለቅ በረዶ መሳይ ጥርስ ያላት ዐይናማ ልጅ ነበረች፣ ያኔ ሲያውቃት፡፡ አሁን አስራ ስድስት አመቷ ነው፡፡ የባህል እዳ ሆኖባት ‹‹የበለጠ እንድታምር››፣ ለቤተሰቦቿ ብዙ ጥሎሽ እንድታስገኝ እንደእናቶቿ ወግ ከንፈሯን ክብ ከተተለተለች ሁለት አመት አልፏታል፡፡

‹‹ሰው ሰራሽ ውበት የሚያስፈልገው ለመልከ ጥፉዎች ነው፡፡ መልከቀናዎቹን መልከጥፉ ለምን እናደርጋለን የጋዘር እናት? …››ብሎ የጋዘርን ከንፈር ለመተልተል የተዘጋጀው ስለት ሲፋጭ እንደዋዛ የጠየቀው ትዝ አለው፡፡

‹‹የአያት የቅድመ-አያት ልማዳችንን አስቀሩ በለና! ይኸው ነው የቀረህ፡፡››

የጋዘር እናት ትንታግ ምላስ እንዴት እንደገረፈው፣ ጎሪጥ ዐይናቸው እንዴት እንደገረመመው ታወሰው፡፡ ጋዘር፣ ለእርድ እንደቀረበ ፍየል ስለት ከቧት፣ አንዱ እጇን፣ ሌላው እግሯን በገመድ አስሮ፣ ጉልበት ያለው ተመርጦ እራሷን በግድ ጠፍሮ፣ የታችኛው

ከንፈሯ ግማሽ ክብ በመስመር ሲተለተል የፈሰሰው ደም በሰቀቀን ታወሰው፡፡ ጋዘር ስለት ሲያርፍባት እንደታረደ ከብት የጮኸችው ተሰምቶት ከሃሳቡ ባነነ፡፡

‹‹መልካም ልማድ እንጅ ጎጅና ክፉ ልማድ እንዴት ይወረሳል? አያት ያጠፋውን አባት እያለማ፣ አባት ያበላሸውን ልጅ እያሻሻል ሲገኝ ይመስለኛል በጎው ነገር››አለ አንቻቦ፣ እንባ የቋጠሩ ዐይኖቹን ወደ ጠራው ሰማይ ወርውሮ፡፡ በውስጡ አፍኖ ይዞት የነበረው ፍቅር የጠፋው ያንጊዜ ነው፤ ከንፈሯ በስለት ተተልትሎ እንደጎርፍ የወረደው ደም ከተንጋለለችበት ላይ ሲረጋ-ነቃ፡፡

አባቱ ጋዘርን ለልጃቸው ሚስትነት ጠይቀው ተፈቅዶላቸዋል፡፡ የከንፈሯ መተልተል የሚያስከትለውን ጥሎሽም ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ ጋዘር ‹‹ከንፈሯን ተተለተለች፤ክብ ሽክላ በከንፈሯ ወጠረች፤ቀለበት ትልትል ከንፈሯን በጭንቅላቷ አጠለቀች››የማለትን ‹‹የምስራች›› ሲሰሙ በባህላቸውና በልማዳቸው መሰረት ወይፈን አርደው ወዳጅ ዘመድ ጋብዘው ሽለሉ፤ ፎከሩ፡፡

በድግሱ ቀን ‹‹ከደም ጋር የተቀላቀለውን ፈርስ አምጡና ይታጠብ! ለሶስት ጉልቻ ልትበቃ ነውና እንደአባቶቻችን ወግ ጎንበስ ብለህ ታጠብ!›› ብለው ልጅ የመዳር ወግ ደርሷቸው ሁለመናቸው ፈክቶ አንቻቦን አዘዙት፡፡

1. ከአነበባችሁት ምንባብ ምን ተረዳችሁ?
2. ቀጥሎ ምን ሊፈጠር ይችላል ብላችሁ ትገምታላችሁ?
3. አንቻቦ ጥያቄውን የሚቀበል ይመስላችኋል?

እሱ ግን የአባቱን ቀርቶ የዚያን ሁሉ ሰው ጉርጥርጥ ዐይን ከቁም ነገር አልቆጠረውም፡፡

‹‹አንተን እኮ ነው!›› አሉት አባቱ አፋቸው ተያይዞ፡፡

በንዴት ‹‹ ኧረ አንድ በለኝ ጎሳ!›› ብለው እዚያ የተሰበሰበውን ትንሹንም ትልቁንም ተማጸኑ፡፡ የጎሳውን ልማድ እንዲፈጽም የሚያደርግ ግን አልተገኘም፡፡

‹‹አልቀበለውም! ›› በማለት አንቻቦ ፈርጠም ብሎ ምላሽ ሰጠ- ለአባቱ፡፡

‹‹ምኑን ነው የማትቀበለው?›› ቁጣቸውን ደብቀው በለዘበ አንደበት ጠየቁት አባቱ፡፡

በደምና በፈርስ መታጠቡንም ሆነ የመረጣችሁልኝን ጋብቻ አልቀበለውም፡፡››

ቁጣቸው አገረሸባቸው፡፡ ከውስጣቸው የሚወጣው ነበልባል አንቻቦን ሳይሆን እሳቸውን መልሶ ሲገርፋቸው ተሰማቸው፡፡

‹‹ሰድበሽኛል! አዋርደሽኛል! አይማረኝ! አልምርህም!›› የሰራ አካላቸው ተንዘፈዘፈ፡፡

‹‹የማልፈልገውን ጋብቻ አልቀበልም ማለት ስድብ አይደለም! ››

‹‹ እንዴት?››

‹‹እኔ የምፈልገው ውበትን ነው፡፡ ያልተበላሸ ውበት! የፈለኩትን ውበት አጥፍታችሁ የጠላሁትን እንድወድ ልታስገድዱኝ አትችሉም፡፡›› ከወትሮው ኮስተር ብሎ ለአባቱ ብቻ ሳይሆን እዚያ ለተሰበሰቡት የጎሳው አባላት ተናገረ፡፡

‹‹አሁን ሌላ የምጠይቅህ የለኝም፡፡ ያስቀየምኩትን የልጅትን ቤተሰብ ብቻ ካስልኝ፡፡ ያስቆጠርኩትን ጥሎሽ እጥፍ አድርገህ ለመክፈል ቃል ግባልኝ፡፡››

‹‹ያልበላሁትን እዳ ለመክፈል የምገባው ቃል የለኝም!›› አባቱ ይህንን ምላሹን ሲሰሙ ከግርግሩ ቀለበት እመር ብለው በመስፈንጠር ወደኋላ አፈገፈጉ፡፡ የአብራካቸውን ክፋይ ወሰኑበት እንደ ህጻን ልጅ አቅፈው ሲያዘናፍሉት የነበረውን ጠመንጃ አቀባብለው ምላጩን ሳቡ፡፡ ጋዘር በማይታመን ፍጥነት ተወርውራ አፈሙዙን ስትመታው ጥይቱ ኢላማውን ስቶ ባረቀ፡፡

በዚህ አጭር ጊዜ የደረሰበትን የህይወት ውጣውረድ አስታውሶ ‹‹ጊዜው እንዴት ይነጉዳል?›› አለ አንቻቦ ከኦሞ ወንዝ ዳርቻ ተቀምጦ የማታ ፀሐይ የሚሞቀውን አዞ እያስተዋለ፡፡

(ምንጭ ፡- የቀድሞው አማርኛ 9ኛ ክፍል (1997) የመማሪያ መጽሐፍ)

***መመሪያ አንድ፡- የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ናቸው በቡድን ተወያይታችሁ ተገቢ መልስ ስጡ፡፡***

1. ጥይቱ ዒላማውን ስቶ እንዲባርቅ ያደረገችው ማን ናት? ለምን?
2. መልካም ልማድ እንጅ ጎጅና ክፉ ልማድ መወረስ የለበትም በሚለው ሃሳብ የሚስማሙት እነማን ናቸው? የማይስማሙትስ?
3. የአያት የቅድመ አያት ልማዳችንን አስቀሩ በለና በማለት የተናገሩት የጋዘር እናት ሀሳብ ተቀባይነት አለው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
4. የአንቻቦን ትዝታ የቀሰቀሰው ምንድን ነው?
5. ያልበላሁትን እዳ ለመክፈል የምገባው ቃል የለኝም ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

**መመሪያ ሁለት፡ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. .የአንቻቦን አባት በደስታ ያስፈነጠዘው ጉዳይ ምንድን ነው?

   ሀ. ወንድ ልጅ መውለዱ ለ. ልጅ የመዳር ወግ ስለደረሰው

   ሐ. ልጁ ደም በተቀላቀለበት ፈርስ መታጠቡ መ. ወዳጅ ዘመድ ጠርቶ መጋበዙ

2. ጋዘር ከንጆን የተተለተለችበት ትክክለኛ ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የበለጠ እንድታምር ለ. ለቤተሰቦቿ ብዙ ጥሎሽ እንድታስገኝ

   ሐ. ሰው ሰራሽ ውበት አስፈላጊ በመሆኑ መ. የአያት የቅድመአያት ልማድ ላለማስቀረት

3. የጋዘር እናት ትንታግ ምላስ የገረፈው ማንን ነው?

   ሀ. አንቻቦን ለ. የአንቻቦን አባት ሐ. የጎሳውን አባላት መ. የጋዘርን አባት

4. አንቻቦ ጋብቻውን አልቀበለውም ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ. የአባቱን ትዛዝ ላለመፈጸም ለ. ጋዘር ቆንጆ ስላልሆነች

   ሐ. ልማዱን ስለሚቃወም መ. ባለጌ ስለሆነ

   5.የአንቻቦ አባት ‹‹ሰድበሽኛል! አዋርደሽኛል! አይማረኝ! አልምርህም!›› ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ.ልጃቸው በሰው መሐል ስለሰደባቸ ለ. የማፈልገውን ጋብቻ አልቀበልም ስላለ

   ሐ. ልጃቸው በፈርስና በደም ስለታጠበ መ. ልጃቸው የማህበረሰቡን ወግና ባህል ስለጣሰ

5. የተቆጠረውን ጥሎሽ እጥፍ አድርጎ እንዲከፍል የተጠየቀው ማን ነው?

   ሀ. የጋዘር አባት ለ. የአንቻቦ አባት ሐ. ጋዘር መ. አንቻቦ

6. የአንቻቦን አባትና የጋዘርን እናት አንድ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው?

   ሀ. ልጅ የመዳር ወግ ስለደረሳቸው ለ. ሁለቱም የልማዱ ተገዥ መሆናቸው

   ሐ. ሁለቱም ሐብታም መሆናቸው መ.ሁለቱም ወንድ ልጅ ስላላቸው

7. ጋዘር ከንፈሯን የተተለተለችው በስንት አመቷ ነው?

   ሀ. በአስራ ስድስት ለ በአስራ አራት ሐ. በሃያ ስድስት መ. በአስር

8. ለሶስት ጉልቻ ልትበቃ ነው የሚለው ዓ/ነገር ምንን ይገልጻል?

   ሀ. ትዳር ልትመሰርት ነው ለ. በደምና በፈርስ ልትታጠብ ነው

ሐ. ከንፈሯ ሊተለተል ነው                                     መ. ልጅ ልትወልድ ነው

9. የአብራካቸውን ክፋይ ወሰኑበት ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. ሊድሩት ወሰኑ                                     ለ. ሊገድሉት ወሰኑ

ሐ. በደም ሊያጥቡት ወሰኑ                                     መ. ያልበላውን እዳ ሊያስከፍሉት ወሰኑ

***መመሪያ ሶስት፡- ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡***

1. የአብራክ ክፋይ
2. ውርስ
3. ትንታግ
4. ውበት
5. ጮርጮ

***መመሪያ አራት፡- የሚከተሉት ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች ናቸው ለያንዳንዱ ጥያቄ አራት አራት ምርጫዎች ቀርበዋል ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡***

1. .አንቻቦ ‹‹እኔ የምፈልገው ውበት ነው ያልተበላሸ ውበት››ያለበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. ጋዘር ውበት ስለሌላት                                     ለ. የጋዘር ውበት በልማዱ ምክንያት ስለጨመረ

ሐ. ጋዘር ከንፈሯ በመተልተሉ ውበቷ ስለተበላሸ                                     መ. በደም መታጠብ ውበትን ስለሚቀንስ

2. የአንቻቦ እድሜ ስንት ነው?

ሀ. አስራ ስድስት          ለ. ሃያ ስድስት          ሐ. ሰላሳ ስድስት          መ. ሃያ አራት

3. አንቻቦ በውስጡ አፍኖ ይዞት የነበረው ፍቅር የጠፋው በምን ምክንያት ነው?

ሀ. ከንፈሯ በስለት ተተልትሎ ደም እንደ ጎርፍ ሲወርድ በማየቱ

ለ. ጋዘር ለእርድ እንደቀረበ ፍየል ስለት ከቧት በማየቱ

ሐ. እጅ እና እግሯን በገመድ ስትታሰር በማየቱ

መ. ከንፈሯ ግማሽ ክብ በመስመር ተተልትሎ በማየቱ

4. በምንባቡ መሰረት የእናት ወግ የተባለው ምንድን ነው?

ሀ. ባል ማግባት          ለ. ልጅ መውለድ          ሐ. ከንፈር መተልተል          መ. ጥሎሽ ማስጣል

5. ጋዞርና አንቻቦ በኦሞ ወንዝ ዳርቻ ከሰሯቸው ስራዎች ውስጥ አንቻቦ የሚያስታውሰው የቱን ነው?

ሀ. የወንዙን አካባቢ እየተዘዋወሩ መጎብኘታቸውን

ለ. ላምም ሆነ ፍየል አልበው በአንድ ጮጮ ቀተት መጠጣታቸውን

ሐ. ከንፈሯን በግማሽ ክብ መተልተሏን

መ. አንቻቦን ለመግደል አባቱ ሲተኩስ አፈሙዙን በመምታት ኢላማ ማሳቷን

6. ጋዞር ከንፈሯን በምትተለተልበት ወቅት ጉልበት ያላቸው ሰዎች ተመርጠው ያከናወኑት ተግባር ምንድን ነው?

ሀ. ሁለቱን እጆቿን መያዝ ለ. ስለቶችን ማቀራረብ

ሐ. እግሯን በገመድ ማሰር መ. እራሷን በግድ ጠፍሮ መያዝ

7. ጋዞር ‹‹ከንፈሯን ተተለተለች፤ክብ ሸክላ በከንፈሯ ወጠረች፤ቀለበት ትልትል ከንፈሯን በጭንቅላቷ አጠለቀች››የማለትን ‹‹የምስራች›› ሲሰሙ በሚለው አገላለጽ ውስጥ የምስራች የሚለው በጥቅስ ምልክት ውስጥ የተቀመጠበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. ፀሐፊው ያልተስማማበት መሆኑን ለመግለጽ

ለ. አንባቢያን ትኩረት ሰጥተው እንዲያነቡት ለማሳሰብ

ሐ. ቃሉ ለአንባቢ ያልተለመደ መሆኑን ለመግለጽ

መ. ከሌላ ሰው የተወሰደ ሐሳብ መሆኑን ለማሳየት

8. በምንባቡ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ምንድን ነው?

ሀ. አያት ቅድመአያት ያቆዩንን ልማድ ማስቀጠል የልጆች ተግባር እንደሆነ

ለ. አያት ወይም አባት ያበላሸውን ልጅ ማስተካከል እንዳለበት

ሐ. የተፈጥሮ ውበት ብቻ በቂ እንዳልሆነ

መ. ጋብቻ በቤተሰብ ፈቃድ ብቻ መመስረት እንዳለበት

9. በአይነ ህሌናው አያት ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ. አሰተዋላት ለ. አስታወሳት ሐ. በአይኑ ገረፋት መ. ተመለከታት

10. አንቻቦ ጋዞርን በስንት ዓመት ይበልጣታል? ሀ.በአስር ለ.በአምስት ሐ.በሁለት መ.በአስራአምስት

**መመሪያ አምስት፡-የሚከተሉትን የተፋለሱ ዓረፍተ ነገሮች በድርጊት ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ አስቀምጡ፡፡**

1. ጋዘር ከንፈሯን ተተለተለች፡፡
2. የአንቻቦ አባት ወይፈን አርደው ወዳጅ ዘመድ ጋበዙ፡፡
3. ጥይቱ ዒላማውን ስቶ ባረቀ፡፡
4. ጋዘር የጠመንጃውን አፈሙዝ መታችው፡
5. አንቻቦ ደም በተቀላቀለበት ፊርስ እንዲታጠብ ታዘዘ፡፡
6. የአንቻቦ አባት ጠመንጃ ተኮሱ፡፡
7. አንቻቦ ጋብቻውን እንደማይቀበል ገለጸ፡፡

**መመሪያ ስድስት፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጽሁፍ መልሱ፡፡**

1. የአንቻቦንና የጋዘርን ውስጣዊና ውጫዊ ማንነት ከታሪኩ ሁነቶች ጋር በማያያዝ አቅርቡ?
2. ከአንቻቦና ከአባቱ አመለካከት የማንን ትደግፋላችሁ? ለምን?

የትምህርቱ መርጃ መሳሪያ፡-የቀድሞው አማርኛ ዘጠነኛ ክፍል መጽሃፍ

ግምገማ፡-የአንብቦ መረዳት የቃል ጥያቄዎችን መልስ መገምገም

- የቡድን ውይይታቸውን መገምገም
- የግልስራቸውንማረም

**ክፍለ ትምህርትአራት**

የትምህርቱ ርዕስ፡- የምንባቡን ፍሬ ሀሳብ በራሳቸው መንገድ በንግግር መግለጽ
የገጸባህርትን የአካልና የማንነት ገለጻ ከታሪኩ ሁነቶች ጋር በማያያዝ መግለጽ ለቃላት
እማሬአዊና ፍካሬአዊ ፍች መስጠት

ለትምህርቱ የተሰጠው ጊዜ 1፡20

የትምህርቱ ዓላማ፡- ከዚህ ክፍለጊዜ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡-

-የምንባቡን ፍሬ ሃሳብ በራሳቸው መንገድ በንግግር ይገልጻሉ፡፡

-የገጸባህርያትንየአካልና የማንነት ገለጻ ከታሪኩ ሁነቶች ጋርበማያያዝ ይገልጻሉ፡፡

-ለቃላት እማሬአዊና ፍካሬአዊ ፍች ይሰጣሉ

## ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. ወላጆች ስለምን ማውራት ያስደስታቸዋል?ለምን?
2. ህጻናት ትምህርት የሚጀምሩት ከየትና ከማን ነው?
3. ህጻናት ከማህበረሰቡ ባህል ውጭ የሆኑ ድርጊቶች ሲፈጽሙ ተመልክታችኋል? ምን?
4. ህጻናት መጥፎ ባህሪ እንዲኖራቸው ከሚያደርጉ ድርጊቶቻችን/አስተምሮዎቻችን/ ውስጥ እናንተ የምታውቋቸውን ጥቀሱ?

### ተማሪው

ወዳጀ አባቴ መሪ ጌታ መድሎት፣ወርቄ የተሰኘ ብላቴና አለው፡፡ ታዲያ እኔ በየሰንበቱ ልጠይቀው በሄድሁ ቁጥር ወሬው በመላ ከወርቄ ፈቀቅ አይልም፡፡

አሁን ባለፈው እሁድ ሰላምታየን አስቀድሜ ወደ ጎጆው ገብቼ ብዙም አልቆየሁ፡፡ ያጣድፈኝ ጀመር፡፡

‹‹ብርቱነህ? የኑሮህ ይዞታስ?››

‹‹ጥሩ ነው!››

‹‹እጮኛ አበጀህ?››

‹‹የለም ገና ነኝ››

‹‹አብጅ እንጂ፡፡ አንዲቱን ፈልግና አግባት...አግብተህ ውለድ...››ዝም ብየ እሰማዋለሁ፡፡

‹‹...እውነት እልሀለሁ ...መውለድን የሚያህል ጸጋ የለም...አሁን ወርቄን ተመውለዴ በፊት የነበረው ህይወቴ ህይወት ነው?›› ከጥቂት እረፍት በኋላ፡፡

‹‹ሰማኸኝ- ወይ?››

‹‹እ››

‹‹ወርቄ አራት ዓመት ተመንፈቅ እንደሞላው ነግሬሀለሁ? የኔ ነገር አልነገርሁህም ለካ! አሁን የመማሪያ ጊዜው ነው፤መምህሩ እኔው ነኝ፡፡ እሱም የዋዛ እንዳይመስልህ፡፡ አስቀድሜ ምን እንዳስተማርሁት ታውቃለህ?››

‹‹ፊደል ነው?››

‹‹የለም ስነ መግባር ነው፡፡ ከስነምግባር ክፍሎችስ አስቀድሜ ምን እንደማስተምረው ነግሬሀለሁ?››

‹‹የለም አልነገርኸኝም፡፡››

‹‹ልግስናን ነው፡፡ በየሳምንቱ እሁድ ማለዳ ወደ ደብር ይዤው እሄድና ሳንቲሜን ተኪሴ እየመዠረጥሁ በመደዳ ለተኮለኮሉት ነዳያን እመጸውታለሁ፡፡ እንግዲህ ይህንን ሳደርግ እሱ

አጠገቤ ቆሞ ያየኛል፤ሌጣ ብራና ማለት አይደል!...እኔ በጎነትን እየጻፍሁበት ነው፡፡ አይደለም እንዴ?››

‹‹ነው!››

‹‹አየህ ሁላችንም እንዲህ ማድረግ ይገባናል:: ይህን ታደረግን የሚፈቃቀር ትውለድ እናፈራለን፡፡ አይደለም ወይ?››

‹‹ኸረ ጥርጥር የለውም!››

‹‹እኮ!...ለዚያነው ወርቂ ለነዳያን ስመጸውት አጠገቤ ቆሞ እንዲያየኝ የማደርገው...ታዲያ እሱ ይጠይቀኛል፡፡ ምን ብሎአትለኝም!››

‹‹ምን ብሎ?››

‹‹ ‹ለምንድን ነው ሳንቲም የምትሰጣቸው አብዬ?›ይለኛል፡፡ ‹ያጡትን ነገር እንዲሸምቱበት ነዋ እለዋለሁ፡፡ አንተ ብቻ ነህ የምትሰጣቸው?›ብሎ ሲለኝ የለም ሌሎች ደጋግ ሰዎችም ይሰጧቸዋል እለዋለሁ፡፡ አንገቱን ደፍቶ በተመስጦ ያሰላስላል፡፡ አይገርምም?››

*እስካሁን ካነበባችሁት የጽሁፍ ክፍል ምን ተረዳችሁ?

*አባቱ ይህንን ተግባር ለህጻን ልጁ ማሳየቱ ተገቢ ነው ትላላችሁ? ለምን?

*ወርቂ አባቱ እንዳሰቡት በስነመግባር የታነጸ ልጅ የሚሆን ይመስላችኋል? ለምን?

‹‹ያስተምሮየን ውጤት በቅርቡ ታያለህ››ሲል አከለ፡፡ ብዙ ባልቆይ ጥሩ ነበር፡፡ግን ቆየሁ፡፡ ሲመሽ ብላቴናው ወርቂ ብጣሪ እንዳየች ድንቢጥ ሲበር መካከላችን ተገኘ፡፡

‹‹ደህና ነህ ወይ ወርቂ?››አልሁት፤አቧራ የለበሰ ጉንጬን በከንፈሬ እየነካካሁ፡፡››

‹‹ደህናነኝ!አንተስ ደህናነህ?››

‹‹ደህናነኝ!››

‹‹ቤትህ ደህና ናት?››

‹‹ደህና ናት፡፡››

‹‹እህትህስ ደህና ናት?››

‹‹ድህናናት ወርቂ››ተንጠራራሁ፡፡

‹‹አንተስ ደህና ነህ?››

‹‹ልቤ እንዳይፈርስ ሰግቸ ትንፋሸን ቆጠብሁ፡፡ አባትየው በፍቅር ዓይን ይከታተለዋል፡፡

‹‹ጋሽዬ ንጅ!››አለኝ ቀጠለና

‹‹አቤት!››

‹‹እንትን!››

ቅቤ ተቀብቶ ለጋ ቅል የመሰለውን ጠጉር አልባ ራሱን እያከከ አቀረቀረ፡፡

‹‹ምን?››

‹‹እስቲ ሳንቲም ስጠኝ?››

‹‹ሳንቲም ምን ያደርግልሀል?››

‹‹…ኧረግ ያጣሁትን ነገር እሸምትበታለሁ እንጂ!ሌላ ምን አረገዋለሁ? ዛሬ ብዙ ሰዎችን ብጠይቃቸው ደጋጎች ሰጡኝ፡፡ አንዳንዶቹግን ወግድ አንተ አባት አሰዳቢ አሉኝ፡፡ በል አንተ ስጠኝ እያ!››ትንሽ መዳፉን ወደኔ ዘረጋ፡፡

ሳቄን በከንፈሬ አስሬ ወደመሪጌታ ተመለከትሁ፡፡ ፈገግታው ፊቱላይ የለም፡፡ ገጹ አመዳይ የወረሰው ቅጠል በመምሰል ላይ ነበር፡፡

ምንጭ ፡- (የቀድሞው አማርኛ 9ኛ ክፍልየተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ) (1997)

**መመሪያ አንድ፡-ለሚከተሉትጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት በቃል መልስ ስጡ፡፡**

1. አንዳንዶች ወግድ አንተ አባት አሰዳቢ ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ወርቄ ሳንቲም ምን ያደርግልሀል ሲባል የሰጠው መልስ ምን የሚል ነበር?
3. መርጌታ መድሎት ለወርቄ ትምህርት የሰጡበት መንገድ ተገቢ ነበር? ለምን?
4. የመሪ ጌታ ፍላጎት ተሳክቷል ትላላችሁ ለምን?
5. መርጌታ መድሎት ፈገግታው ከፊቱ ላይ የጠፋው በምን ምክንያት ነው?

**መመሪያ ሁለት፡-ለሚከተሉት ቃላት በምንባቡ መሰረት አውዳዊ ፍች ስጡ፡፡**

1. ነዳያን
2. ስነምግባር
3. ብላቴና
4. ተመስጦ
5. ብጣሪ
6. መመኸሪጥ

**መመሪያ ሶስት፡- ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ጥያቄዎችን በጥሞና በማንበብ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡**

1. መርጌታ መድሎት ስንት ልጅ አላቸው? ሀ.አንድ ለ.ሁለት ሀ.ሦስት መ.አራት
2. መሪጌታ መድሎት ‹‹አንዲቱን ፈልግና አግባት…አግብተህ ውለድ…››ያሉበት ምክንያት ምንድን ነው?

   ሀ.የሚስትን አስፈላጊነት ለመግለጽ ለ.የልጅን አስፈላጊነት ለመግለጽ

ሐ.የትዳርን ውስብስብነት ለመግለጽ መ.የብቸኝነት ህይወት አስከፊ መሆኑን ለመግለጽ

3. ወርቂ የስንት ዓመት ህጻን ነበር? ሀ.የስድስት ለ.የስምንት ሐ.የአራት መ.የአስር
4. ወርቂ በመጀመሪያ ጊዜ የተማረው ምን ነበር?

   ሀ.ፊደል ለ.ንግግር ሐ.ጽህፈት መ.ስነመግባር

5. መርጌታ መድሎት ወርቂን የሚያስተምሩት መቸ መቸ ነው?

   ሀ.ሰኞ ለ.እሁድ ሐ.ሀሙስ መ.ሁልጊዜ

6. ወርቂ መሪጌታ መድሎትን የሚጠይቃቸው ምን ብሎ ነበር?

   ሀ.ለምንድን ነው ሳንቲም የምትሰጣቸው ለ.ለምንድን ነው ቤተክርስቲያን የምንሄድ
   ሐ.ለምንድን ነው ትምህርት ቤት የማልሄድ መ.ለምንድን ነው ይህንን ምታሳየኝ

7. አንገቱን ደፍቶ በተመስጦ ያሰላስላል፡፡የተባለ ማን ነው?

   ሀ.መሪጌታ መድሎት ለ.ተራኪው ሐ.ወርቂ መ.የኔ ቢጤው

8. ‹‹ያስተምሮዬን ውጤት በቅርቡ ታያለህ ››ያሉት ወርቂ ምን ሆኖ ያየዋል ብሎ በማሰብ ነው?

   ሀ.በስነምግባር የታነጸ ለ.መግባረ ብልሹ ሐ.አዋቂ መ.ነዳያን

***መመሪያ አራት፡-ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡***

1. ተራኪው ልቤ እንዳይፈርስ ሰገቸ ትንፋሸን ቆጠብሁ ያለው በምን ምክንያት ነው?
2. በታሪኩ ውስጥ ከሌጣ ብራና ጋር የተነጻጸረው ምን ነበር?
3. ተራኪው በመጨረሻላይ ሳቁ የመጣበት ለምን ነበር?
4. በታሪኩ ውስጥ አመዳይ የወረሰው ቅጠል የተነጻጸረው ከምን ጋር ነበር?
5. መሪ ጌታ ተራኪውን ምን ሲሉ መከረውት ነበር? አስረዱ፡፡
6. በታሪኩ ውስጥ ከድንቢጥ ወፍ ጋር የተነጻጸረው ማን ነበር?
7. ብዙ ባልቆይ ጥሩ ነበር ያለበት ምክንያት ምን ነበር?

***መመሪያ አምስት ፡-የሚከተሉት ዓ/ነገሮች በያዙት ሃሳብ ላይ በቡድን ተወያዩ፡፡***

1. ፊቱ አመዳይ የወረሰው ቅጠል መሰለ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ህጻን ሌጣ ብራና ማለት ነው? በማለት የገለጹበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. ያስተምህሮየን ውጤት በቅርቡ ታያለህ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. የምንባቡ ዋና መልክት ምንድን ነው?

***መመሪያ ስድስት፡- በሚከተለው ቃል እማሪያዊና ፍካሪያዊ ፍቹን የሚያሣዩ ዓረፍተ ነገሮች ስሩ፡፡***

1. ድንቢጥ
2. ብጣሪ

መርጃ መሳሪያ፡- የቀድሞው ዘጠነኛ ክፍልየአማርኛ መማሪያ መጽሃፍ

ግምገማ ፡- የአንብቦ መረዳት የቃል ጥያቄዎችን መልስ መገምገም

- የግል ስራቸውን መልስ ማረም

- የቡድን ውይይታቸውን መልስ መገምገም

# ምዕራፍ አንድ

## አጭር ልቦለድ

### የምዕራፉ ዓለማዎች፡- ተማሪዎች! ይህንን ምዕራፍ ከተማሩ በኃላ፡-

- ለቃላትእማራዊና ፍካራዊ ፍች ትሰጣላችሁ
- የግሶችን ቅርጽ በመለዋወጥ ሌሎች ግሶችን ትመሰርታላችሁ ፡፡
- የሀረጋትን ምንነት ትገልጻላችሁ ፡፡
- ያዳመጣችሁትን ፍሬ ሀሳብ ትጽፋላችሁ
- ከተለያዩ ንግግሮችና ጹሁፎች ማስታወሻ ትይዛላችሁ፡፡
- ለምትጽፉት ጹሁፍ አስተዋጸኦ ታዘጋጃላችሁ፡፡
- የልቦለድን የአጫጭር ልቦለድና የልቦለድ አላባዊያንን ምንነት ታብራራላችሁ፡፡

**ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች**

- አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ተለይቶ የሚታወቀዉ በምንድ ነዉ
- ካነበባችኋቸዉ ወይም ካዳመጣችኋቸዉ አጫጭር ልቦለዶች መካከል ከሌሎች በበለጠ የምታስታዉሱት የተኛዉን አጭር ልቦለድ ነዉ? ይህን ልቦለድ እንድስታዉሱ የደረጋችሁን ምክንያቶች ግለጹ፡፡
- ከዚህ በታች አንድ አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል የልቦለዱን ርዕስና የመጀመሪያ አንቀጹን በማንበብ ስለምን እደሚተርክ ገምቱ፡፡
- ጹሁፉ ከየተኛዉ የጹሁፉ አይነት ዉስጥ ይመደባል? ለምን?

**አንድ ገመድ አለኝ**

ሁለት ወንድማማቾች እናታቸው ስታርፍ በቤት ውስጥ ያገኙት አንድ ትልቅ ገመድ ብቻ ነበር፡፡ ታላቁ ልጅ እጅግ በመበሳጨቱ ገመዱን ጠቅልሎ ጣራ ላይ ወረወረውና ከቤት ወጥቶ ሄደ፡፡ ታናሹ ግን ምንም ቢሆን ገመዱ የእናቱ ቅርስ ነውና እንደምንም ብሎ ጣራ ላይ ወጥቶ አወረደው፡፡ ከባዱ ጥያቄ ግን ከዚህ በኋላ ያለውን ኑሮ እንዴት መግፋት ይችላል? የሚለው ነበር፡፡ ለብዙ ሰዓታት ተቀምጦ አሰበበት፡፡

ምንም ነገር ሊታየው ግን አልቻለም፡፡ መንገዱ ሁሉ በግንብ የታጠረ ነው፡፡ አስቦ አስቦ ወደ አንድ ጠቢብ ዘንድ ሄደ፡፡ ጠቢቡ ሰው እንዳገኘው የጠየቀው ጥያቄ ‹‹ምን አለህ›› የሚል ነበር፡፡ መልሱም ቀላል ሆነ ‹‹ ምንም›› ጠቢቡ ሰውም ‹‹በዓለም ላይ ምንም የሌለው ሰው የለም፡፡ ምናልባት ግን ጥቂት ብቻ ያለው ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ አንተ ከወንድምህ በተለየ ጥበብ አለህ፤ ይህ ጥበብህም ነው ወደ ጠቢብ ያመጣህ›› አለው፡፡ ልጁ ግን በርግጠኛነት እየማለ ምንም እንደሌለው ተናገረ፡፡

ጠቢቡም ‹‹ይህ ፈጽሞ ሊሆን የማይችል ነው፡፡ ሰው ሆኖ ምንም የሌለው የለም፡፡ ረስተኸው ነው እንጂ አንዳች ነገር አለህ›› አለው፡፡ ልጁ ቢያወጣና ቢያወርድም ያለውን ነገር ሊያገኘው አልቻለም፡፡ የሚያውቀው ምንም እንደሌለው ብቻ ነው፡፡ ያን ጊዜ ጠቢቡ ልጁን ይዞት ወደ አንድ ክፍል ገባ፡፡ ክፍሉ ሊዳሰስ በሚችል ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ የተሞላ ነው፡፡ ጨለማው ዓይን ሊወጋ ይደርሳል፡፡ ከጠቢቡ ጋር በዚያ ክፍል ውስጥ እንደገቡ ‹‹ምን ይታይሃል?›› አለና ጠየቀው፡፡ ልጁም መለሱን ወዲያው ነበር ያገኘው ‹‹ጨለማ›› ጠቢቡ ግን እንደገና ጠየቀው፡፡ ‹‹ሌላ ነገር አለ፤ ፈልገው›› ዘወር ዘወር አለ፡፡ግን ምንም፡፡ ጠቢቡ እንዲህ አለው ‹‹ና አብረን ቁጭ እንበልና ጊዜ ወስደህ ተመልከት››

ተቀመጡም፡፡ ልጁ በግራና በቀኝ፤ በፊትና በኋላ ማየት ጀመረ፡፡ ለብዙ ደቂቃዎችም አየ፡ ፡ በመካከል ላይም ‹አሃ›› የሚል ድምጽ ከልጁ ሲወጣ ተሰማ፡፡ ጠቢቡም ‹‹እሺ ምን ተገኘ›› አለው፡፡ ‹‹በዚያ በኩል ባለው ቀዳዳ ብርሃን ነገር ይታየኛል›› አለው፡፡ ጠቢቡ አቀፈው፡፡

‹‹አሁን አእምሮህን መጠቀም ጀመርክ፡፡ አእምሮን መጠቀም ማለት ከዓይነ ሥጋ ይልቅ በዓይነ ልቡና ማየት መቻል፣ ከእዝነ ሥጋ ይልቅ በእዝነ ልቡና መስማት መቻል ማለት ነው፡፡ ‹ልብ ካላየ ዓይን አያይም› ሲባል አልሰማህም፡፡ አእምሮውን የሚጠቀም፣ ሰው ሁሉ የሚያየውን ብቻ ሳይሆን የማያውንም ያያል፡፡ ለዚህ ነው አእምሮ ያለው ሰው ተስፋ የማይቆርጠው፡፡ አእምሮ ያለው ሰው በግንብ መካከል በር፣ በጨለማ መካከል ብርሃን፣ በተራራ መሐል መንገድ፣ በሞት መካከል ሕይወት ይታየዋል፡፡‹‹መንገድ ያለው ከውጭ አይደለም፡፡ መንገድ ያለው ከውስጥ ነው፡፡ የውጭው መንገድ እግር ነው የሚሄድበት፡፡ የውስጡ መንገድ ግን ልቡና ነው የሚጓዝበት፡፡ በልቡናቸው የሄዱ ሰዎች ናቸው በእግራቸው ለመሄድ ፈልገው የእግሩን መንገድ የሠሩት፡፡ ከእነርሱ በኋላ ግን ብዙዎቹ በልቡናቸው ሳያዩ ይጓዙበታል፡፡ መጀመርያ በልቡናቸው የበረሩ ሰዎች ናቸው አውሮፕላንን የፈጠሩት፣ መጀመርያ በልቡናቸው የተገናኙ ሰዎች ናቸው ስልክን የሠሩት፡፡ እናም መንገድ ያለው ውስጥህ ነው፡፡ አንተ ውስጥ መንገድ አለ፡፡

‹‹ምን አልባት ያ መንገዱ አልተጠረገ ከሆነ ጥረገው፤ ተጎድቶ ከሆነ ጠግነው፤ አርጅቶ ከሆነ አድሰው፡፡ ከዚያ በኋላ ሁሉም ነገር ቀላል ነው፡፡ለማየት ጊዜ ውሰድ፡፡ ወሳኙ የጨለማው መጠን አይደለም፡፡ ወሳኙ አንተ የሰጠኸው ጊዜ መጠን ነው፡፡ ለማሰብ የምትወስደው ጊዜና የምታስብበት መንገድ፡፡ ጊዜ ወስደህ ባሰብህ ቁጥር ያለኸው ጨለማ ውስጥ አለመሆኑን ታውቀዋለህ፡፡ እስኪ ትንሽ ጊዜ እንውሰድ››

ሁለቱም ጥቂት ጊዜ ተቀመጡ፡፡

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

1.ታሪኩን ከማንበባችሁ በፊት የገመታችሁት ትክክል ሆነ ወይስ አልሆነም? ለምን ?በማስረጃ ግለጹ፡፡

2. በልቦለዱ የስካሁኑ ክፍል ምንምን ነጥቦች ተነሱ

3.ታሪኩ በምን መልኩ ይቋጫል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማሰረጃችሁስ ምንደነዉ?

ያ ልጅም ማየት ጀመረ፡፡

‹‹እስከዚያ በዓለም ላይ ታዋቂ የሆነውን ‹የተጠማውን ቁራ ታሪክ› ልንገርህ፡፡ ቁራው ውኃ ጠማውና በአካባቢው ወዲያና ወዲህ እያለ መፈለግ ጀመረ፡፡ ግን አላገኘም፡፡ በመጨረሻም በውኃ ጥም ወደቀ፡፡ ነገር ግን ተስፋ ለመቁረጥ አልፈለገምና እንደምን ብሎ ተነሥቶ አካባቢውን ማማተር ጀመረ፡፡ በሩቁም አንድ ገንቦ አየ፡፡ ወድቆ እየተነሣ ገንቦው ጋ ደረሰ፡፡ ሲያይ ጥቂት ውኃ ውስጡ አለ፡፡ ምንቃሩን አስገብቶ ሊጠጣ ሲሞክር የገንቦው አንገት ጠባብ ስለነበር አልቻለም፡፡ ገንቦውን ሊያዘነብለው ሲገፋውም ዐቅሙ ተዳክሞ ነበርና ያንን ከባድ ገንቦ መግፋት አልተቻለውም፡፡

‹‹ማሰብ ጀመረ፡፡ መንገድ ከውስጥ ነውና ውስጡ መንገድ ፈለገ፡፡ መንገዱንም አገኘው፡፡ በአካባቢው ያሉትን ጠጠሮች እየለቀመ ወደ ገንቦው ውስጥ መጣል ጀመረ፡፡ ለብዙ ጊዜ ሲጥል ገንቦው በጠጠር እየተሞላ ውኃውም ወደ ላይ እየወጣ መጣ፡፡ በመጨረሻም የገንቦውን ታችኛውን ክፍል ድንጋዩ ሞላውና ውኃው ወደ ገንቦው አፍ ደረሰ፡፡ ቁራውም ጠጣ፡፡››

በታሪኩ ትረካ መካከል ልጁ አንዳች ቅርጽ ያለው ነገር ተመለከተ፡፡ መሥመር ያለው ነገር፡፡ ከወለሉ ጀምሮ ወደ ጣራው የተሠመረ፡፡ ዓይኑን ከታች ወደ ላይ እያንከባለለ ተከተለው፡፡ አንዳች የብርሃን መሥመር፡፡ ቀጭን የብርሃን መሥመር፡፡ ከታች ወደ ላይ ሄደና እንደገና ወደ ግራ ዞረ፤ ተከተለው፡፡ ከግራ ደግሞ ወደ ታች ተጠመዘዘ፤ አብሮትም ሄደ፡፡ ከዚያም ተመልሶ ወለል ላይ ደረሰ፡፡

‹‹ያ የብርሃን መሥመር ምንድን ነው›› አለው ጠቢቡን፡፡

‹‹ጠጋ ብለህ እየው››

ፈራ፡፡

‹‹አትፍራ ጨለማውን ሳትፈራ እንዴት ብርሃኑን ትፈራለህ፡፡ ምንጊዜም የማያውቁት ነገር ያስፈራል፡፡ ሂድ ተጠጋ፡፡

ሄደና ተጠጋ፡፡ የጣውላ በር በሚመስለው ነገር ዙርያ የሚገባ ብርሃን ነው፡፡

‹‹እስኪ ንካው›› አለው ጠቢቡ፡፡ እየፈራ እየደፈረ ነካ አደረገው፡፡ ጣውላ ነገር ነው፡፡

‹‹በምትችለው ዐቅም ሁሉ ግፋው›› አለው፡፡ ላቡ ጠብ እስኪል ገፋው፡፡ ሲጢጢጥ እያለ፤ በመጨረሻ ያ ጣውላ የመሰለ በር ነገር ወደ ኋላው ወደቀ፡፡ ያን ጊዜ በውጭ ያለው ብርሃን ፏ ብሎ ገባ፡፡ ዓይኑን ጨፈን አድርጎ ሲገልጠው በበሩ ፊት ለፊት ሰፊ መንገድ አለ፡፡

‹‹በሕይወትህ ለመለወጥ ከፈለግህ ሦስቱን መሠረታዊ ነገሮች አሁን ተምረሃለል›› አለው፡፡

‹‹ምንድን ናቸው?››

‹‹መጀመርያ እምነት ነው፡፡ ምንጊዜም መንገድ አለ፡፡ ሊዘጋ የማይችል፤ ሊታጠር የማይችል፤ መንገድ አለ፡፡ እርሱም አንተ ውስጥ ነው፡፡ ሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡ ጊዜ ስጥ፡፡

ለማሰብ ጊዜ ይኑርህ፣ ለመፈለግ ጊዜ ይኑርህ፣ ምንጊዜም በፍለጋ ላይ ሁን፡፡ አሁን ያልታየህ ቆይቶ ይታይሃል፡፡ ነገር ለመቁረጥ እንጂ ተስፋ ለመቁረጥ አትቸኩል፡፡ ‹ገና አላገኘሁትም› በል እንጂ ‹የለም› አትበል፡፡ አለ፤ ግን አልደረስክበትም፡፡ መድረስ ጊዜና ጥረት ይጠይቃል፡፡ ሦስተኛው ነገር ያገኘኸውን አጋጣሚ ንካው፡፡ ያገኘኸውን ብርሃን ንካው፡፡ ካልነካኸው በሩ ግድግዳ እንደሆነ ይቀራል፡፡ ከነካኸው ግን በሩ መንገድ ይሆናል፡ ፡ ብርሃን ማየትህ ብቻ ዋጋ የለውም፤ ብርሃኑ በሚገባ እንዳይገባ ያደረገውን ነገር መንካት አለብህ፡፡ እስኪወድቅና ብርሃኑ በሚገባ እስኪገባ፣ መንገዱም ወለል እስኪል መግፋት፡፡

‹‹ሳይነኩት በምኞት ብቻ የሚወገድ ችግር የለም፤ የሚከፈትም በር የለም፡፡ አየህ ማሰብ የብርሃን ጭላንጭልን አሳየህ፤ ጊዜ ሰጥቶ ማስተዋል ይህንን በር ገለጠልህ፤ መንካት ደግሞ መንገዱን አሳየህ፡፡ አሁን አይበቃህም››

‹‹ይበቃኛል››

‹‹ታድያስ አሁን ምን አለህ››

‹‹ገመድ አለኝ››

‹‹ሂድ ጊዜ ሰጥተህ፣ መጣፍ አገላብጠህ፣ ዐዋቂ ጠይቀህ፣ ግራ ቀኙን አስብ፡፡ ይህች ገመድ ሕይወትህን የመለወጫ ምክንያት ትሆንሃለች፡፡ የባለጸግነት መጀመርያ፣ የሥልጣን እርከን፣ የሊቅነት ፋና፣ የጀግንነት መንሥኤ ትሆንሃለች፡፡ ያለበለዚያ ደግሞ የመታነቂያ መሣርያ ትሆንሃለች፡፡ ሁለቱም በእጅህ ነው፡፡››

አሰናበተውና ሄደ፡፡

ከጦማሪ ዲ/ን ዳንኤል ክብረት የተወሰደ

***መልመጃዎች***

**ክፍል አንድ ፡- ምንባብ**

***የሚከተሉ ጥያቄዎችን በልቦለዱየመጀመሪያ ክፍል መሰረት ትክክል ከሆነ እዉነት ስህተት ከሆነ ሀሰት በማለት መልሱ የመልሳችሁንም ምክንያት ከጽሁፉ ዉሰጥ በመፈለግ ግለጹ፡፡***

1.ሁለት ወንድማማቾች እናታቸው ስታርፍ በቤት ውስጥ ያገኙት አንድ ትልቅ ገመድ ብቻ ነበር፡፡

2. በመበሳጨቱ ምክንያት ገመዱን ጣራ ላይ ወረወረውና ከቤት ወጥቶ የሄደዉ ታናሹ ልጅ ነበር፡፡

3. ገመዱ የእናቱ ቅርስ መሆኑን ተርድቶ እንደምንም ከጣራ ላይ ገመዱን ያወረደው ታናሹ ልጅ ነው፡፡

4. ሁለቱም ወንድምማማቾች የእናታቸዉን ቅርስ የነበረዉን ገመድ ለማዉረድ ጣራዉ ላይ ወጥተዉ ነበር፡፡

**ልቦለዱን መሰረት በማደረግ የሚከተሉ ጥያቄዎችን በቃል መልሱ፡፡**

1. ታላቁ ልጅ የእናቱን ቅርስ የሆነዉን ገመድ ጣራ ላይ ያስወረወረዉ ምክንያት ምድነዉ?
2. ‹‹መንገድ ያለው ከውጭ አይደለም፡፡ መንገድ ያለው ከውስጥ ነው፡፡ ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እደሆነ አብራሩ፡፡
3. ብዙዎቹ በልቡናቸው ሳያዩ የጓዙበታል ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እደሆነ አብራሩ፡፡

4. ‹‹ሳይነኩት በምኞት ብቻ የሚወገድ ችግር የለም፤ሲል ምን ለማለት ፈልጎ እደሆነ አብራሩ፡ ፡

**ዋና ዋና የሆኑትን የልቦለዱን ድረጊቶች በቅደም ተከተል አስቀምጡ ፡፡ይህንን ስታደረጉ ጥንድ ጥንድ ሆናቸሁ በመወያየት ና የሚከተለውን አስቀምጡ**

ድርጊት 1. ታላቁ ልጅ እጅግ በመበሳጨቱ ገመዱን ጠቅልሎ ጣራ ላይ ወረወረው

ድርጊት 2 ----------

ድርጊት 3 -----------

ድርጊት 4 ---------

**ክፍል ሁለት፡-**

**በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ተወያያና የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞቻችው አቅርቡ ፡፡**

1. ‹ ሰዎቸ ለምንድን ነው ከብርሃን ይልቅ ጨለማን የሚፈሩት

2.በቤታቸሁ በሬድዮ ስላዳመጣችሁት ልቦለድ

3.መምህራችሁ አጭር ጽሁፍ ያነብላችኋል በጥሞና አዳምጣችሁ በ ፤ሀ ፤ስር የተገለጹትን ገለጻዎች በ ፤ለ፤ ስርከተዘረዘሩትገላጮችጋር አዛምድ

| <u>ሀ</u> | <u>ለ</u> |
|---|---|
| 1. የወሃ መቅጃ | <u>ሀ</u> እንስራ |
| 2. ብረሃን | ለ .ጠቁር |
| 3. ጠቁር | ሐ .መብራት |
| 4. ቁራ | መ. አሞራ |

**ክፍል ሦስት፡**

**ከልቦድ ሌሎች የፈጠራ ስራዎች ጋር በተያያዘ የተደረጉ ዉይይቶችን የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ወዘተ ከሬድዮከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ ጠቃሚ ሀሳብኑዉ የምትሉትን በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍሉ አቅርቡ**

ጽሁፋች -የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ

- መንሴዔና ዉጤትን ያገናዘበ መሆኑን ያረጋግጡ

በአጭር ልቦወለድ ዉስጥ ሁለቱ ገጸባህሪያት የጠበቀ መቀራረብ ከፍተኛ የመፌተሔ ሃሳብ እዲያገኝ ጠቅሞታል ወይስ አልጠቀመዉም በሚለዉ በሚለዉ በቡድን ሆናችሁ ሀሳባችሁንሚክናታዊ በመሆን ተከራከሩ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ፡፡

**በክርክር ጊዜ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ስጡ**

-በቂ ዝግጅት ማዘጋጀት

-ከርዕሱ ጋር የተያያዙ ሀሳቦችን ማቅረብ

-የቀረቡ ሃሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ማረጋገጥ

-ተራ ጠብቆ መናገር

-የሌላዉን ሰዉ ሀሳብ አለማንቋሸሽ

-ለተቃዋሚ ሃሳብ ተገቢ መልስ መስጠት

**ክፍል አራት**

**ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በልቦለድ ዉስጥ ያላቸዉን ፍች የሚሳዩ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ**

1.አብረን 4.ቀዳዳ

2.ብረሃን 5.መስመር

3.ጠቢቡ 6.ገመድ

**ክፍል አምስት ፡-**

**የቃላት እማራዊና ፍካራዊ ፍች**

አንዳንድ የአማረኛ የቃላት እማራዊና ፍካራዊ ፍችዎች አሏቸዉ እማራዊ ፍች የሚባለዉ የቃሉ ቀጥተኛ ወይም መዝገበ ቃለዊ ፍች ነዉ፡፡ ፍካራዊ ፍች ደግሞ ዋሉ ከቀጥተኛ ፍችዉ ባሻገር የሚሰጠዉ

ምሳሌ፡- ቤት፡ የሚለዉ ቃል በእማራዊ ፍችዉ ግርግዳ ጣሪያ ያለዉ የሰዉ ልጅ ምሳሌ መኖሪያ ቤት ማለት ሲሆን ፍካራዊ ፍችዉ ደግሞ የአንድ ሰዉ ጠቅላላ ኑሮ ትዳር ወዘተ ማለት ነዉ፡፡

**የሚከተሉትን ቃላት እማሪያዊና ፍካራዊ ፍች በቀረበዉ ምሳሌ መሰረት በሰንጠረዥ ዉስጥ አስቀምጡ**

| | ቃል | እማራዊ ፍች | ፍካራዊ ፍች |
|---|---|---|---|
| | እባብ | በደረቱ የሚሳብ መርዛማ ፍጡር | መሰሪ፡ተንኮለኛ |
| 1 | ንብ | | |
| 2 | ርግብ | | |
| 3 | ድንጋይ | | |
| 4 | ጨለማ | | |
| 5 | ብረሃን | | |

**የሚከተሉትን ቃላት እማራዊ ና ፍካራዊ ፍችዎች በጥንድ በጥንድ ሆናችሁ ከተወያያችሁ በኃላ በአረፍተ ነገር አስገብታችሁ አሳዩ፡፡**

1.ገመድ 3.ጠባብ

2. መንገድ 4.ጣሪያ

**እማሪያዊና ፍካራዊ ፍች ያላቸዉን አምስት ቃለት ሰብስባችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በሚከተለዉ ሰንጠረዥ አቅርቡ ና በፍችዎቻቸዉ ላይ ተወያዩ፡፡**

| | ቃል | የቃሉ | |
|---|---|---|---|
| | | እማራዊ ፍች | ፍካራዊ ፍች |
| ሀ | | | |
| ለ | | | |
| ሐ | | | |
| መ | | | |

**ክፍል ስድስት ፡**

**በዚህ ምዕራፍ ትምህርት ዉስጥ መጀመሪያ ላይ አንድ ገመድ አለኝ የሚል አጭር ልቦለድ አንብባችል፡፡አሁንም እደገና አንብባችሁ የሚከተሉትንጥያቄዎች በበልቦወለዱ መሰረት መልሱ፡፡**

1.ልቦለዱን አጭር ልቦለድ ያሰኙት ምክንያቶች ምን ምን ናቸዉ?

2. ልቦለድ ዉስጥ ያሉ ገፀባህሪያትን ዘርዝሩ ፡፡

3.የዚህ ልቦለድ ዋና ጭብጡን አዉጥታችሁ ከጻፉችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አብራሩ፡፡

4.አንድ አጭር ልቦለድ አንብባችሁ ማስታወሻ ከወሰዳችሁ በኋላ በራሳችሁ አባባል

**ዘይቤዎችና ፈሊጣዊ ንግግሮች**

ልዩ ልዩ ዜይቤዊ አነጋገሮች

እንደአንበሳ ጠንካራ ነዉ

ልጅቷ ንብ ነች

ለሰዉ ሞት አነሰዉ  አለች ቀበሮ

ዜይቤ ና ፈሊጣዊ ንግግሮችን ጠይቃችሁ ጽፉችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

**ፈሊጣዊ ንግግሮች**

ቀለም ያዘ

ሆዱ ቆረጠ

አደብ ገዛ

እነዚህ ከላይ የዘረዘርናቸዉ የፈሊጣዊ ንግግሮች  ምሳሌዎች ናቸዉ በእነዚህ ምሳሌዎች መሰረት  ሌሎች ፈሊጣዊ ንግግሮችን ጻፉ

የዜይቤና የፈሊጣዊ ንግግሮች አንድነት እና ልዩነታቸዉን ጻፉ

# አባሪ "መ"

## የቅድመ ፈተና የፓይለት ዉጤት

የቅድመ ፈተና የፓይለት ዉጤት ከ40

| ተ.ቁ | የተማሪዎች መለያ ቁጥር | | | | | | | | | | | | የትክክለኛ መልስ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | |
| 1 | √ | X | X | √ | √ | √ | X | X | X | √ | X | X | 5 |
| 2 | X | X | X | X | √ | √ | X | X | x | √ | X | X | 3 |
| 3 | X | X | √ | √ | X | x | √ | √ | X | X | X | X | 4 |
| 4 | √ | √ | X | X | X | X | √ | √ | √ | √ | X | X | 6 |
| 5 | X | √ | √ | √ | X | X | X | X | √ | √ | X | √ | 6 |
| 6 | X | √ | X | x | √ | √ | √ | X | √ | X | X | X | 5 |
| 7 | √ | x | X | X | √ | x | √ | X | √ | X | X | X | 5 |
| 8 | √ | x | x | √ | X | √ | √ | X | X | X | X | X | 4 |
| 9 | √ | √ | √ | X | √ | X | X | X | √ | X | √ | X | 4 |
| 10 | X | √ | √ | √ | X | X | √ | X | √ | X | √ | √ | 7 |
| 11 | X | √ | √ | X | X | X | √ | X | √ | X | X | X | 4 |
| 12 | √ | x | X | X | √ | X | √ | X | √ | √ | X | X | 3 |
| 13 | √ | x | X | X | X | X | X | √ | √ | X | X | X | 3 |
| 14 | X | x | X | √ | √ | √ | X | X | X | √ | X | X | 4 |
| 15 | √ | x | X | X | X | X | √ | X | √ | X | X | √ | 4 |
| 16 | X | √ | √ | X | X | X | X | X | X | √ | X | x | 3 |
| 17 | √ | √ | √ | X | X | X | √ | X | X | √ | X | X | 5 |
| 18 | √ | √ | X | X | √ | √ | X | √ | √ | X | X | X | 6 |
| 19 | √ | √ | √ | √ | X | X | X | √ | X | √ | X | X | 6 |
| 20 | X | x | X | X | √ | √ | √ | X | X | √ | X | √ | 5 |
| 21 | X | √ | X | √ | X | √ | X | X | √ | X | X | x | 4 |
| 22 | √ | x | √ | X | X | √ | X | X | X | √ | X | √ | 6 |
| 23 | X | √ | X | X | X | √ | √ | X | √ | X | √ | √ | 6 |
| 24 | X | √ | X | X | √ | √ | X | X | √ | √ | X | X | 5 |
| 25 | X | √ | √ | X | √ | √ | X | √ | X | √ | X | √ | 7 |
| 26 | √ | x | X | X | X | X | X | X | X | √ | X | √ | 3 |
| 27 | √ | √ | X | √ | X | X | X | X | √ | √ | √ | √ | 7 |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 28 | X | x | √ | X | √ | √ | X | √ | X | √ | X | x | 5 |
| 29 | X | √ | X | X | X | X | X | √ | √ | X | √ | x | 4 |
| 30 | √ | √ | X | X | X | X | √ | X | X | X | X | x | 3 |
| 31 | X | x | √ | √ | X | X | X | X | X | X | √ | √ | 4 |
| 32 | √ | √ | X | X | X | X | X | √ | X | X | √ | √ | 4 |
| 33 | √ | x | X | X | X | √ | X | √ | X | X | X | x | 3 |
| 34 | X | x | √ | X | X | X | √ | X | X | X | √ | x | 3 |
| 35 | X | √ | X | X | X | X | X | √ | √ | X | X | √ | 4 |
| 36 | √ | x | √ | X | X | X | X | √ | X | X | √ | √ | 5 |
| 37 | √ | x | X | X | √ | X | √ | X | X | X | √ | √ | 5 |
| 38 | X | √ | X | X | X | X | √ | √ | X | √ | X | √ | 5 |
| 39 | √ | √ | X | X | X | √ | √ | √ | X | √ | √ | x | 7 |
| 40 | √ | √ | X | √ | X | X | X | X | √ | X | √ | √ | 6 |
| ትክክለኛ መልስ ድምር | 21 | 22 | 14 | 11 | 13 | 15 | 17 | 14 | 18 | 18 | 12 | 16 | |

# አባሪ “ሰ”

## የሙከራ ና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት

የሙከራ ና የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት

| ተ.ቁ | የሙከራ ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት | የቁጥጥር ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት | |
|---|---|---|---|
| 1 | 21 | 1 | 18 |
| 2 | 18 | 2 | 21 |
| 3 | 16 | 3 | 16 |
| 4 | 14 | 4 | 14 |
| 5 | 17 | 5 | 19 |
| 6 | 19 | 6 | 17 |
| 7 | 20 | 7 | 19 |
| 8 | 18 | 8 | 21 |
| 9 | 21 | 9 | 18 |
| 10 | 19 | 10 | 20 |
| 11 | 16 | 11 | 16 |
| 12 | 15 | 12 | 14 |
| 13 | 14 | 13 | 15 |
| 14 | 13 | 14 | 21 |
| 15 | 21 | 15 | 13 |
| 16 | 18 | 16 | 18 |
| 17 | 17 | 17 | 15 |
| 18 | 17 | 18 | 17 |
| 19 | 15 | 19 | 17 |
| 20 | 22 | 20 | 22 |
| 21 | 13 | 21 | 13 |
| 22 | 15 | 22 | 15 |
| 23 | 16 | 23 | 16 |
| 24 | 12 | 24 | 12 |
| 25 | 14 | 25 | 14 |
| 26 | 21 | 26 | 20 |
| 27 | 17 | 27 | 17 |
| 28 | 16 | 28 | 16 |
| 29 | 18 | 29 | 18 |
| 30 | 20 | 30 | 20 |
| 31 | 21 | 31 | 21 |
| 32 | 23 | 32 | 23 |

# አባሪ “ረ”

## የድህረ ፈተና የፓይለት ውጤት

| የጥያቄ ቁጥር | የተማሪዎች መለያ ቁጥር | | | | | | | | | | | የትክክለኛ መልስ ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | |
| 1 | √ | × | × | √ | √ | x | X | X | x | √ | x | X | 4 |
| 2 | X | x | X | X | √ | √ | X | X | | √ | x | X | 3 |
| 3 | X | x | √ | √ | X | X | √ | √ | x | X | x | X | 4 |
| 4 | √ | √ | X | X | X | X | √ | √ | x | √ | x | X | 5 |
| 5 | X | √ | √ | √ | X | X | X | X | √ | √ | x | √ | 6 |
| 6 | X | √ | X | x | √ | √ | √ | X | √ | X | x | X | 5 |
| 7 | √ | x | X | X | √ | x | √ | X | √ | X | x | X | 5 |
| 8 | √ | x | x | √ | X | √ | √ | X | x | X | x | X | 4 |
| 9 | √ | √ | √ | X | √ | X | X | X | √ | X | √ | X | 4 |
| 10 | X | √ | √ | √ | X | X | √ | X | √ | X | √ | √ | 7 |
| 11 | X | √ | √ | X | X | X | √ | X | √ | X | x | X | 4 |
| 12 | √ | x | X | X | √ | X | √ | X | √ | √ | x | X | 3 |
| 13 | √ | x | X | X | X | X | X | √ | √ | X | x | X | 3 |
| 14 | X | x | X | √ | √ | √ | x | X | x | √ | x | X | 4 |
| 15 | √ | x | X | X | X | X | √ | X | √ | X | x | √ | 4 |
| 16 | X | √ | √ | X | X | X | x | X | x | √ | x | X | 3 |
| 17 | √ | √ | √ | X | X | X | √ | X | x | √ | x | X | 5 |
| 18 | √ | √ | X | X | √ | √ | x | √ | √ | X | x | X | 6 |
| 19 | √ | √ | √ | √ | X | X | x | √ | x | √ | x | X | 6 |
| 20 | X | x | X | X | √ | √ | √ | X | x | √ | x | √ | 5 |
| 21 | X | √ | X | √ | X | √ | x | X | √ | X | x | x | 4 |
| 22 | √ | x | √ | X | X | √ | x | X | x | √ | x | √ | 6 |
| 23 | X | √ | X | X | X | √ | √ | X | √ | X | √ | √ | 6 |
| 24 | X | √ | X | X | √ | √ | x | X | √ | √ | x | X | 5 |
| 25 | X | √ | √ | X | √ | √ | x | √ | x | √ | x | √ | 7 |
| 26 | √ | x | X | X | X | X | x | X | x | √ | x | √ | 3 |
| 27 | √ | √ | X | √ | X | X | x | X | √ | √ | √ | √ | 7 |
| 28 | X | x | √ | X | √ | √ | x | √ | x | √ | x | x | 5 |
| 29 | X | √ | X | X | X | X | x | √ | √ | X | √ | x | 4 |
| 30 | √ | √ | X | X | X | X | √ | X | x | X | x | x | 3 |
| 31 | X | x | √ | √ | X | X | x | X | x | X | √ | √ | 4 |
| 32 | √ | √ | X | X | X | X | x | √ | x | X | √ | √ | 4 |
| 33 | √ | x | X | X | X | √ | x | √ | x | X | x | x | 3 |
| 34 | X | x | √ | X | X | X | √ | X | x | X | √ | x | 3 |
| 35 | X | √ | X | X | X | X | x | √ | √ | X | x | √ | 4 |
| 36 | √ | x | √ | X | X | X | x | √ | x | X | √ | √ | 5 |
| 37 | √ | x | X | X | √ | X | √ | X | X | X | √ | √ | 5 |
| 38 | X | √ | X | X | X | X | √ | X | X | X | X | x | 2 |
| 39 | √ | √ | X | X | X | X | x | X | X | √ | √ | x | 3 |
| 40 | √ | √ | X | √ | X | X | x | X | √ | X | √ | √ | 6 |
| ትክክለኛ መልስ ድምር | 21 | 22 | 14 | 11 | 13 | 14 | 16 | 12 | 18 | 17 | 12 | 15 | |

## አባሪ “ሽ “

### የሙከራና የቁጥጥር ቡድን  ድህረ ፈተና  ዉጤት

| የሙከራ  ቡድን  ድህረ ፈተና  ዉጤት | | የቁጥጥር  ቡድን  የድህረ ፈተና ዉጤት | |
|---|---|---|---|
| 1 | 23 | 1 | 17 |
| 2 | 28 | 2 | 20 |
| 3 | 27 | 3 | 15 |
| 4 | 23 | 4 | 18 |
| 5 | 22 | 5 | 15 |
| 6 | 18 | 6 | 16 |
| 7 | 33 | 7 | 20 |
| 8 | 32 | 8 | 18 |
| 9 | 25 | 9 | 17 |
| 10 | 25 | 10 | 19 |
| 11 | 26 | 11 | 20 |
| 12 | 24 | 12 | 14 |
| 13 | 23 | 13 | 16 |
| 14 | 22 | 14 | 15 |
| 15 | 24 | 15 | 21 |
| 16 | 28 | 16 | 14 |
| 17 | 23 | 17 | 16 |
| 18 | 19 | 18 | 16 |
| 19 | 30 | 19 | 15 |
| 20 | 28 | 20 | 17 |
| 21 | 32 | 21 | 22 |
| 22 | 20 | 22 | 20 |
| 23 | 25 | 23 | 19 |
| 24 | 24 | 24 | 17 |
| 25 | 29 | 25 | 16 |
| 26 | 22 | 26 | 20 |
| 27 | 22 | 27 | 15 |
| 28 | 26 | 28 | 13 |
| 29 | 21 | 29 | 15 |
| 30 | 26 | 30 | 14 |
| 31 | 19 | 31 | 14 |
| 32 | 29 | 32 | 21 |

# አባሪ “ቀ”

## የተሰላ የSPSS ውጤት

### የቅድመ ፈተና የፓይለት ዉጤት

**Reliability Statistics**

| Cronbach’s Alpha | N of Items |
|---|---|
| .754 | 40 |

### የድህረ -ፈተና የፓይለት ዉጤት

**Reliability Statistics**

| Cronbach’s Alpha | N of Items |
|---|---|
| .766 | 40 |

**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | pretest1 | 17.41 | 32 | 2.928 | .518 |
| | pertest2 | 17.38 | 32 | 2.893 | .511 |
| Pair 2 | Post test experiment | 24.94 | 32 | 3.893 | .688 |
| | Post test conterol | 17.03 | 32 | 2.495 | .441 |

**Paired Samples Test**

| | | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 | pretest1 - pertest2 | .031 | 2.443 | .432 | -.849 | .912 | .072 | 31 | .943 |
| Pair 2 | Post experiment - post test conterol | 7.906 | 3.913 | .692 | 6.495 | 9.317 | 11.429 | 31 | .000 |


**Paired Samples Statistics**

| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|---|
| Pair 1 | pretest1 | 17.41 | 32 | 2.928 | .518 |
| | pertest2 | 17.38 | 32 | 2.893 | .511 |
| Pair 2 | Post test experiment | 24.94 | 32 | 3.893 | .688 |
| | Post test conterol | 17.03 | 32 | 2.495 | .441 |

| Paired Samples Test | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
| | | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 | pretest1 - pertest2 | .031 | 2.443 | .432 | -.849 | .912 | .072 | 31 | .943 |
| Pair 2 | Post test experiment - posttestcoterole | 7.906 | 3.913 | .692 | 6.495 | 9.317 | 11.429 | 31 | .000 |

| Paired Samples Statistics | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | Mean | N | Std. Deviation | Std. Error Mean |
| Pair 1 | pretest1 | 17.41 | 32 | 2.928 | .518 |
| | pertest2 | 17.38 | 32 | 2.893 | .511 |
| Pair 2 | Post test experiment | 24.94 | 32 | 3.893 | .688 |
| | Post test control | 17.03 | 32 | 2.495 | .441 |

| Paired Samples Test | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Paired Differences | | | | | t | df | Sig. (2-tailed) |
| | | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean | 95% Confidence Interval of the Difference | | | | |
| | | | | | Lower | Upper | | | |
| Pair 1 | Pre test1 - per test2 | .031 | 2.443 | .432 | -.849 | .912 | .072 | 31 | .943 |
| Pair 2 | Post test experiment - post test control | 7.906 | 3.913 | .692 | 6.495 | 9.317 | 11.429 | 31 | .000 |